መስተአየት

ራስ ታዘብና ተሓድሶአውያን መጣጥፎች

ንጉሤ ቡልቻ

ሐምሌ ፪ ሺህ ፪ ዓመተ ምሕረት
አዲስ አበባ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved

Copyright © 2010 Negussie Bulcha
መ.ሣ.ቁ 30723 ስ.ቁ 0911219851
Email su_ethiopia@yahoo.com

በሊቪንግ ትሩዝ አገልግሎት የታተመ

ምስጋና

1. ከጧቱ ጀምሮ አሳብ በመስጠት ጽሑፎቹን በማንበብና ምክር በመለገስ ለሕትመቱ ገንዘብ በማፈላለግ በሌሎችም መንገዶች ሁሉ ሥራውን ላበረታቱት የ LIVING TRUTH አባላት አቶ ሰሎሞን ከበደ፣ ዶ/ር አታላይ ዓለም፣ አቶ ፈቀደ ተፈራ፣ ዶ/ር ሽመልስ አድማሴ እና ወ/ሮ ሜሪ ላቀው
2. መጣጥፎቹን አንብበው ለጋሥ አስተያየታቸውን ለሰጡት ለዶ/ር ንጉሤ ተፈራ አቶ ጌታቸው በለጠና አቶ ሰሎሞን ጥላሁን
3.. በቀዳሚው ትየባ ለተባበሩት የቢብሊካ ኢትዮጵያ ጸሐፊዎች ዕሠይና ቤተልሔም — በመካተቻው ትየባ እና የገጽ ቅንብር ሥራ በትጋት ለሠሩት የቃለ እግዚአብሔር አንባቢዎች ማኅበር አባላት ብርሃኑ ሰለሞን ቅድስት ፈይሣና ረድኤት ሰለሞን እንዲሁም እዚህ ስሞቻቸው ያልተጠቀሱ በቀኝም በግራም ለሥራው ልዩ ልዩ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሁሉ ልዑል አምላክ በረከቱን ያዝንብላችሁ እያልሁ ምርቃቴን ና ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በዚህ ግቡ

"መስተአየት" የሚባል ቃል የለም። ጽፈት ያልለመዱ ጨዋዎች ግን መስታውትን "መስታየት" ማለታቸው የታወቀ ነው። የቋንቋ ቅልጥፍና ወግም ይህንኑ ያጸድቃል እንጂ አይኰንንም። በግዕዝ ቋንቋ ደግሞ "መስተ" የሚለው የተግባር መግለጫያ ፊት ደቀን የተለመደ ነው፤ መስተዋድድ÷ መስተጻምር÷ መስተጋብር እንዲሉ። እንግዲያው መስተአየት "አየ" በሚለው የአማርኛ ግሥ ላይ የተጣበቀውን የግዕዝ ፊት ደቀን ይዞ አንድ ቃል ሆነ። ፍቺውም «ማያ÷ ማሳያ ÷መታዘቢያ» እንደ ማለት ነው። «ለዚህማ ከሆነ ያው መስታወት የሚለው ቃል ነበረልህ አይደል አዲስ ለመፍጠር ምን አደከመህ» ቢባልስ? አሞ ይቻል ነበር፤ የትኩረት ስግብግብነቱ ጐትቶኝ ነው እንጂ።

"ቃሉስ ይሁን ግን የሚታየው የምንታዘበው ምኑን ነው።" ቢባልስ? ያው እኛኑ ነው፤ ኑሮአችንን ሕይወታችንን ግንኙ ነቶቻችንን ፍልስፍናችንን በዕለት ውጣ ውረድ አባሮሽ በውልብታ የምናየውን (አሱንም ማየታችንን እንጃ) በርጋታ ስናይ የምንፋጠጠውን የኛን የራሳችንን መልክ ነው። በአብዛኛው የወንጌላዊው ማኅበረሰብ ገጽታ ተያይዞም የሌላው ሰው ሁሉ ልቡናዊ መልክ የቀረበበት ሰሌዳ ነው።

ማየቱ እንደ ትዕይንቱ ዐይነት ራስ ይዞ ለመጮኽ ይረዳናል፣ በራሳችን እንድንስቅ ያግዘናል÷ ታዳጊ ፍለጋ ይቀሰቅሰናል፣ የላላ መቀነት የተፈታ ሱሪ ጠበቅ እንድናደርግ ይጠቅሰናል፤ የተስፋ ወጋገን ይፈነጥቅልናል ወዘተርፈ። እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚሆነው ከሃሌ ኩሉ አምላክ ስንጽፍና ስናነብ አብሮን የሆነ እንደ ሆነ ነው። አብሮን ይሁን።

ከእነዚህ መጣጥፎች አብዛኞቹ ካለፉት 18 ዓመታት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በተለያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች ላይ ቀርበው የነበሩ ሲሆኑ በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ ገና ብቅ ማለታቸው ነው። ከዚህ የጊዜና የአርእስተ ጉዳይ ስርጭት የተነሣ ሁሉን ባንድ ወንዝ ለማፍሰስ ሙከራ ሲደረግ ወጣ ገባነት ቢታይ «ጠባዩ ነው» ብሎ ማለፍ ብቻ ይበቃል። ይሁን እንጂ ለአንባቢ ከሞላ ጉደል የተመቸ ፈር ለማስያዝ ብዬ በአራት ተናጠልና ተያያዥ ምዕራፎች ሰድሬአቸዋለሁ። እያንዳንዱ ስድር በርዕሰ ጉዳይ ተቀራራቢነት ያላቸውን መጣጥፎች ይዞአል። ይህ የምዕራፍ አከፋፈል በፍጹም ፍጹማዊነት የለውም፤ አከፋፈሉም እንደሚከተለው ነው፤

፩፡ <u>ደጃፌ ላይ ቆሜ</u>፡-

የቤቴን መሠረት ሳልለቅ የውስጡ ሙቀት እየተሰማኝ ዙሪያ ገባውን ለመቃኘት የተደረገ ሙከራ ነው። ራሴን ጨምሮ ሁሉን ታዛቢ እይታ ነው። የኛን ትውልድ አካሄድ ለመመዘን የተደረገ ጥረት ነው።

፪፡ <u>ጓዳዬን ስፈትሽ</u> ፡-

በተለይ የክርስቶስን ማኅበረሰብ ሕይወት ትስስሩንና ዕድገቱን ወይም በሽታውንና ክሳቱን መስለምለሙንና መለምለሙን በሰቀቀንና በተስፋ እየቃኘ ከጥሪው ጋር የሚያገናዝብ እይታ ነው።

፫፡ <u>አምባ ወጥቼ</u>፡-

ስለጠቅላላው ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ ድነት ለማሰብ የተደላደለ አፋፍ (የወንጌል ጉብታ) ላይ ቆሞ ጎይለ እግዚአብሔርንና ጥበበ

እግዚአብሔርን ከኑሮ ጋር ለማቆራኘት የሚሞክር ሰፊ እይታ ነው።

፬ <u>መቅደስ ውስጥ ስገባ</u>፡ የትዝብቶች፥የሰቀቀኖች፥የተስፋ-ዎች ሁሉ ማካተቻ ወደ ሆነው ወደ ሰማየ ሰማያት ለማሻቀብ እንዲረዳ በመቅደሱ በኩል ወደ ላይ ያንጋጠጥሁበትና የተሓድሶ ዝናብ የተጠባበቅሁበት ምልከታ ነው፡

የመጨረሻዎቹ ገጾች የመፍትሔ ቃላት ገበታ ይዘዋል። ለወጣት አንባብያን ለሌሎችም እንዲመች ዐስቤ ነው። አንዳንዶቹ ቃላት እኔው ያዋቀርኋቸው ናቸው፤ በተለያየ ሁኔታ። የሌሎችን ጥንስስ ዘርፌ ወይም ነባር ቃላት አዛርፌ አዲስ ገጽና ቅርጽ አበጅቼላቸዋለሁ። አንዳንድ ብልሆች የቃላቱን ገበታ ባያዩም እንዲያው በመላ ሊረዱዋቸው የሚችሉ ናቸው። ግን መኖሩን ይኑሩ።

አበርክቶት

ይህ የመጣጥፎች ስብስብ ፡-

የጻፍኩዋቸውን ላነበቡልኝ፣ ጎሽ ያሳድግህ ብለው ለመረቁኝ፣ እባክህ ጻፍ፣ ጻፍ እንጂ! ብለው ላተጉኝ፣ በቅን ልብ ለጸለዩልኝ በቅርብም በሩቅም ላሉ ውድ የእግዚአብሔር ቤተሰብ እና ዙሪያ ዙሪያውን ላሉ ሁሉ በፍቅር ተበርክቷል።

የምለው ሳይሆን የሆንሁት የበለጠ ዋና ነው።

እርሱ ለሰዎች የምነግረውን እንዲሰጠኝ መማጠኔ

የሚፈልገውን ዐይነት ሰው እንድሆን

እንዲሠራኝ ከመማጠን ጋር ሊሆን ይገባል።

እኔ የሆንሁት

ከምናገረው ይበልጥ ይሰማል

በጥቂት ቢሰማ እንኳ ይበልጥ ያሰማል።

የምሆነውም የምናገረውም ተጠቃሎ

ለእርሱ ክብርና

ከክብሩ ለሚወጣ የሰው ብርሃን ይዋል።

ማውጫ ገጽ

1. የአገር ያለህ! 9
2. የባቢሎን እብደት 14
3. ዓላማ የለሽ ዓላማ ያለሽ 19
4. የአንድ ትውልድ ሙሾ 22
5. የነጻነት ያለህ! 30
6. እስር ቤቱን ስበር 35
7. ወጣት አልወጣት 39
8. ለቤተስኪያን ሂያጆች 45
9. ጠባሳ የለህም? 48
10. የክህደት እምነት 50
11. የብርሃን ያለህ! 58
12. የብዙ ዐይነቶች አንድነት 62
13. አይቱ ፍኖታ ለጎብሬ 66
14. ዕርቅ-የጥበብ መንገድ 70
15. ዘጠኝ ወንጀሎች 73
16. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብርሃን ፍለጋ 79
17. የጠማው ንጹሑን ይጠጣ 85
18. በምን አወቅኸው 87
19. የመልእክት ያለህ! 91
20. የተቀባዮች ቅን ድርሻ 98
21. ይፈለጋል የቁጣ ችሎታ 105
22. ጉዳይ አለህ? 110
23. የማን ልጆች ናቸው? 113
24. ሲርበኝ ምን ላድርግ? 116
25. ለእንጀራ ብዬ 122
26. የእግዚአብሔር ልጅ - የሰው ወዳጅ 126
27. የፍቺ አልባነት ማርከሻ 130
28. ልደቱ የለውጥ አብነቱ 133
29. የልደት ስደት- የስደት ልደት 142
30. ነገ ካለ 150
31. የምረቃ ድምቀት 154
32. የብፅዕና ጉዳና 157
33. የጸጋና የእውነት ዝናብ 162
34. የፍቅር ያለህ! 168
35. ለሞት እንዳልተኛ 172
36. ፍኖተ ተሐድሶ 176
37. ጥልቅ ፍስሓ 190
38. ጎይል ጎይል 194
39. ማን ይምራን ምን ይምራን? 203
40. ቀኝና ግራ 208
41. የብላቴንነት ወራት መዝሙር 213
42. ቢዚ- ቢዚ 214
43. ሰው ኑሮውን መሳይ (ትግልና ቅርጽ) 221

መፍትሔ ቃላት 222

፩. ደጃፌ ላይ ቆሜ

1. የአገር ያለህ! 9
2. የባቢሎን እብደት 14
3. ዓላማ የለሽ ዓላማ ያለሽ 19
4. የአንድ ትውልድ ሙሾ. 22
5. የነጻነት ያለህ! 30
6. እስር ቤቱን ስበር 35
7. ወጣት አልወጣት 39
8. ለቤተክሲያን ሂያጆች 45
9. ጠባሳ የለህም? 48

የአገር ያለህ!

የአገራችን ሕሊናዊ በር ለሁሉም ክፍት ሆነ። በፍርሃት ይሁን በድንቁርና በጀብደኝነት ይሁን በአርቆ አስተዋይነት ለብዙ ዘመናት መክተን የያዝነው መዝጊያችን ገርበብ ብሎ ሳይሆን ብርግድ ብሎ ተከፈተ። አሁን ወልጋዳም ጉፋፋም፣ ሃምሳ ቀንድ ያበቀለም ጭራቅ እንዳይገባ የሚከለክል ምንም ዘበኛ የለም። ደግሞ ለክፉቱ በገፍ የሚገባው የተቃናው የለዘበውና የተገራው ሳይሆን ጉዳጉድ ግሳንግሡ ነው።

ድንበራችንን ዘልቆ ሲገባ በእንግዳ አክባሪ ባህላችን ተሳስቀን ተቀብለነው አገሩን ይሄዳል ስንል እዚሁ ተንፈራጥጦ ተቀመጠ። ጭራቁ ሁሉ ቤተኛ ሆነ። ለመሆኑ እዚህ አገር ክፉ አስተሳሰብና ዝቃጭ የሥነምግባር አተላ እንዳይደፋ የሚከለክል ሃይ ባይ ይገኛል?

እስኪ ደግ ደጉን እንናገር፡- ከዓለም ጎብረተሰብ ሥልጣኔ ተራርቃ፣ በዚሁም ምክንያት ኋላ ቀር ሆና የኖረች ኢትዮጵያ ለዕውቀት፣ ለሥልጣኔ፣ ለሥራ ትጋት፣ ለቴክኖሎጂ ቀሰማ፣ ለትውውቅ ለቅርርብ፣ በዚሁም ሳቢያ ለሚገኝ የሸመታ ዕድል በሯን ብትከፍት ምን አለበት? ምንም። ሉልአቀፋዊ (ግሎባል) በሆነ ዓለም ውስጥ በራን ከርችሜ ስለ ዕድገት ማለም የትም አያደርስም።

ገበያው ላይ ያለው ዕቃና አገልግሎት ብቻ በሆነ ኖሮ እጅግም አያሳስብም ነበር። አሁን ግን እየተሸጠ፣ እየተሸመተም ያለው የአስተሳሰብ ዐይነትና የኑሮ ዘይቤ ነው። ከዚሁም አብዛኛው መሠረታውያን የሆኑትን የሰብአና ማልሚያ እምነቶች የሚንድ፣ ሠናያት ምግባራትን የሚያኪያኪስ፣ መለኪያ የለሽነትን የሚያራግብ፣ እብደትን የሕይወት ፈርጥ አድርጎ የሚያሳይ፣ የሞራል ልቅነት ሲያይ ብራቮ! እያለ የሚያጨበጭብ፣ ከማኅበረሰብ ጤና ይልቅ ፈንጠዝያን

የሚያከብር፣ አዳዲስ የርኩሰት አራዊት የሚያራባ የክፋት ሸቀጥ ነው። ይህ ብዙ መደብሮች ቢኖሩትም የጅምላ መሸጫው ሚዲያ የሚባለው የሕዝብ መገናኛ ነው። ፊልሞቻችን፣ ሙዚቃው፣ መጻሕፍቱ፣ ሬድዮው፣ ቴሌቪገቦኑ፣ መጽሔቱ በየጓዳው፣ በየአዳራሹ፣ በሚዳው ሁሉ የሚዘራው ንጽሕና አምካኝ ዘር፣ ከልካይና አስተዋይ በሌለበት ሁኔታ እያጐነቆለ ነው።

ዓለሙ ሁሉ በእብደት ሲሮጥ የቀደመን ስለመሰለን እነሱ በሶምሶማ የሚሄዱበትን ሁሉ እኛ ኢትዮጵያውያን በሽምጥ ጋልበን ደረስንበት፤ በአንዳንድ በኩል እንዳንቀድማቸውም ያሰጋል። መለኪያ የለሽነት ልክ ሆነ። ቀደም ባሉት ዓመታት ይህ ነጭ፣ ይህ ጥቁር ማለት ይቻል ነበር። «ኧረ ነውር ነው!» ሲባል አዎ ነውር ነው ይባል ነበረ፤ ወይም ቢያንስ መሬት መሬት እያየን ዐጉር እያሻሸን እንለማመጥ ነበረ። ክፋት ዛሬ የተፈጠረ ባይሆንም በስሙ ተጠርቶ ክፉ ይባል ነበር፤ ተጻራሪውም ሠናይ፣ ዕጹብ፣ ግሩም፣ ድንቅ፣ ማለፊያ፣ በጎ፣ መልካም ይባል ነበረ። አሁን ግን የሥነ ምግባር ዛፍ ከነሥሩ ተመንግሎ ባየር ላይ ሰፈፈ። እኩይና ሠናይ የሚዳኙበት ችሎት ተዘጋ።

«እንዴ ምን ጉድ ነው የምታወራው ምን ዓይነት የመዓት ነቢይ መጣብን» የሚል ሰው ይኖር ይሆን? «እንዴ የስንት ታቦት የስንት ደብር አገር፣ የስንት መስጂድ የስንት ሼህ አገር፣ የስንት ጸሎት ቤት የስንት ምዕመናን አገር።» ይሁና! ይህ ሁሉ ሆኖም ሙት ሃይማኖታዊነት እንደ ሰደድ ለተዛመተው የሥነምግባር ዝቅጠት፣ እንደ ካንሰር ለሚራባው ሚዛን የለሽ ባህርይ በቂ መልስ ሊሰጥ አልቻለም። ይልቁን ወርቀዘቦ የግብዝነት ካባ ስለደረበለት ውስጥ ውስጡን እየበተበተ እንዲበላን ጉልበት ሰጠው።

ቤተቅዳሴ ተጣበበ እንጂ ቅዱስ ልቡና አልተገኘም፤ ማተባችን ወፈረ እንጂ ከቆዳችን አልዘለቀም፣ ቤተጸሎት የወንበዴዎች ዋሻ ሲሆን ልበ ቅኖች በፍርሃት ተሸሸጉ፣ ጮሌዎች መንበሩን ተቆጣጠሩ። እውነት በመንገድ

ጥራጊ አሰስገሰስ ታፈነች፣ ተዳፈነች። ቤተክርስቲያን ለዘመናዊነት እና ለድኅረ ዘመናዊነት የወርቅ ጥጃ ማሠሪያ ጉትቻ አዋጣች፣ ተሠረቶ ሲመጣላትም እልል አለች።

እኛ ኢትዮጵያውያን ታላቅ ሕዝብና አገር ያለን ሰዎች ነን እያልን ስናውጅ ኖረናልና መሆን አለመሆናችንን ረጋ ብለን እንጠይቅ። ታላቅነት በምን መስፈርት?

ኢትዮጵያ የጥንታዊ ሥልጣኔ ምድር

ኢትዮጵያ የአልደፈርባቦች፣ የጀግኖች አገር

ኢትዮጵያ ባህሏን ጠብቃ የቆየች የበለጸገ ባህል ያለው ሕዝብ አገር

ኢትዮጵያ ድብልቅ ማንነቷን በአንድ በብሔራዊ ጥላ ሥር ይዛ

ለመዝለቅ የቻለች ጎበረብሔራት ምድር የራሷ የጽሕፈት ባህል፣

የሚያኮራ ቅርስ ያላት አገር

በዚህ በዚህ ሁሉ ሲለካ እውነትም ይህ ሕዝብና አገር ታላቅ ነው። በማንነታችን ደስ ልንሰኝ፣ ሳንሸማቀቅ ኢትዮጵያዊ ነኝ ልንል ይገባል እላለሁ። ይሁን እንጂ ሌላም ገጽታ አለን።

ከሥራ ይልቅ ለወሬ የተጋን

መቆራቈስን እንደ ወግ የያዝን

ለበጎ ለውጥ አፈፍ ብለን የማንነሳ

በሥልጣኔ ስም ለሚመጣ መርዝ ማጥለያ የሌለን

ቤት ውስጥ ካለው ወርቅ ይልቅ ማዶ ያለው ብረት የሚስበን

መሆናችንን ስናስበው እጅግም ታላቅነት አይሰማንም።

አንድ ሌላ ሕዝብ ነበረ፣ እስራኤል የሚባል። ምሳሌነቱ ስለሚጠቅመን ለታላቅነቱ የተነገረለትን መለኪያ እስኪ አናትኩርበት።

ተናጋሪው የሕዝብ መሪ የነበረው ሙሴ ነው፣ መቸቱ እስራኤል ከግብፅ ባርነት ነፃ ወጥተው ወደ ተስፋይቱ አገር ሲጓዙ ሳለ በሙሴ ዘመን ማብቂያ ላይ ነው።

«ገብታችሁ በምትወርሷት ምድር፣ እንድትፈጽሟቸው እግዚአብሔር አምላኬ ባዘዘኝ መሠረት ሥርዐትንና ሕግን አስተምራአችኋለሁ። በጥንቃቄ ጠብቋቸው፤ ሰለ እነዚህ ሥርዐቶች ሁሉ ለሚሰሙና፣ በእውነት ይህ ታላቅ ሕዝብ የቱን ያህል ጥበበኛና አስተዋይ ነው ለሚሉ ሕዝቦች ይህ ጥበባችሁንና ማስተዋላችሁን ይገልጣልና። በምንጠራው ጊዜ ሁሉ አምላካችን እግዚአብሔር ቅርብ እንደ ሆነ ለማልከቱ የሚቀርቡት ሌላ ታላቅ ሕዝብ ማነው? ዛሬ እኔ በፊታችሁ እንዳስቀመጥሁት ሕግ ያለ፣ ጽድቅ የሆነ ሥርዐትና ሕግ ያሉት ሌላ ታላቅ ሕዝብስ ማነው? (ዘዳ 4:5-8)

ለሕዝብ ታላቅነት ሁለት መለኪያዎች ጐልተው ይታያሉ።

ሕግ እግዚአብሔር

ህልዎተ እግዚአብሔር

ወይም በሌላ አነጋገር

ሕዝብ የሚተዳደርበት የጽድቅ ሥርዐትና

ከሕዝብ ጋር ግንኙነት የሚያደርግ ሕያው አምላክ

እንግዲያው ታላቅ ሕዝብ ሙት ሃይማኖታዊነት ይዞ የባህል ገባር ሆኖ ደመነፍሱን የሚንቀሳቀስ ሳይሆን ዛሬ ሲጠሩት ከሚሰማና ከሚናገር ሕያው አምላክ ጋር ትኩስ (ፍሬሽ) ግንኙነት ያለው ሕዝብ ነው።

ታላቅ ሕዝብ ማለት መለኪያ የለሽ፣ ሥርዐት የለሽ፣ ከየጐዳናው የሚነፍሰው ነፋስ ሁሉ የሚያንገዋልለው ካስማ አልባ ድንኳን ሳይሆን - ለፈሪሃ እግዚአብሔርና ለሕዝባዊ ልማት የሚያሠለጥነው ርቱዕ ጽድቅ የሆነ ሥርዐት ያለው ሕዝብ ነው። የዚህ ሥርዐት ምንጩ ቃለ እግዚአብሔር ነው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው የእውነትና የብርሃን ህብት

ነው።

ቤተ ክርስቲያን የዚህ የጽድቅ ሥርዐት ዐዋጅ መደብ ናት፣ የጽድቅ ሥርዐቱ ዐዋጅ ነጋሪትም ናት (ከነሰሙ ነጋሪት) «የእርሱን በጐነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ» ተብለናልና ድምጿን ከፍ አድርጋ ከዳር እዳር የሚያስተጋባ የጽድቅ አዋጅ ማወጅ ጥሪዋ ነው።

ይህ የጽድቅ ሥርዐት የሚፈተሽባት መደብ፣ የሕያው አምላክ ህልዎት የሚከሰትባት መቅደስም ናት። እርሷ ዘንድ የታየ፣ የተደመጠ፣ የሠራ፣ ባገር ሁሉ እንዲናኝ የእውነትና የበጎ ምግባር ሠርቶ ማሳያ ሞዴል ናት። ለአገርና ለሕዝብ ታላቅነት የምታበረክተው አስተዋጽኦ አላት. ኢየሱስ ጌታችን ሁለት ደግቅ ስዕሎችን እፊታችን ዘረጋልን።

«እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤

እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።»

ይህን ማንነት ዘነጋን ማለት የራስ በራስ ውድመት ጨዋታ ውስጥ ገባን ማለት ነው። ወደ ውጭ ተጥሎ መረገጥ።

ባጭር ቃል ጌታችን እየነገረን ያለው በጎበረተሰቡ መካከል ግቡ፣ ግቡ፣ ግቡ፣ ግቡ ዳር አትቁሙ፣ በትዝብት አትመልከቱ እያለን ነው። ገብታችሁ ያለ ምልክት ያለ ዓላማ ጥፋ ግን አላለንም - ገብታችሁ አስሙ (መልካም ጨው እንደሚያሰማ ሁሉ) ለውጥ አምጡ፣ ስትገቡ ማንነታችሁን አትሽጡ፤ ነፍስ አድን ማንነታችሁን ይዛችሁ፣ ጠብቃችሁ፣ አዳብራችሁ ግቡና አድኑ፤ የሕዝቡን ነፍስ ከሚበጫጭቁ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት አትርፉ ነው የሚለን።

ዓለሙ ጣም ያጣ፣ ውሃ ውሃ የሚል፣ የደነዘ የፈዘዘ ነው፤ ይህ ዓለም ግስም ያለ ጨለማ የወረሰው ሕዝቡም በታላቅ ዕውርነት የሚርመሰመስ ነው አታዝኑለትምን? አትታደጉምን? የእኔን ብርሃን አትፈነጥቁምን? የእኔን የሕይወት ጣዕም አታስተዋውቁምን? መዓዛዬንስ አትናኙምን? እያለን ክርስቶስ መድኃኒታችን ይጠይቀናል።

የባቢሎን እብደት የሰማይ አምላክ ፈውስ

«ሕልም ተርጓሚ አስማተኛ መተተኛ ከለዳዊ.....በቃኝ::» ባዮሎጂስት ሳይኮሎጂስት አግሮኖሚስት አስተሮኖመር..... በቃኝ» በተንጣለለው የባቢሎን ዩኒቨርስቲ የዕድሜያቸውን እኩሌታ የፈጁ መጻሕፍት ያሹ፣ ዓይን ያሹ አእምሮአቸውን የፈተሉ የገመዱ ያሾሩ እነዚህ ሁሉ አንድ ጥያቄ መመለስ ካልቻሉ ለምን ይኖራሉ?

አስቸኳይ ትእዛዝ ---- ያለ ርኀራሄ በስይፍ ይቆረጡ

ቤቶቻቸው የጉድፍ መጣያ ይደረጉ::

የትዕይንቱ ቦታ ----- የባቢሎን ቤተ መንግሥት

ጊዜው ----- 590 ዓመተዓለም ግድም

ተናጋሪው ----- ንጉሥ ናቡከደናጸር

የጽሑፍ ዓይነት ---- እውነተኛ ታሪክ

(ትንቢተ ዳንኤል .2)

ለከለዳውያኑ ጠቢባን የቀረበላቸው ጥያቄ ከተለመደው ለየት ያለ ነበር:: እንደ ቀድሞው ቢሆን ንጉሡን ያወከውን ነገር በእውቀትም ሆነ በብልጠት ሊመልሱት በቻሉ::

ለወትሮው ንጉሡ ሕልም አልሞ ቢሆን ሕልሙን ይነግራል:: ፍቺው አልገባኝም አስረዱኝ ይላል:: ዛሬ ግን የሚላቸው «ሕልም አልሜያለሁ ነገሩ ግን ከእኔ ዘንድ ርቆአል:: ሕልሙንም ፍችውንም አስታውቁኝ» ነው:: ሊቃነ ጠበብቱ መላልሰው የሚጠይቁት «ንጉሥ ሆይ ሕልሙን ንገረንና ፍችውን እኛ እናምጣ:: ችግርህን ይሄ ነው በል መፍትሔው እነሆ እንበልህ» እያሉ ነው::

የንጉሡ ቁጣ ጉሮሮውን ቢተናነቀውም እነዚህ ምስኪን ሊቃውንት ምን ሊያደርጉለት ይችላሉ? እንዲያውም ርግጡን ሲያስረዱት «የምትጠይቀው የተገረ ነገር ነው..... አማልክት ይፈቱት እንደሆነ እንጂ የንጉሡን ነገር

ያሳይ ዘንድ የሚችል ሰው በምድር ላይ የለም» አሉት:: በዚህ ጊዜ ነው ንጉሡ ከጤና አእምሮ ተርታ የወጣው፤ ያዙልኝ ግደሉልኝ አጥፉልኝ ያሰኘው::

ዓለም በአሁኑ ወቅት ሁኔታዋ እንደ ናቡከደነፆር ነው:: መፍትሔ ማጣት ብቻ ሳይሆን ጥያቄዋንም በውሉ አልለየችም:: የትኛው ነው የዓለም አሳሳቢ ችግር? የችግሩስ መነሻ ምንድን ነው? ለሥቃይዋ ምክንያቱ ምንድን ነው? በሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ላይ በአሁኑ ጊዜ በጠቢባኑ ዘንድ ስምምነት የለም::

የችግሯ ዝርዝር ክር ባይጨበጥላትም ዓለም መቸገሯ ጤና ማጣቷ ግልጽ ነው:: ምላሷን አፈር አፈር ብሏታል:: ዓይኗም ተስለምልሞአል:: መድኃኒቷን መፍትሔዋን÷ በጥድፊያ÷ በቃበዙ÷ በሚያሳዝን ዓይን ትጠብቃለች::

የራሷ መተተኞች ጠቢባን ለእንደዚህ ዓይነቱ ዙሪያ ድፍን እንቆቅልሽ መልስ የላቸውም:: ይህ ከፊደል በላይ ነው ከክምር መጻሕፍት ከላቦራቷር ፍተሻ በላይ ነው:: ትምህርትንና ሥልጣኔን ብወድም ይህን መናገር አለብኝ:: ዓለም መፍትሔ ስትጠይቅ እንደ እብድ ሆናለች:: ንግግሯ ሁሉ «ወይ መልሱልኝ አለዚያ ጥፉልኝ» ነው:: «አዋቂዎቿ» በእሽሽታ በጥልፍልፍ ሊያዘገይዋት የሚችሉ አይመስልም:: ሰው ለብርቱ ጥያቄው መልስ ሲያጣ የሕይወት ሚዛኑን ይስታል፤ ሥርዓት መጣስ ጌጥ ይሆናል፤ ተስፋ ማጣት የዕለት ሲሳይ ይሆናል፤ ጨለማ ይሰፍናል:: በዚህች ፕላኔት ላይ ከዚህ ጎልቶ የሚታይ ነገር አለ? በየጎረቤታችን በየቤታችን የምናየው ይህንኑ አይደል?

የ21 ዓመቱ ወጣት ሕይወትን ሊጀምር ሲደርስ ራሱን በገመድ ማንጠልጠሉ ምን ማለቱ ነው? ትዳራቸውን በታላቅ ጭብጨባ ጀምረው የጭብጨባው ማሚቶ ሳይበርድ የሚለያዩት ምን ማለታቸው ነው? ልብሱ ሳጥኑን ሞልቶት እያለ በነፍስ ብርድ የሚንቀጠቀጠው ምን

ማለቱ ነው? የሚበሉት ስለተረፋቸው የት እንደሚያኖሩት ሲጨነቁ ከቁራሽ እጦት የተነሳ በየሜዳው የሚፈነገለው ሰው ጉዳይ ምን ማለት ነው? የምንኖርባት ዓለም በተስፋ ማጣት ጨለማ ውስጥ ወድቃለች ማለት ነው። መፍትሔውን የሚያሳያት ከአዘቅቱ የሚጎትታት አጥታለች ማለት ነው። ችግራችንን እንድናውቅ ልዑል እግዚአብሔር ይርዳን።

የነዳንኤል ምላሽ

ምርኮ ከአገራቸው ያፈናቀላቸው እግራቸው ባቢሎን ቢሆንም ነፍሳቸው ኢየሩሳሌም የታሰረ ዳንኤልና ባልንጀሮቹ ከከለዳውያን ዩኒቨርስቲ ከተመረቁት መካከል ነበሩ። ጠቢባኑ መገደል ሲጀምሩ እነርሱም ሊታለፉ እንደማይችሉ ገብቷቸዋል። የናቡከነፆርን እብደት÷ የጠቢባኑን ሞት÷ የሕዝቡን መታመስ ዳር ቆመው ሊያስተዛዝኑ ወይም በትርጓቱ እየተገረሙ ሊጠቃቀሱ አልተፈቀደላቸውም። ጉዳዩ የሞት የሽረት ጥያቄ ነው። ስለዚህ ዳንኤል ጥቂት ጊዜ ለመነ። የመጸለያ÷ የማሰቢያ÷ የመማለጃ የማሳዘኛ። የንጉሡን አስቸኳይ የሞት ትእዛዝ በፈሊጥ በማስተዋል አለዘበ። በተገኘው ትንሽ ፋታ ጓደኞቹን አስተባበረ ምክንያቱም የእርሱ ዕጣ የእነርሱም ነው። እነዚህ የጭንቅ ዘመን ባልንጀሮችና የሰማይ አምላክ አማኞች ሁለት ነገር ለመኑ።

ልዑሉን እግዚአብሔርን ከማያምኑ፣ ታዳጊ ከሌላቸው ከባቢሎን ጠቢባን ጋር እንዳይሞቱ ምሕረት ከሰማይ እንዲሰጣቸው/የምሥጢር መቋጠር ፍርድ ነበረና።/ አሁን ባለው የዓለም ጭንቀት ገለል ያልን ተመልካቾች አይደለንም። ልንሆንም አይገባም። የእኛ ሕይወት ከሕዝብ ሕይወት ጋር ተቋጥሯል ተነካክተናል። መልስ ግን በሜዳ አይገኝም በመጨነቅም አይመጣም። ለክርስቲያን ራእይና ምሥጢር በየጓዳው ይገለጽለታል፤ ከአምላኩ ጋር በሚደረገው መተያየት ይገለጽለታል፤ በፈሪሃ እግዚአብሔር አካሄድ ይገለጽለታል። የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ተግቶ የሰማይን ድምፅ ማጣራት ያስፈልጋል። አረፍ ብለን ካላሰላሰልን ካልተማጠንን

እንኳን ለዓለም ለራሳችንም የዕለት ውጣ ውረድ መልስ የለንም። በዚህ ታላቅ አገልግሎት የሚያምኑትን ሁሉ የማስተባበር ኃላፊነት አለብን። «እንዳንጠፋ ለምኑ» ነው የእግዚአብሔር ልጆች ጥሪ።

«አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም፣ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ቁጣው የዘገየ ምሕረቱም የበዛ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ።»

ኢዮ 2÷12-13

ራእዩን ማስታወቅ

ውስብስቡ ቋጠሮ ተፈታ። «ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነው» የሰማይ አምላክ ምስጢሩን ገለጸ። ዳንኤል ከእግዚአብሔር ለተገኘው መፍትሔ ታላቅ አክብሮት ነበረው። ይህን ዙሪያ - ብርሃን አምላክ በታላቅ ውዳሴ ያመልከዋል ይገዛለታል። እንዲህ እያለ።

«የጠለቀውንና የተሰወረውን ይገልጣል፤ በጨለማ ያለውን ያውቃል ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው..... የለመንህን.....አስታውቀኸኛልና እገዛልሃለሁ አመሰግንህማለሁ።»

ዳንኤል ወደተቸገረው ንጉሥ ገብቶ ራእዩን ሲያስታውቅ ሁለት ተቃራኒ መሰል ባሕርያት አጣጥሞና አዋህዶ ነበር። ታላቅ ድፍረትና እውነተኛ ትህትና።

ድፍረቱ ምንድን ነው ቢባል ከአንድ ጠቢብ በስተቀር ሌላ አላውቅም ከአንድ መድኃኒት በስተቀር ሌላ የለም ከአንድ ብርሃን በስተቀር ሌላ ጭላንጭል እንኳ የለም ማለቱ ነው።

«ጠቢባን አስማተኞች ሕልም ተርጓሚዎች ቃላተኞች.... አይችሉም» የሚችል ግን አለ «ምስጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ» እንዴት ዓይነት ኢምሑራዊ አነጋገር ነው። መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ይወስዱ የለምን? የለም፣ የሰማዩ መንገድ ግን አንድ ነው። ጠባብነት

ቢባል ይባል ድፍረት ቢባል ተገቢ ድፍረት ነው።

ደፋሩ ዳንኤል በአምላኩ ተጓደደ፣ በጌታው ተመካ እንጂ ስለራሱስ የሚያውቀው ያው ሌላ ሥጋ ለባሽ ብቻ መሆኑን ነው።

«ይህ ምስጢር ለኔ መታወቁ..... በዚህ ዓለም ካሉ ሰዎች ይልቅ በጥበብ ስለበለጥሁ አይደለም።» ዳንኤል የሰማይ ብርሃን ቢያጥለቀልቀውም መሬታዊነቱን አልረሳም። በአምላኩም በተጨነቀውም ንጉሥ ፊት ትሑት ነበር።

ቅዱሳን አሁን በግልጽ ቋንቋ በርቱዕ አንደበት በመንፈስ ቅዱስም ድፍረት እውነቱን ሊገልጡ ያስፈልጋል። ነገር ግን ይህ ድፍረት የርግብን ትሕትናና የዋሕነት ሊጎናጸፍ ይገባዋል። የትኛውም የጥበብ መሥመር የዓለምን መሠረታዊ መከራ ሊያሳይ አይችልም። ከዚህም የኃጢአት መከራ ለማውጣት ከቶ አይሆንለትም። አምላካችን ብቻውን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለጥያቄያችን መልስ ሆነ። እግዚአብሔር ይመስገን።

ያ የጌታችን የዋህ ተከታይ ጴጥሮስ ሲመክረን እንስማ፡

«በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ። ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን» 1ጴጥ 3:15

ዓላማ የለሽነት - ዓላማ ያለሽነት

ጧት ተነሥቼ ፊቴን መታጠብ፣ ቤት ያፈራውን ወደጉረሮዬ ወርውሬ ወደ ጐዳናው መፈትለክ፣ ስምሪቱ ሲያበቃ በጀንበር መቆልቆያ ወደ ቤት ማዝገም የሠርክ አዙሪት ሕይወት ሊሆን ይችላል። ይኸው አዙሪት መዓልት ሌሊት እያፈራረቀ ዕድሜያችንን ሲገዘግዝ እያየን ምን እንላለን? ትርጥም አልባ አዙሪት፣ ዓላማ ቢስ እንከርት።

ዓላማ ቢስነት መገለጫው ብዙ ነው። እንደ ጐርፍ እየገሠገሠ የሚጠፋውን ጊዜ ግዴለሽ ሆኖ ማሳለፍ አንዱ መታያው ነው። ሁሉን ነገር እንዳረሰ ያለዕቅድ መሥራት ሌላው ገጽታው ነው። ከየጐዳናው ለሚጐትተን ደፋር ሁሉ እሺ ማለት፣ የተገቢ እምቢታን ክቡርነት መርሳት - በዋል ፈሰስነት፣ የዚሁ የዓላማ እጦት መልክ ነው። ዓላማ ሳይኖረን ሲቀር ዕቃነት ይሰማናል፣ ያለፈ ያገደመ ነፋስ ከየጥጋጥጉ ጋር ያላጋናል። የቆምንበት ቦታ ሁሉ ተገፍተን የደረስንበት ይሆናል፣ ባለ አቅጣጫ ሂያጆች አንሆንም።

ዓላማ ማጣታችንን ለማረጋገጥ ብዙ ምርምር አይጠይቅም። የየዕለቱ ኑሮ የታከተን ከሆነ፣ በግራም በቀኝም መሄድ ለውጥ የለውም የምንል ከሆነ፣ የተጀመረ ነገር ሲቋረጥ ደንታ የማይሰጠን ከሆነ፣ ከዛሬ ባሻገር ሌላ ቀን የማይታየን ከሆነ በነሲብ እንደምንኖር በቂ ምስክር አግኝተናል።

ለዓላማ ቢስነት የሚሰጡ ምክንያቶች አሉ.-

- እኔ አቀድሁ አላቀድሁ ተፈጻሚነት ከሌለው ምን ዋጋ አለው?
- ዓላማ ይኑረኝ ብዬ ዐሥር ጊዜ ውጥን ባወጣ አቅሙ ከሌለኝ ምን ፋይዳ አለው?
- ለዚህ አጭር እድሜ ደሞ ዓላማ ኖረ አልኖረ እንጀራ በልቶ ከማደር የበለጠ ማሰብ ምን ይጠቅማል?

- ከሰማይ ባለቤቱ የቆረጠው ነገር መፈጸሙ ላይቀር ወዲያ ወዲህ ማለት ከንቱ መባከን ነው።

ባለ ዓላማ ሰው መሆን ዓላማው ግቡን ሲመታ ከሚያስገኘው ጥቅምና ርካታ ሌላ ከፍተኛ ዋጋ አለው። በዓላማ መኖር ከዓላማው ፍጻሜ ባላነሰ መንገድ (ምናልባትም በበለጠ ሁኔታ) ሰብአዊነታችንን የሚገነባ ነገል ነው። "እዚህ ለመድረስ እሠራለሁ፣ ይህን ለመጨበጥ ችሎታዬን ሁሉ በአንድ አቅጣጫ አሠማራለሁ" የሚል ቁርጠኛ ሰው መንፈሱ እጅግ የበለጸገ ደልዳላ ሰው ነው።

የዓላማ ሰውነት ከሚለግሠን ጸጋዎች አንዳንዶቹን እነሆ፡-

➢ የሕይወትን አዎንታዊ አመለካከት ማዳበር

አንድ ዳር ለመድረስ ስፍጨረጨር ሕይወትን ታላቅ ዋጋ እሰጣታለሁ፣ ካለመኖር መኖር ይሻላል እላለሁ፣ ራሴን ለአልባሌ ነገር አላጋልጥም፣ ውጥኔ እስኪሟላ ድረስ ራሴንም ዙሪያዬንም እያከበርሁ እንቀሳቀሳለሁ።

➢ በትጋትና በዲሲፕሊን መኖር

የሚለካ ግብ፣ የሚደረስበት ርቀት ስናስብ ከፍተኛ የትጋት ልቡና ያድርብናል፣ ራሳችንን ለመግዛት፣ ነገን በማሰብ ዛሬን ለመታገሥ ትርጥም እናገኛለን።

➢ ሰላማዊና የሰከነ አእምሮ ማበጀት

ማረፊያ ማጣትና፣ መቅበዝበዝ ከዓላማ ቢስነት ጋር ሊያያዝ ይችላል። ሰው አእምሮው በሁነኛ ዓላማ ከተያዘ መስመር ያገኛል፣ ይሰክናል።

➢ የተስፋ ብርሃን ማየት

ነገ ከሌለ ተስፋ የለም። ዛሬ ላይ ሆነን ብሩህ ነገዎችን የምናየው ዓላማ ይዘን ስንንቀሳቀስ ነው።

እነዚህ ሁሉ በገንዘብ ሊገዙ የማይችሉ ዕፁብ ስጦታዎች ናቸው። ሕይወቱ በክቡር ዓላማ የሚመራ ሰው የሚጐናጸፋቸው ሽልማቶች ናቸው።

የአርባ ቀን እድል ቢኖርም ባይኖርም ዓላማ ከማበጀት የሚከለክለን ነገር የለም። አቅመ ቢስነት ሰበብ እንዳይሆን እስቲ ያቅማችንን እናድርግና እንሙት። ደግሞስ በጎ ዓላማ ያለውን ሰው የበጎ ሁሉ ምንጭ የሆነው ባለዓላማ ፈጣሪ አይረዳውም? ማጎበረ ሰበስ በቅን መንገድ በጎ የሚያስብ ሲያይ አይተባበርምን? ቢያንስ ቢያንስ አክብሮት አይሰጠውም?

ሕይወታችንን በዘፈቀደ፣ ባወጣ ያውጣው አንወርውረው፣ የረባ ዓላማ እንፈልግለት፣ አቅጣጫም እናስይዘው።

የአንድ ትውልድ ሙሾ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ይህችን ትውልድ በምን እመስላታለሁ?» ማለቱ ትልቅ የትውልድ ትንተና ሥራ ከተከታዮቹ እንደ ሚጠበቅ ያመለክታል። እርሱ የነበረበት ትውልድ በዘፈንም በልቅሶም የማይጨበጥ ሙልሞልሟ ትውልድ ነበረ። ቁርበት ለብሶ፣ አንበጣ እየበላ የኖረውን ባህታዊ ሰባኪ በሰይፍ ያስገደለ፣ ጨርቅ ለብሶ እንጀራ እየበላ ያስተማረውን ሰው ወዳጅ ሰባኪ በእንጨት ላይ የሰቀለ መናጢ ትውልድ ነበረ። ሆኖም ምንም የማያግደው ልዑል እግዚአብሔር በዚያው ትውልድ መካከል ለትውልዶች ሁሉ የሚበጅ አስገራሚ ሥራውን ሠራ።

ወዳጆቼ፣ የእኛ ትውልድ ምን ይመስላል? እኛ ምን እንመስላለን? ተገቢ ጥያቄ ነው። ይህን የትውልድ መልክ ትንተና በአንዲት መጣጥፍ እሠራለሁ ብዬ እኔም አልሞኝ። ሰውም አላሞኝ። ነገር ግን ዓይናችንን በጤና የከፈትን እንደሆነ ፈጥጠው የምናያቸውን ጉልሃን አካሄዶች መናገር ክርስቲያናዊም ሰዋዊም ግዴታችን ይመስለኛል።

በዚህ ሰፊ-ጠባብ ዓለም ሁሉ ነገር የተንሳካ ቢሆንም እንኳ አቅማችንን የሚመጥን ትግል ለማድረግ እንዲቻል ትኩረታችንን በምናውቀው ሕዝብ ላይና ከዚያም በጠበበ ሁኔታ ኃላፊነቱ ከባድ በሆነው ክርስቲያን ጎብረተሰብ ላይ ማድረግ ግዴታ ነው።

የአበሻ ሕዝብ መታመስ ከጀመረ ቆይቷል የቅርቡ ብቻ ቢቆጠር ሩብ ምዕተ ዓመታት ያልፋሉ። እነዚህ ዓመታት አልፎ አልፎ ብቅ ካሉ የብርሃን ጮራዎች በስተቀር በአብዛኛው የመደናገር፣ የሁካታ፣ የግርግር፣ የጥላቻ፣ የበቀል፣ የድብብቆሽ፣ የተንኮል፣ የዝርፊያ፣ የጭከና፣ የራብ፣ የርዛት፣ የሕመም፣ የሞት፣ ፈጣን የኋሊት ግሥግሤና የቀቢጸ-ተስፋ ዓመታት ነበሩ።

ችግሮቻችን በከፊል የተፈጥሮ ሂደት መዛባት፣ የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት አድሎአዊነትና ቴክኖሎጂያዊ ኋላቀርነት ቢሆኑም ፊታውራሪያቸው የሰው ልጅ የልብ ጥመት ነው። የመሪም የተመሪም። የቀብር ጉድጓችን ፈጣን ቆፋሪዎች እኛው ነን።

«እነዚህ ዓመታት ያፈሩት የሰው ዓይነት ምን ይመስላል? የተባለ እንደሆነ ጉራጌዎች «አውከሬ» ብለው የሚጠሩት፣ ወፎች ማሽላውን በልተው እንዳይጨርሱት ገበሬ በቡትቶና በሣር ባርኔጣ አውተፍትፎ የሠራው «ቁራ - አስፈሬ» አሻንጉሊት ነው ብንል ግነቱ ከመጠን አያልፍም።

ይህ የማሽላ ጠባቂ አሻንጉሊት ራሱ ምንድን ነው? ቢባል ሕያው ሰው ለመምሰል የሚሞክር፣ በተለይ ከሩቅ ሲያዩት የሚያሳስት ሲቀርቡት ግን ሰው ሠራሽ ዕቃነቱ ጎልቶ የሚታወቅ ተዋናይ ነው። ትጉህ ሠራተኛ መስሎ በእጁ በትር ቢጤ ይዞ በንቃት የተሰለፈ ዘበኛ ወይም የሚያነጣጥር ፡ ወታደር ይምሰል እንጂ ምንም የተጨበጠ ሥራ አይሠራም። በልምጩ ዘንግ ርዝመት ያስፈራራ እንጂ «ቢከፍቱት ተልባ» ነው።

ከሁሉ ከሁሉ የከፋው ነገር ይህ አሻንጉሊት ነፍስ የሚባል የለውም። ማንነቱ ገበሬው የፈጠረለት የውሸት መስፈራርቾ ማንነት ነው እንጂ «እኔ» ብሎ አስተንትኖ የሚያውቀው፣ የሚያሳውቀው፣ በዚያውም መሠረት የሚኖርበት ማንነት አይደለም። ትውልዱ ማንነቱ የተጥበረበረበት ድንግርግር ትውልድ ነው።

ይህ ትውልድ የዓላማ ጭካኔ ያጣ ትውልድ ነው። ለምን እንደቆመ አስተንትኖ ስለማያውቅ በነፍሱ አይወራረድም። ለሞት ለሽረት ራሱን አያጋልጥም ሲያባብልና ሲባበል መኖር ይወዳል ኃይማኖቱ ሽቀጥ ሆኗል። ክርስትና ገበያ እንዲያገኝ ጌጥና ድምቀት፣ ሆይ ሆይታና ጩኸት የሚያስፈልገው መስሏል። ክርስቲያን መሆን የሞት የሕይወት ውሳኔ መሆኑ ቀርቶ ከመንገድ አላፊና ከጎረቤት የሚከረጅ

የመጨረሻው ፍሽን ሆኗል። ስለዚህ ዘመናውያን ስልጡኖችና ንቁዎች እንዲሻሙት ብልጭልጭ ማስታወቂያ አበዛን። ይህም ደቀመዛሙርት ሳይሆን «ቲፎዞዎች» አፈራልን። «የኢየሱስ ክርስቶስ ክለብ» ደጋፊ ነው። የሚያስፈልገውን የሜዳ ታክቲክ ሁሉ ተጠቅሞ ለክለቡ ማሸነፍ ይሟሟታል። ክለቡ ተስፋ የሌለው ከመሰለው ሌላ ለማቋቋም የሚከለክለው የለም። ኳስ ሜዳው ላይ ተገኝቶ መጫ.ጫ.ሁን ነው ሊያጣ የማይፈልገው። መስጠት፣ ዲሲፕሊን፣ መታገሥ፣ መጠበቅ፣ መገዛት የሚሉት ቃላት ያረጁና የማይጠቅሙ ወይም የሚያስፈሩ ናቸው። በምትካቸው ፍጥነት፣ የዛሬ ድል፣ በእጅ ማድረግ፣ መወርወር፣ ማንሳት፣ አቋራጭ መፈለግ፣ ታዋቂ መሆን ዝነኞች ሆኑ።

ትውልዱ ግላዊና ስግብግብ ሆነ። እግዚአብሔር የፍጥረተ - ዓለም ጠባቂነቱ ሳይሆን የግል ፍላጎት ሞይነቱ ጎላ። ከችግራችን ብዛት ይሁን ከዓይነ ልቡናችን ጥበት የማኅበረሰብን ደህንነት ከማሰብ ይልቅ የየግላችንን «እንጀራ ማብሰል» ዋና ጉዳያችን ሆነ። የምንወዳቸው የስብከት አርእስት «እንዴት በቂ እንጀራ ሊኖኝ እንደሚችል» «እንዴት ከዚያኛው ሰው እንደ ምንበልጥ» የሚነግሩንን ነው። "ተስማሚ" ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ አይታጡም።

ትውልዱ ዓላማ - ስስ ነው። ዘልቀው ቢመረምሩት ከጥቂት ወራት የበለጠ የኑሮና የሕይወት ሕልም የለውም። ሁሉም ነገር ከቁጥጥር ውጪ እንደሆነ ስለሚያስብ አራዝሞ ለማየት ፍላጎትም አቅምም አንሶታል። ስለዚህ የዕለት የዕለቱን እየጫረ ነው የሚተኛው። ደግሞ ዓላማ እኮ ረጅም እንዲሆን ትልቅ መሆን አለበት። እኛ በጣም ትልቅ ከሆነ አምላክ ጋር እንዳለን በድንግዝግዝ ቢታወቀንም ገና የትልቅነቱን ግዝፈት ለማየት አልተሰናዳንም። እርሱ እንደ አቅሙ ብርታት ብርቱ ነገር በእኛ እንደ ሚሠራ ለማሰብ አልቻልንም። «እግዚአብሔር ትልቅ ነው» ስንል እዚያ ማዶ ብቻውን ሆኖ ነው የሚታየን እንጂ ከእኛ ጋር፣ በእኛ ውስጥ ገብቶ፣

በእኛ ዘመን ትልቅ ነገር እንደሚያደርግ መቁጠር አልቻልንም። ስለዚህ ሕልማችን ቁጥቁጥ ናት።

ትውልዱ ተድላ አላዳጅ ነው። ርካታ የሚገኘው ስሜት - ሕዋሳታዊ ፍላጎቶቻችንን በማሟላት እንደሆነ ስለሚቆጥር ሞቶ ተሟሙቶ ነጥቆና ተባልቶ በድኩማን ራሳ ላይ ተረማምዶም ቢሆን ሥጋዊ ጩኸቱን ማስታገስ አለበት። ይህ ፈንጠዝያ ፍለጋ ሃብታም ድሃ የሚመርጥ ልባም ነገር አይደለም። ያንን የውስጥ ወትወታ ለማለዘብ ሁሉም እንደ አቅሙ ይሯሯጣል። ባይሳካለት እንኳ የምኞቱን ጣዖት እያባበለ ያስተኛዋል እንጂ በምንም ዓይነት ዓይኑን ሞልቶ ሊጋፈጠው አይደፍርም። ይህ ሰው ክርስቲያን የሆነ እንደሆነ ያንኑ አውሬ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቀለም ቀባብቶ በተለሳለሰ ጮሌ ቋንቋ ተጠቅሞ «ለጌታ ክብር እንዲውል ብዬ» ደግሞ «ለራስ ማሰብም እኮ መንፈሳዊ ነው» በሚሉ ሐረጎች እየደባበሰ ያነግሠዋል። ሌሎች እንዲበለጽጉ፣ ሌሎች ከሕመማቸው እንዲያርፉ መሥዋዕታዊ ኑሮ ለመኖር መወሰን ትልቅ ዳገት ሆኖብናል፤የኑሮ ዘዬአችን «ከራስ በላይ ነፋስ» ነው።

ትውልዱ በጥላቻ፣ በቂምና በበቀል ደድሯል። ጠብ ለመጫር ፈጣን ነው። የጫረውን ትንሽ እሳት አፋፍሞ ጫካውን ሁሉ የሚበላ ሰደድ ለማድረግ ጊዜ አይወስድበትም። ይህ ትውልድ እርስ በእርሱ የተፈራራ ጥላውን የማያምን ደንባራ ትውልድ ሆነ። ራሱ ከራሱ ጋር ስምረት ስለሌለው ከሌላው ጋር ተጣጥሞ መኖር ርቆታል። የርኅራኄ ሕዋሱ ደነዘ፤ ብዙ መራቀቅ የማይጠይቀው ሰብዓዊ ሐዘኔታ እንኳ ከሕሊናው ተሟጠጠ። እርቅና ሰላም የፈዝ ቃላት ሆኑበት። የባልንጀራውን ሕይወትና ኑሮ እንደ አሮጌ እራፊ ብስክስክ አድርጎ ሲጥል በእብድ ፍጥነትና ጉልበት ነው።

ትውልዱ ፈሪ ነው። ምንድነው የሚፈራው? ነገን አጥብቆ ይፈራል። ምክንያቱም በነጋ ቁጥር የውድቀትና የሞት ድምጽ እየበረታ

የሕይወትና የልምላሜ ተስፋ እየሸሸ ሲሄድ ስላየው ነው:: «ምን አበላለሁ?» ከሚለው ጀምሮ «ማንን ማመን ይቻላል?» እስከሚለው ድረስ በፍርሃት ጥያቄ ተወጥሯል:: የነካው ነገር ሁሉ ተስፈንጥሮ የሚገድለው ስለሚመስለው ምንም ነገር ሳይነካ «ጎመን በጤናውን መኖር መርጧል»:: ይህን የፈሪ መንገድ ይምረጥ እንጂ በሽሽቱ ብዛት የሚፈራውን ነገር አላመለጠም:: እንዲያውም ድንጉጥ እንግዳውን እንዳወቀ ውሻ ፍርሃቱ እየተከታተለ ከቀዬው እስኪርቅ ያሳድደዋል::

የትውልዱን አበሳ ላበዛ አልፈልግም:: ለመፍረድም አልተሾምሁም:: ማድረግ የሚገባንን ከመናገሬ በፊት ግን መመራመሪያ ጥያቄዎች ላስቀምጥ አንደኛው የቀደመው ትውልድ ለዚህ ትውልድ ትቶት የሄደው ወይም እየሄደ ያለው ምንድን ነው? የሚል ነው:: አንዱ ትልቅ በሽታችንና ሰቀቀናችን በእኛ ዘመን የሚታዩ «የእምነት አባቶች»፣ «የፍቅር አባቶች»፣ «የቅድስና አበጋዞች» ሲጨንቀን ሄደን ምክር የምንጠይቃቸው አስተዋዮች ከሩቅ ፈለጋቸውን ተከትለን ለመሮጥ የምንደፍርባቸው መሪዎች አሉን ወይ? የሚለው ነው:: ሽማግሌዎች እጃቸው ከግፍ ያልጸዳ ከሆነ፣ መሪዎችና የእውነት መምህራን የምንላቸው ከምስባኩ ሲወርዱ የሚኖሩት የተጭበረበረ ሕይወት ከሆነ ምን ዓይተን ነው የምንተርፈው? መሪዎቻችን የጠራውን ውሃ ለማደፍረስ የሚቸኩሉ ከሆነ እንዴት እኛ የሠላም አርበኞች እንሁን? ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን ጋር ለአፍታ ብንቀመጥ ውዳሴ ከንቱና አሉባልታ ያጠመቀው ወሬያቸው እየገፈተረ ካስወጣን እኛ እንዴት የቁም ነገር ሰዎች እንሁን? ሁለተኛው የመራመሪያ ጥያቄ - ይህ ትውልድ አሁን የሆነውን ነገር ተቀብሎት ወዶት የተቀመጠ ነው? ወይስ በላዩ ከተጫነበት ቀንበር ለመላቀቅ የሚታገል ተሸናፊ ነው? ጠጋ ብለን በስከነ ልቡና ካየነው ይህ ትውልድ ብርቱ ጥማት ያከለለው፣ ርኀራኄያችንንና የጥንቃቄ ሕክምናችንን የሚሻ ምስኪን ትውልድ ሆኖ እናገኘዋለን:: የእውነት

የዓላማ - የነጻነትና የፍቅር ጥማት አለበት:: መላ መንፈሱን አደራርቆ የቁም አስከሬን ያስመስለው ይኸው ለረኃም ጊዜ የተጠናወተው መሠረታዊ የነፍስ ምግብና ውሃ እጦት ነው:: እየተዋከብን በንዳና ላይ ስንጋፋ «ራስ ወዳድነቱ»ን እንኮንናለን እንጂ «እስቲ አረፍ ብለን እንጫወት» ብንለው ለፍቅርና ለእውነተኛ ቅርርቦሽ ነፍሱ ሲዋትት እናገኘዋለን:: ከሩቅ ሲጣደፍ ስናየው ወይም በንግግሩ ብዛት ሰው ለማሳመን ሲወተውት ስንሰማው ጥራዝ ነጠቅ ወሸካታ ይመስለናል እንጂ ነፍሱን ካዳመጥን ዙሪያውን ቃኝቶ ፍሬ እውነቱን ባለማግኘቱ ምክንያት ያገኘውን ገለባ ነገር ማናፈስ ልማድ የሆነበት የእውነት ራብተኛ እንደሆነ እንረዳለን:: ሊያምነውና መንፈሱን ሁሉ ሊማርከው የሚችል ነገር ካገኘ ራሱን ለመስጠት ወደኋላ የሚል አይደለም:: ፍርሃቱ የመነጨው በጨለማ በድንግዝግዝ ከፎቅ እንደሚወርድ ሰው በዳበሳ ከሚያደርገው አካሄዱ ነው::

መዳኛችን ምንድን ነው? ምን እናድርግ? ሁላችንን የሚመለከት ጥያቄ ነው:: በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለነው ሁላችን በአርምሞ ነገሩን ዓይተን መልስ ልንሰጥበት ይገባል:: ይሄ ትውልድ ካልዳነ የሚቀጥሉት ሦስትና አራት ትውልዶች ወዮላቸው ብል የመዓት ነቢይ አልሆንም:: የእግዚአብሔር ቃል በአንድ ትውልድ የተሠራው ሥራ የሚቀጥሉትን ተከታታይ ትውልዶች እንደሚነካ በቂ ምስክር አስቀምጧል::

«እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር መሐሪ ሞገስ ያለው.....እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ.... የአባቶችንም ኀጢአት እስከ ሦስትና አራት ትውልድም በልጅ ልጆች ላይ የሚያመጣ አምላክ ነው::» (ዘፀ 34:6-7)

ስለዚህ ትውልድ የሚገደን የጌታ ልጆች ልናደርግ የሚገባንና ልናስተላልፈው የሚያስፈልግ መልእክት አለ:: ይህን የምንናገር እኛ

እዚያ ማዶ በጠዳ ሰገነት ላይ ሆነን ሌሎች ትቢያው ላይ ተቀምጠው አንጋጠው እየሰሙን ሳይሆን ራሳችንም አለንበትና ለእኛው እንደምንናገር ሆነን ነው።

ይህ ትውልድ - ክርስቲያኑ ሕዝብ - እውነተኛና ክቡር የሆነውን ማንኑቱን እንዲገነዘብ ማገዝ ያሻል። መነሻና መድረሻ ያለው፣ ባለብዙ ማዕረግና ባለ ዘላለማዊ ዕጣ መሆኑን ማሳወቅ ይገባል። ምንም ኃጢአት ሊከሰው ባልተቻለው በክቡር የክርስቶስ ደም የተገዛ፣ በእምነት የሰማይና የምድር ፈጣሪ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ፣ እንከን፣ እድፈት ለማይገኝበት መንግሥት የታጨ ሰማያዊ ዜጋ እንደሆነ አጥብቆ ይረዳ። እንደ ድመት እየተፍረገረገ በየሰኒው ጥጋጥግ የወተት ሞላጭ እንዳይቀላውጥ ከማይነጥፍ የሕይወት ውሃ ምንጭ ጋር መያያዙን ይወቅ። አንገቱን ቀና አድርጎ መራመድ ያለበት ኪሱ በረብጣ ስለሞላ ሳይሆን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አሳዳሪው ስለሆነ መሆን አለበት።

ትውልዱ የነገሮችን ዋጋ ተመን መለዋወጥ ያስፈልገዋል። ዘመነኛው ነፋስ ያላግባብ እያራገበ ጣራ የሰቀለውን ገለባ በስሙ ጠርቶ ገለባ ማለት መቻል አለበት። የከበረውን ከተዋረደው እየለየ ለሁሉም ልክልኩን ማሰቀመጥ አንዱ ትልቁ ሥራው ነው።

ለምሳሌ፡«ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው»።

በጮሌነት ራስን ከማዳን ይልቅ በትሕትና መሥዋዕት መሆን የከበረ ነገር ነው።

በመሪነት መሰላል ወደላይ ከመሽቀዳደም ይልቅ በሎሌነት ምንጣፍ ላይ እግር ማጠብ ይበልጣል።

በስልጡን እሳታዊ ምላስ የነፍስን ራቁት ከመግለጥ ይልቅ ሰላማዊ ዝምታ ጤና ይሰጣል።

በአገልግሎት ብዛት እየባከኑ የማይጠቅም አቧራ ከማስነሳት ይልቅ የጌታ·ችንን ድምጽ ለማዳመጥ አደብ መግዛት ይጠቅማል።

ክርስቲያኑ ጎብረተሰብ ይህች ምድር የእግዚአብሔር ሥራት እንደሆነች ልብ ብሎ ከፍጥረተ - ዓለም ጠባቂ ጋር መተባበር እንዳለበት ይወቅ። ሣር ቅጠሉ-አፈር ጠጠሩ ሁሉ እኮ የእኛ ጌታ የእግዚአብሔር ነው። ስለ ዛፍ መጨፍጨፍ - ስለ ሐይቅ መበከል- ስለ ጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ዕጣ ፈንታ መጨነቅና ማልቀስ - የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግም መነሣሣት ንጹሕ ክርስትና ነው። «ለድሃ አደጉ ተምዋገት ሊታረዱ የተፈረደባቸውን ታደግ» የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው።

ትውልዱ ባለ ጥሪ መሆኑን በጥልቅ ይረዳ። «እናንተ ግን ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁ የእርሱን በጎነት/ድንቅ ሥራ እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ ናችሁ» ያለን ቅዱስ ጴጥሮስ በሚያስገርም የቃላት ስብስብነት የመኖራችንን ዓላማና ተልዕኮ ሲያስታውቀን ነው። ከተልዕኮ ውጪ መኖር እንዴት አሰቃቂ ዕዳ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንገድ እየተንጠራወዝን እንዳናዛጋ ብሎ ነው «ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ» ያለን። ትውልዱን የዚህ የዋህና ትሑት ሰው ቁርጠኛ ተከታይ ካደረግነው መንገዱን በወርቃማ ፍሬ ሞላነው።

የነጻነት ያለህ
(ለተማሪዎች)

ትምህርት ቤት የአሳብ ገበያ ነው። የአመለካከት የኑሮ ዘዴ፣ የፍልስፍና፣ የእምነት ክህደት፣ የክህደት እምነት። ከየስላቹ የሚፈልቁ እነዚሁ የአሳብ ሸቀጦች አደባባዩ ላይ ይናኸራሉ ይሳሳማሉ፤ ይጋጫሉ፣ ተጋጭተው ይታረቃሉ፤ ቁርጡን ተጠያይቀው ይገበያያሉ።

በሰማይና በምድር ፈጣሪ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሰው እዚህ ገበያ ውስጥ ሲኖር የአኗኗሩ ሁኔታ የጌታው ፈቃድ እንደገባው መጠን ልቡን ለእውነት እንዳሰለጠነው መጠንና ዐይኑ አንደተከፈተለት መጠን ነው። አንዳንዱ በገበያው ዳር ቆሞ የሚዥጎደጎደውን ጅር እየታዘበ ሁሉን በአጠገቡ ያሳልፋል። ሌላው አንዳንዱ ከየመደብሩ የሸቀጥ ዐይነት እየቆነጠረ እያደባለቀና እያዋሃደ ኮረጆውን ይጠቀጥቃል። ምናልባት የሚበዛው ግን በገበያው መካከል ባለ አንድ በር፣ መስኮት አልባ ዳስ ሠርቶ ከሁካታው፣ ከውጣ ውረዱ፣ ከእሰጣ ገባው ሁሉ ተከልሎ ይኖራል። ለአንዳንድ አስፈላጊ ጉዳይ ብቻ ሲባል ወጣ ብሎ ግርግሩ ውስጥ ዘው ይልና ወዲያው በጥድፊያ እዚያው ዋሻ ውስጥ ይከተታል እንደ ቀንድ አውጣ። ለነዚሁ ጉዳዮቹ የወጣ ዕለትም ራሱን፣ አፉን፣ ዐይኑን፣ እጁን በስንት ክንብንብ ጀቡኖ ነው።

ይህ የዳስ ነዋሪ ወይም "ዛጎል ቤቴ" ለምን እንደዚህ እንደሚኖር ሲጠየቅ ከሚሰጣቸው መልሶቹ አንዳንዶቹ እነሆ፦

➢ "ውጪው የደባ ገበያ ነው፤ ቅንነት የሚባል ድራሹም የለ ስለዚህ በተንኮሉ ወጥመድ እግሬ እንዳይጠለፍ ነው መከተቴ"

➢ "ገበያተኞቹ ሁሉ የጭራቅ ዝርያ ያለባቸው ይመስለኛል፤ ገና ሳትደርስባቸው ነው በዐሥር ቀንድ የሚወጉህ፤ ለዚህ ነው ጐመን በጤና ብዬ ወደ ጐጆዬ የምሮጠው"

➢ "ደግሞ ከነሱ ምን አገኛለሁ ይህቺ ጐጆዬ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አካትታ ይዛለች። ባልንጀርነት ሲያምረኝም እንደኔ ዐይነት ዳስ የሠሩ አልፎ አልፎ አላጣም እነሱ ዘንድ መሄድ እችላለሁ።"

እነዚህ መልሶች እውነትነት አላቸው። የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ያላወቀ ከርሱም ጋር ሕያው ግንኙነት ያልመሠረተ ጎብረተ ሰብ ምን ጨዋ ቢሆን ከራስ ወዳድነት ተለቃልቆ ሊጸዳ አይችልም። ሕይወቱ ጉድፍን ማከማቸት ብቻ ሳይሆን በየመንደሩም የሚዘራ ነው። በልብ የሞላው ሲተርፍ መውጣቱ አይቀርምና። ስለዚህ አየሩ ተበክሏል። በዙሪያችን ሁሉ የጎጢአት ጢስ በያለበት ይትጐለጐላል። ንጹህ አየር ለመተንፈስ ሲባል ሽሽት ቢጀመር ምክንያቱ ግር አይለንም።

ዓለማዊው ሰው ከሩቅ ሲያዩት የእሾህ ክምር መምሰሉ በእግዚአብሔር ፍርሃትና በመልካም አሳቦች የለሰለሰን ቆዳ የሚጣረር መምሰሉ አይቀርም። ክርስቲያኑ ሕዝብ የራሱ ጎብረተ ሰብና የራሱ የአኗኗር ባህልም ስላለው በዚያው ሙቀት ውስጥ መኖሩ ሕይወትን ቀላል ያደርገው ይሆናል።

ዳሩ ግን ሌላም እውነት አለ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የዩኒቨርስ ፈጣሪ ነው። የሰማይና የምድሩ፣ የሣር የቅጠሉ፣ የሰውም ፈጣሪ ነው። የወንዱ የሴቱ፣ የገራሙ፣ የእብዱ። በመሠረቱ እኮ የእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር የለም። እርሱ ባለቤትና ጠቅላይ ገዥ ነው። በዲያብሎስ ተንኮል ከብቸኛ አባቱና ጌታው ያፈነገጠ ዓለም ውስጥ ነው የምንኖረው። ይኸው ብቸኛ ጌታ ብቸኛ አዳኝ ሆኖ መጥቷል።

የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላ አውራጃዎች ሲዞር ምን ያደርግ ነበር? በከተሞች፣ በመንደሮች፣ በገበያ በምኩራብ፣ በቀራጭ ቤት፣ በፈሪሳዊ ግእድ፣ በለቅሶ ቤት፣ በሰርግ ቤት፣ ይህን ያፈነገጠ ዓለም ያስታርቅ ነበር ከአባቱ ጋር በራሱ በኩል። ልዑል እግዚአብሔር

ዓለሙን ለራሱ አልተወውም። ወደ ዓለሙ መጣ እንጂ። "በሽተኛ ሆይ የራስህን መድኀኒት ፈልግ" አላለም። በልጁ መስዋዕት መድኀኒቱን ሰጠው እንጂ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ገና ያላመኑትን እንዴት ነው የሚያስባቸው? "ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱንም ደግሞ ላመጣ ይገባኛል" አለ። እንደሚንከራተቱ በጐች፣ ቤታቸውን አጥተው እንደጠፉ በጐች በየስርቻው ያገኛቸው ሁሉ እንደሚደበድባቸው እንደሚያዋክባቸው፣ የተቅበዘበዙ፣ የደከሙ ተንከራታች በጐች። "መንገዱ በዚህ ነው" እያሉ ስንት ሌቦች ወደ ማረጃው ጐተታቸው።

እንግዲህ የዛጐሉ ሰው ምን ያስፈለገዋል ቢባል መልሱ ነፃነት ነው።

ነፃነት ማለት ባለ አንድ ሜትር ካሬ ዳስ ውስጥ እንድኖር ማን ፈረደብኝ የሚል ብርቱ ጥያቄ ነው። ነጻነት ማለት ከዳሱ ውጭ ያለው መሬት ሁሉ የአባቴ ነው ብሎ መፎከር ነው። ነጻነት ማለት በተረጋገጠ ዐለት ላይ ቆሞ እነሆኝ እዚህ አለሁ፤ እነሆ እናንተም እዚያ አላችሁ ማለት መቻል ነው። ይህ ነጻነት መሠረቱ ጽኑ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በተገኘው ድል ምክንያት በስሙ በማመንም በተገኘው ታላቅ ስጦታ ምክንያት የሆነልን የእግዚአብሔር ልጅነት ክብር ነው።

የክርስቶስ ባሪያ እንደዚህ ነጻ ሲሆን እጅ እግሩ፣ ዐይን አፉ ሲፈታ ሦስት ነገሮች የሚሆኑ ይመስለኛል። የመጀመሪያው ነገር ይህ ነፃ ሰው እውነተኛ ዕይታ ማግኘቱ ነው። በዙሪያው ያሉትን አብሮ አደሮች፣ አብሮ በሎች ለማየት ዐይኑ ይከፈታል። ጥምጥሙን ከለላውን ከዐይኑ ላይ ያነሣል። እነዚህ ሰዎች እውነተኛ ማንነታቸውን ምንድን ነው ይላል። በሳቅ፣ በጨዋታቸው የሸፈኑትን ጎዘናቸውን የነፍስ ኩርፊያቸውን ያስተውላል። ብዙዎች ጐረቤቶቻችን ንግግራቸው የጀግና ይምሰል እንጂ ከብብታቸው ሥር ያለው ሰብእና በፍርሃት የሚንቀጠቀጥ ነው። ሲሟገቱ እውነት የያዙ

ይመስል ቃላት ያዥጐድጉዱ እንጂ ውሽንፍሩን አስጨርሰን ስንሰማቸው የሕይወት ባዶነታቸውን እናያለን። የሚሰድቡን፣ የሚንቁን፣ የሚያላግጡብንና የሚሸሹን እነዚህን ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጠን ነፃነት በርኃታ ስናያቸው ዛቻና ጥላቻቸው ሁሉ የመከላከያ ጋሻዎች የድንግርግራቸው መደበቂያ ጭምብሎች ይሆናሉ። ከዚህ እውነተኛ ማየት ርኀራኄ ይፈልቃል። "እረኛ እንደሌላቸው በጐች ተጥለውና ተጨንቀው አያቸው አዘነላቸው" እንደሚለው ማቴዎስ ወንጌላዊው። የሰዎችን ሁኔታ አስተውለን ብንመለከት የምንረዳው መሠረታዊ ችግራቸው ተመሳሳይ መሆኑን ነው። ይህም ከአዳም ጀምሮ ያልተቋረጠው ጠብ ነው። ከሚወደንና ከሚጠቅመን ከነፍሳችን ፈጣሪ ጋር መራራቅ፣ መለያየት፤ በዚህም ሳቢያ የተከተለው ስንት እበሳ።

ስለዚህ ይህ ነፃነቱን ያገኘ ሰው የሚሆንለት ሁለተኛ ነገር ለመሠረታዊ ጥያቄ መሠረታዊ መልስ እንዳለው ማስተዋል ነው። ይህንንም አስተውሎ ሳይፈራና ሳያፍር ግን በትህትናና በፍቅር ይህን መድኀኒት በገበያው ላይ በይፋ ያቀርባል። ቅዱስ ጳውሎስ በአቴና አደባባይ እንዳደረገው። "እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎአል ... ሰውን ሁሉ ንስሓ ግቡ ይላል ... በቀጠሮው ቀን የሚፈርድ አሁን ግን የሚያድን ሰው አዘጋጅቷል ያውም ከሞት የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ"።

ሦስተኛው የሚያከናውነው ነገር ይህ የነፃነት ልጅ የሚያምነውና የሚናገረውን እዚያው ገበያው ውስጥ በገሃድ በሚጨበጥ መልክ መኖሩ ነው። ቃሉ ሳይጥበረበርበት "እንዲህ እያለ እንዴት እንደዚያ ይሠራል" "ለካ ምላሱ ብቻ ነው" ሳይባል ከእርሳስ አያያዙ እስከ ሰው ማስተናገዱ፣ ከጸሎት ጥሞናው እስከ ደስታ ጭብጨባው ያው አንድ ሰው ሆኖ ይኖራል። ሲወድቅ ውድቀቱን በብልጠት ሸፍኖ አያጭበረብርም።

ሲሳሳት ይቅርታ ለመጠየቅ አያፍርም ኑሮን ይኖረዋል እንደ ክርስቲያን፣ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ፣ እንደ ክርስቶስ ባሪያ። ውስጣዊው ሰውነቱን የሸፈነ የሥጋ አካል እንዳለው አይክድም፣ የሚጐዳ፣ የሚደክም፣ የሚጠፋ፣ ግን ደግሞ በዚሁ ሰውነት ውስጥ ሌላ ታላቅ ሰብእና በመለኮት ጣት የሚንቀሳቀስ ባለቡሩክ ተስፋ ሰው እንዳለ እያሳየ ይኖራል።

የዛጐሉ ሰው ሆይ ና ተገለጥ፤ የአምላክህን ምድር ርገጥ፣ የቀድሞ ወዳጆችህን አትራቃቸው፣ የወደዱህን ግን ደግሞ ውደዳቸው። ጌታህና አዳኝህ አንተ ጠላቱ ሳለህ ከወደደህ፣ ፍለጋ ወጥቶ ካገኘህ በገበያው ውስጥ ተቅበዝባዦችን ፈልጋቸው። እነሆ በረቱ በላቸው። እነሆም እረኛው።

«እስር ቤቱን ስበር ክንፍ ስጠኝ ልብረር»

(ለክርስቲያን ምሩቃን)

አብዛኛው ሰው የሕይወቴ ጥሪ ነው ብሎ የያዘው ነገር የለውም። በልቶ ከማደር አድሮ ከመብላት፣ ሥራ ወጥቶ ከመግባት ወይም ገብቶ ከመውጣት ድግግሞሽ ያለፈ ሁነኛ ዓላማ የለውም። መሽቶ መንጋቱን ዓይኑ እያየ ቆዳውን ሲሸበሽበው፣ ቀለሙን ሲለውጠው፣ ወገቡን ሲያጎብጠው፣ ብርሃኑን ሲያስለመልመው እየፈዘዘ ያሳልፈዋል ሞልቶ እንደሚፈስ ጅረት።

አብዛኛው ሰው ነፍሱ ውስጥ አሳት የለም፤ ካልተገደደ በስተቀር ይሁንኝ ብሎ በሙቀት የሚከታተለው የሕይወት ጎዳና የለውም። የኑሮ ጎማው ሽክርክሪት እንዳይቆም በድግግም መተሻሸት የሚለጠ ጎማውም እንዳይንሸራተት ጅላጅል ሚዛኑን ጠብቆ ይንከላወሳል። ምክንያቱም ነቅቶ ቢገሰግስ የሚደርስበት ቦታ አይታየውም ለማን አባቱ ሲል ነው ትንሩሽ የሚያጥረው! ወደዚያ ወደ ማዶው ደርሶ የሚደነቅበት ጉጉት የለውም። እንዲያውም ማዶ የለም ሁሉ እዚህና ያው ነው።

አብዛኛው ሰው ክንፍ የለውም ከተለመደው ከፍታ በላይ ወጥቶ አያውቅም። አጠቃላዩን ባንድ እይታ ለማየት ዕድል አላገኘም አጠቃላይ የሚባል ነገረ መኖሩንም በቅጡ አያውቅም። እሱ የሚያውቀው የቅርቡን ነው፣ ዝርዝሩን ነው፣ የጓዳውን ነው። የአጎቱ ልጅ በኤድስ በሽታ ማቆ በቀደምለት ሞተ። ተሯሩጦ ለቀብር ከደረሰ ይበቃዋል። መሥሪያ ቤታቸው ደሞዝ ይጨመራል አሉ የእሱን ክፍል ይመለከታል። አንድ ሃምሳ ብር ቢጥሉለት የታክሲ ወጪውን በግማሽ ይችልለታል። በሕንፃ ሥራ ኮሚቴ ውስጥ ተመርጧል። ማክሰኞ ስብሰባ እንዳይቀር ስዓቱን በቀኝ እጁ አዙሯል። ከአመት በኋላ ኮሚቴው እስኪለወጥ ቢሠራ ምንም አይደል። ነገሮችን በዝርዝሩ ነው

የሚያውቃቸው ዓለሙ ብጥቅጥቅ ነው። አንድ ቁራጭ እዚህ ሌላ ቁራጭ እዚያ።

አብዛኛው ሰው በርሮተከንፎ አያውቅም። «እንዴ መብረር አደገኛ ነው» ይላል። ምክንያቱም አንዳንድ የበረሩ ባልጀሮቹ ክንፋቸው ቆሳስሎ ያው እዚያ ጥግ ያቃስታሉ፤ ያኔ የበረሩ ጊዜ ያዩትን እያወሩ። ስለዚህ ይህ ሰው በሕይወት ስርጥ ጎዳና ሲሽሎከሎክ ዕድሜውን ሊጨርሱ የሚችሉ በቂ ጠመዝማዞችና ኮሪደሮች አሉት።

ይህ አብዛኛው ሰው ክርስቲያን ሊሆን ይችላል። ክርስቲያን ሆኖ «የተማረ የተመራመረ» ሊሆንም ይችላል። የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሊሆን ይችላል። ይህ አብዛኛው ሰው ነገር ሲሰለቸው አልፎ አልፎ ቁና ይተነፍሳል ተንፍሶ ግን ወዴትም ዞር አይልም። ጎማውን በትካዜ እየገፋ ይንከላወሳል። ሄዶ ሄዶ እቆመበት ድረስ።

ምንድነው ጥሪ? ምንድነው እሳቱ? ክንፉስ ምንድነው? ራእይ ነው። ብዙ ሰው ባለ ራእይ አይደለም። አንዳንዱ ምናልባት አንድ ጊዜ ብልጭ ያለለት ነገር ነበረው። ደመናና ጭጋግ፣ አቧራና ጢስ ጮራውን አደበዘዙበት እንጂ። ዓይኑን አሥር ጊዜ ያሻል። ቅርጽ ያለው ነገር ግን አይታየውም። ነፍሱ በማየት ራብ ስትሳቀቅ ምናምን እየጎሰጎሰ ያስተኛት ለምዷል። አሁን የነፍሱ ጓዳ ቢፈተሽ ስንት የዘመን ገለባ አለው። ስንት ገፈትና አሠር አጠራቅሟል ነፍሱን ያባበለበት ገፈራ።

ባለ ራእይ መሆን የእግዚአብሔርን ዓይን ማግኘት ነው። ነህምያ ለምሳሌ ባለ ራእይ ነበረ። ፍራሹንና ቅሌቱን እግዚአብሔር በሚያይበት ዓይን ማየት ስለቻለ። ቅዱስ ጳውሎስ ባለራእይ ነበረ። ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ወንጌል ብልጥግና እግዚአብሔር አብ እንዳየው ማየት ስለቻለ። አብርሃም ባለ ራእይ ነበረ። «መሠረት ያላትን ከተማ» ከፍቅ ማየት ስለቻለ። ራእይ ሁሉን ቻይ አምላክ የሚያየውን በእኛ ውሱን አቅም ለማየት መብቃት ነው። ያቅማችንን ያህል።

ራእይ የሰነፍ ሰው የቀን ቅዠት አይደለም። «እንዲያው ምናልባት ባለ ሠላሳ ፎቅ ቤት ሠርቼ በአናቱ ላይ ኳስ መጫወት ብችል»፣ «እንዲያው ምናልባት እንደ አላዲን ቀለበት ጣቴን አሻሽቼ አሥር ኩንታል ወርቅ የተጫኑ ግመሎች ፊቴ ቢደቀኑ» ራእይ የራስ ወዳድነት ያልተገታ ምኞት መቀቀያ «መንፈሳዊ ሰታቴ» አይደለም። «ወንድሞች ጌታ ታላቅ ሰው እንደሚያደርገኝ ራዕይ ሰጥቶኛል። ዛሬ ከእኔ ጋር መዋል ማለት ከሰማይ ምንጭ ጋር አሸንዳ የመዘርጋት ያህል ነው፤ በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ሁሉ የየራሳቸው ካዲላክ መኪናዎች፣ ቤቶች እንዲሁም ትልልቅ የንግድ ሱቆችና አውሮፕላኖች እንደሚኖሯቸው ይታየኛል። ለዚህም ጉዳይ ማስፈጸሚያ ያላችሁን አሁን ለእኔ ብትሰጡ ራእዩ ይፋጠናል።»

የመንፈሳዊ ራዕይ ማዕከል የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። የፈረሰው እንዲጠገን፣ ያልተያዘው መሬት እንዲያዝ፣ ባንዲራው ባልተተከለበት እንዲተከል፣ ጉልበት ሁሉ እንዲንበረከክ፣ ምላስ ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ እንዲመሰክር ነው።

አንድ ቀን ለአገልግሎት ተጠርቼ ወደ ስብሰባ ቦታ ሄድኩ። መጽሐፍ ቅዱሴን ይገፍ ማስታወሻ ደብተሬን አመቻችቼ ስጠራ ወደ ምሰባኩ ወጣሁና ልናገር አፌን ገና ሳልከፍት በምሰባኩ (ፑልፒቱ) የውስጥ ጉበን ላይ በእንግሊዝኛ የተጻፈ ጥቅስ አየሁ። እንዲህ ይላል «ጌታው እኛ ማየት የምንፈልገው ኢየሱስን ነው።» ጥቅሱ አቀፈጠነኝ፣ ገራኝ፣ ልክ አስገባኝ፣ ትሁት አደረገኝ፣ ቦታዬን ነገረኝ፣ ተልዕኮዬን አስታወቀኝ፣ ያ ጥቅስ ባለውለታዬ ነው።

በጤና የታየን ከሆነ የኢየሱስ ጌትነት፣ ጌትነቱ የሚታወጅበት መንገድ፣ በእኛ ልዩ ሁኔታ ይህ ታምራት የሚገለጥበት ጥበብ ነው የሚታየን። ለምን አንድ ቀን አይሆንም የኢየሱስ ጌትነት በሕይወቴ ታይቶ ከምድር ብሰናበት።

ወዳጆቼ ሆይ፣ ዐይን አላችሁ? ያልፈዘዘ፣ ሩቅ የሚያይ። ሩቅ አይቶ በቅርብ ያለውን መንገድ የሚያመቻች። ለምሳሌ ከመንገዱ ላይ ጋሬጣውን ማንሳት፣ እሾሁን መመንጠር፣ ስርጓጉጡን ማስተካከል ሊሆን ይችላል። የክብር ንጉሥ ሠረገላ እንዲሮጥ፣ ሥጋ ለባሽ ሁሉ የእግዚአብሔርን ክብር እንዲያይ። ሕይወታችን እባካችን ተራ አትሁን እንደማንም ሰው ሁሉ ከራሳት አሥረን፣ ማኪያቶ እየጠጣን አንሙት።

በቆይታ፣ በርጋታ ጌታን እንለምን። «ማየት የሚያስፈልገኝን አሳየኝ። የምታሳየኝን ልተጋበት የሚያስችል ጉልበት ስጠኝ። ወኔዬን አኮስትር፣ ሐሞቴን አቆፍጥን፣ አልጫነቴን አውጣ ከታዛቢነት ወደ ተሳታፊነት ጥራኝ። ራሴን በግድ ወደ ማሳህ እንዳልወረውር፣ ዳር ቆሜም እንዳላንሾካሹክ ኩልል ያለ ጥሪ ስጠኝ። በምትሰጠኝ አቅምና ቦታ በምታስለምደኝ ስልትና ጥበብ እንድራመድ አሰልጥነኝ። ሁሉ ከአንተ በአንተና ለአንተ ነው ለዘላለሙ አሜን።»

ከእናንተው ጋር ብርሃን ለማኝ ወንድማችሁ

ወጣት አልወጣት

መጀመሪያ ወጣት

ልክ ልካችሁን ብነግራችሁ ትቆጡኛላችሁ? ማለቴ «የተገለጠ ዘለፋ ከተሰወረ ፍቅር ይሻላል» (ምሳ 2:5)። ሰዉ በየጓዳው ያማችኋል «የዘንድሮ ልጆች የጉድ ልጆች ናቸው» ይላችኋል። ከሁሉ ከሁሉ «ሰው አይሰሙም» የራሳቸውን ካልሆነ ሌላ የሚያደምጥ ጆሮ የላቸውም።ግና አንድ ቃል ሲናገሩዋቸው በእልፍ ቃላት እሩምታ አፍ ያዘጋሉ። የሰከነ ውይይት የሚሉትን አያውቁትም አይወዱትም። በራሳቸው ድምፅ ጢም ተደርገው ተሞልተዋልና እንዴት እናናግራቸው? ይሏችኋል። ወጣቶች ይህ እውነት ነው እንዴ?

ምናልባት «መካሪዎች ነን» ባዮች የዕብነ በረዱ አሥረኛው ፎቅ ላይ ሆነው እናንተን ወደ መሬት እያዩ ስለሚናገሩ ይሆን? ወይስ እውነት የምትወዱት ድምፅ የራሳችሁን ነው? «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለቁጣ የዘገየ ይሁን» የሚል ቃል እንዳለ አታውቁም?

የሚሉዋችሁን ልንገራችሁ: ወጣቱ ሁሉ አጫፋሪ ነው የራሱ የሆነ ማንነት አውጥቶ አውርዶ የተቀበለው እውነት የለውም። የእነገሌ አጨብጫቢ ብቻ ነው። አንድ የታወቀ ሰው ወይም ቡድን ያገኘ እንደሆነ በእርሱ ዙሪያ እንደ ንብ መትመም ነው እንጂ ክፉና ደጉን ለመለየት በርጋታ ማጤን የሚባለውን በፍጹም አይሞክረውም። «ዘራፍ እኔ የክሌ አሸክር» ነው ፉከራው። «ጀግና» የሚለውን ሰው ሲነኩበት እንደ ግሥላ ይገሥላል፣ እንደ አንበሳ ይከመራል እንደ ነብር ዓይኑ ይቀላል ከዚህ በኋላማ ለሚነካው ወዮለት «ጀግኖች» የሚላቸው ሰዎች ሥጋና ደም እንዳለባቸው የስህተት ነፋስ አንዳንዱ እንኳ ነፍሳቸውን እንደሚያዘምም ሊቀበል ያዳግተዋል።

ምናልባት ይህ የመጣው ከወጣት ጀግና ፈላጊ ተፈጥሮ የተነሳ ሊሆን ይችላል። ጀግና መፈለግና እርሱን ለመምሰል መሞከር ምን ክፉት

አለበት? ምንም:: ግን የሁልጊዜ ጀግና እንክን የለሽ አለቃ አንድ ብቻ ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን ምን ታመጡለታላችሁ በፍቅር ቢሆን በጥበብ፣ በቃል ቢሆን በሥራ፣ በርኅራኄ ቢሆን በኃይል ማን ይመስለዋል?

በሚያሳቅሉት ጠላቶች ፊት ለፊት ቆሞ «ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ የሚከሰኝ ማን ነው?» ብሎ በድፍረት የጠየቀ ክስም ስላልተገኘበት ሰውን ሁለ ያስደመመ የእውነት ፈታውራሪ ነው::

ወጣቶች ስሙ አብራችሁ መክነፍ ካስፈለጋችሁ ከዚህ ሰው ጋር ክነፉ:: ባንዲራ መያዝ ከፈለጋችሁ የማንንም ቀለማም ጨርቅ አታውለብልቡ:: የዚህን ሰው የፍቅር ዓርማ አንግቡ:: ማንም አያንበርክካችሁ ለአላፊ አግዳሚው ሁሉ ሎሳልት አትሁኑ፤ ነፍሱን የሰጠላችሁ ጌታ እያለ:: ሌሎች ጀግኖችን ማድነቅ ይቻላል፤ ነገር ግን የጀግና መለኪያችሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን:: ሌላም የሚሉዋችሁ አለ:: መለኪያቸው ተሳስቷል መንፈሳዊነትን የሚመዝኑት በምድር ብልጥግና በብርቅርቅነት በታይታ በጌጥና በቁንጥ ሆኗል:: የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ ብሎ የሚለውጠው ኮት ከሌለው የድኽነት መንፈስ ተጠናውቶታል:: በእግሩ የሚኳትን ከሆነ «ራስ እንጂ ጅራት አላረግህም» የሚለው ቃል አልገባውም ትሉታላችሁ አሉ:: በጣም መንፈሳዊ የሆነ ቢሆን በኪሱ ብር ይታጨቃል:: ዝናብ የሚያፈስ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ እየኖረ እንዴት የንጉሥ ልጅ ነኝ ይላል ትላላችሁ እየተባለ ነው፣ እውነት እንዲህ ትላላችሁ?

መቸም እንደዚህ የምትሉ ከሆነ የአዲስ ኪዳንን ክቡራን ሰዎች አፈር ድቤ እያገባችሁ ይመስለኛል:: አዚያ መጽሐፍ ላይ ከቡራን የተባሉት የበግና የፍየል ሌጦ የለበሱ - ቀበሌ የማያውቃቸው ተንከራታቾች ናቸዋ ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም እኮ ጠሙን እንዳያድር (አንዳንድ ቀን ጠሙን ሳያድርም አልቀረም) በትርፍ ጊዜው ድንኳን የሚሰፋ ከዚያችውም

ለሌሎች የሚሰጥ አገልጋይ ነበረ:: በባንክ የሚያከማቸው ብዙ ገንዘብ የነበረው አይመስልም:: የኢየሱስ እናት ማርያምስ ብትሆን ባለ ብዙ ገንዘብ ብትሆን ኖሮ ለመሥዋዕት ርግብ ታቀርብ ነበርን? «በእጅ ያልተሠራች ሰማያዊት አገር ይናፍቁ ነበርና እንደ መጻተኛ ኖሩ» የሚለው ይልቅ የእግዚአብሔር ሰው አመለካከት ነው::

ሪቫይቫል ታሳድዳላችሁ ይሏችኋል? ምንድነውሱ ሪቫይቫል? ሞቅታነዋ በኪይ ቦርድ ታምቡር ድምድምታ በጎረምሳ ኮቴ ረገዳ ባልተለካ ድምጽ ጩኸት «የፈለገውን ይሁን ጎረቤት» ድፍረት አብሮ መሆን:: እንደዚህ የሚሉዋችሁ ሰዎች እውነት እናንተ የምትፈልጉት ገብቷቸው ይሆን? እናንተ የምትፈልጉት መነቃቃት ለጌታ በተከፈተ ልብና አካል አክብሮት መስጠት ሳይቆጥቡ ለእርሱ መገዛት አይደለም እንዴ? ግን በሌላ ተተርጉሞባችኋል:: አገር እየረበሹ ነው ከእነርሱ ጋር ለ10 ደቂቃ እንኳ መጸለይ አይቻልም ጩኸት በጩኸት ነው ጆሮህ ይታመማል በፍጹም ጥሞና የሚባል ነገር አያውቁም:: ጨፋሪውን ሁሉ ጠጋ ብለህ ብታነጋግረው ጥልቀት የሌለው ዘላይ ብቻ ነው:: የሕይወትን ውስብስብ ሊፈታ የማይችል የጊዜውና የአሁን ሰው ብቻ ነው:: ከየቦታው የቆነጠረውን አንዳንድ ቅመም ደበላልቆ ነው ሪቫይቫል የሚለው:: ጌታን የማጸመጥ በርጋታ የማምለክ የሌሎችን የጸሎትና የአምልኮ ልማድ የማክበር ብቃት የለውም ሆይ ሆይታና ጥድፊያ ብቻ ነው የሚገዛው ይሉዋችኋል::

እውነተኛ ሪቫይቫል - ደስታ አለበት:: ስለዚህ በሙቀት ብትዘምሩ እኔ ክፋቱ አይታየኝም:: እውነተኛ ሪቫይቫል ንስሐም አለበት በጥሞና ኑዛዜ በማድረግ ራስን መመርመር ተገቢ ነው:: ነጻነታችንን ለማንም መሸጥ አያስፈልገንም ግን የእኛ መብት ለሌሎች እንቅፋት እንዳይሆን ተጠንቀቁ ተብለናል:: እርኒታችንም የክፋትና የሥርዓት አልበኝነት መሸፈኛ አይሁን:: እውነተኛ ሪቫይቫል ጥልቀት አለው የሚጀምረው

ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለሆነ የሰውን መገሙር ብቻ ሳይሆን የዕለት ኑሮውን ይነካል «ሃሌሉያ እንደሚያሰኝኝ» ሁሉ «ሰው እንድወድ» ያደርገኛል።

ሌላ ደግሞ «ሁሉ ነገር ዛሬ ካልሆነ....» ትላላችሁ አሉ ምን ማለታችሁ ነው ፈጣሪ እንኳ በአንድ ቀን ሥራውን አልጨረሰም።

ቀጥሎ አልወጣት

ከወጣትነት ተርታ በዘመን ቁጥር ምክንያት የተፈናቀለ ወጣቱን በጎሪጥ የሚያይ አላፊ ትውልድ ሆይ ወጣቱ የሚላችሁን ስሙ፣ አንሰማም ብትሉ እንዳከረፋችሁ መሄዳችሁ ነው። የሚበጀው ማዳመጡ ነው።

መጀመሪያ ነገር እኛን ወጣቶችን በሙሉ በደምሳሳው ይጠረጥሩናል፣ አያምኑንም «ለኮንፍራንሳችን ጋሻ እከሌን እንጋብዝ» ብንል ዶክትሪን ሊገለብጡ ነው ይሉናል። ለቤተክርስቲያን የሚያስቡ ለእውነት የቆሙ እነሱ ብቻ እንደሆኑ ይመስል በስንት መከራ አስፈቅደን ያገኘነውን መሰብሰቢያ ቤት «ምን እንደሚሠሩ ስለማናውቅ እኛ አላፊ አንሆንም» ብለው ያዘጉብናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስንወጣ እህቶችና ወንድሞች ሁለት ሁለት ሆነን ከሄድን የሚያስቡን በአንድ መንገድ ብቻ ነው። ለምን አታምኑንም? እውነት ለምን አታምኑዋቸውም? ፍላጎቱ ቢኖራቸውም ብቃቱ የላቸውም እያላችሁ ይሆን? መጀመር ቢያውቁም ጽናት የላቸውም እያላችሁ ይሆን? ችግራችሁ ይገባኛል። ግን ስሙ ሳሙኤል በእስራኤል ሁሉ የታመነ ነቢይ እንደሆነ ከመታወቁ በፊትኮ እግዚአብሔር በልጅነቱ ድምፁን አሰምቶታል ሥራም አስለምዶታል። ዳዊት ጎልያድን ዘርሮ ሆ ከመባሉ በፊትኮ ከስንት አንበሳና ድብ ጋር ታግሏል የመለማመጃውን ሜዳ ለምን ትከለክላላችሁ? እናንተስ ብትሆኑ የምትንገዳገዱበት ጊዜ የለም? እየታረመ ጎሽ እየተባለ እየታረመ አይዞህ እየተባለ የሚኬድበት ጎዳና ነው ሕይወት ራሱ።

እንደዚህም ይሏችኋል «አዋቂ» ነኝ ባዩ ጎበረተሰብ ለውጥን እንደ ጦር ይፈራል። ጥንት ከለመደው ሥርዓት ውጭ አንድ ነገር እንኳ እንዲነቃነቅ አይፈልግም። ሌላው ቀርቶ በአንድ እሁድ ጠዋት ሁለት መዝሙር በመዘመር ፈንታ ዛሬ አምስት ይዘመር ቢባል በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተፈጠረ ከፍተኛ ነውጥ አድርጎ ያስባል። በወር አንድ ጊዜ እሁድ ጠዋት በአምልኮ ፈንታ ምዕመኑ ሁሉ ለምስክርነት ይሰማራ ቢባል «አዲስ ትምህርት መጣ» ይላል። ወዳጆቼ አዋቂዎች በጎ ውጤት ማምጣቱንና መሠረታዊ ጤነኛነቱን መርምሩ እንጂ አዲስ ነገር አትፍሩ። አንዳንድ ቀን «አባታችን ሆይ» የሚለውን ጸሎት የሰብስባው መክፈቻ ጸሎት አድርጉት።

ትላልቆች ሆይ - ሌላም እየተባላችሁ ነው። እኛ ወጣቶች ሥራ እንፈልጋለን ጉልበት አለን ጉጉት አለን። ዕድሜያችን ጠቃሚ ተግባር ላይ እንዲውል እንፈልጋለን ነገር ግን የሚያሠማራን የለም። ሥራ ካልሰጡን እኛ መፍጠራችን አይቀርም፣ በይ ቀድደው በዚህ ሂዱ ካላሉን ግንብም ቢሆን በስተን እንወጣለን እኛ ይህንን እንሥራ ስንላቸው «እኛ በምንሠራው ኑሩ» ይሉናል። በቤተ ክርስቲያን ቁጭ ብሎ ተቀላቢ መሆን ደከመን ጡንቻዎቻችንን የሚያንቀሳቅስ ነገር ስንሞክር ቤቱን ልንንደው የተነሳን ይመስላቸዋል ከተናደ ይናዳ! ሌላ ሰፊ ቤት ለመገንባት ዕድል ይሰጠን ይሆናል።

እውነት እናንተ አዋቂዎች ሰው ያለሥራ ሲቀመጥ ሊያብድ እንደሚችል ዘንግታችሁት ነው? ወይስ «የተሰጣቸውንስ በቅጡ መች ሠሩት» ብላችሁ? ስሙ - የእግዚአብሔር መንግሥት ሰፊ ናት መከሩም እጅግ ብዙ ነው ወጣቶች በዚህ መስክ ላይ ሊሠሩት የሚፈልጉትና የሚችሉት ጉዳይ ያለ ከመሰላቸው እናንተ መደሰት ነው ያለባችሁ። ቅርጽ እየሰጣችሁ ከጎላ መከታተል ነው ጥሪያችሁ። አንዱ ወጣት እድ ሁለት ዓመ ቢገኝስ ጠጋ ብላችሁ እዩ። አንዳንዴ ልጆቹ ራእይና ቅዠትን መለየት እያቃታቸው ሁሉን ቢነካኩ የተሻለውን መስመር

ማሳየት ይገባል እንጂ እንዲበገኑ አትተውአቸው «በመጨረሻው ዘመን መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ....ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ::»

ሽማግሌዎች - አዋቆች - መሪዎች - ትልልቆች ሆይ ብዙ ነገር ብትባሉም ከሁሉ ከሁሉ የሚያሳስበኝ «እነዚህ መሪዎቻችን ግብዞች ናቸው» የሚለው ነው:: የሚናገሩት የሚሰብኩት ሌላ የሚኖሩት ሌላ እኛ በተቻለ መጠን እንደ ቃሉ መኖር እንፈልጋለን:: ለምሳሌ ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል ካለ አባቴ ከስድስት ከቱ አንዱን ለምን ለአየለ አይስጠውም? ትናንት ቤታችን መጥቶ ሲጸልይለት «የሥራ ዕድሉን የዘጋህበት ጋኔን ለቀህ ጥፋ» እያለ ሲጮህ ነበር:: ጸምና ጸሎት ጠቃሚ እንደሆነ ሲናገሩ ቢውሉ አይደክሙም ግን ለአንድ ሰዓት ተንበርክከ መጸለይ ያቁነጠንጣቸዋል:: «ቅድስና ጠፋ» እያሉ ብዙ ጊዜ ያወራሉ እኛ ቤተ ክርስቲያን እንኳ በዚህ ዓመት አራት ጊዜ በዚህ ርዕስ ላይ ትምህርት ሲሰጥ ነበር ግን መሪዎቻችን ከስብሰባ ውጭ አንዱ የአንዱን ጉድ እያወሩ ሲተማሙ ስንሰማ ይዘገንናል::

አዋቂዎች - ይህን መቸም ምንም ልጨምርበት አልፈልግም:: እኔ አንድ ነገር ልንገራችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መሬት ቢመጣ (እንደ ድሮው ዘመን) ጠቡ ከማን ጋር ይመስላችኋል? ማጅራት መቺዎችን ሄዶ ከመውቀሱ በፊት ሴተኛ አዳሪዎችን ምንም ከመናገሩ በፊት ከቤተ ክርስቲያን አለቆች ጋር የሚፋጠጥ ይመስለኛል:: መስሎኝም እፈራለሁ:: ሁሉን የሚታገሰው ጌታ ግብዝነትን መታገሱን እጠራጠራለሁ:: ወጣቶች ባለብዙ ስህተት እንደ መሆናቸው ሁሉ ባለብዙ ቅንነትም ናቸው: ስሚቸው ታገሱዋቸው አቅኑዋቸው:: ከሁሉ ይልቅ ደግም ውደዷቸው:: የልባቸውን በር የሚከፍቱላችሁ በፍቅር ጣት ብታንኳኩ ነው::

በመጨረሻ ለወጣትም ለአልወጣትም ይህን የምጽፍላችሁ ሰው ሁላችሁንም በእርግጥ የምወዳችሁ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ለ "ቤተ ክስያን" ሂያጆች

በየሰንበቱ÷ የተጋን እንደሆነም በየሠልስቱ ቤተ ክርስቲያን የምንሔደው ለምንድን ነው? የነፍስ ዕዳዬን ለመክፈል፣ ስማዩ እንዳይቆጣ፣ የባዶ ቤት ድብርቴን ለማባረር፣ ማኅበራዊ አንቱታ እንዳላጣ፣ ደግሞስ የክት ልብሴን መቼ ልልበሰው?

በአውሮዳና አሜሪካ ወደ ቤተ ክርስቲያን/ቤተ ጸሎት የሚሄደው ሰው ቍጥር እያሽቆለቆለ እንደመጣ ይነግሩናል፣ እየሰማንም እናዝናለን:: እኛ አገር ቤተ ክርስቲያን ሂያጅ ብዙ ቢሆንም አካሄዱ እንዴት ነው የሚለው ያሳስበናል:: ረጋ ብለን መጠየቅም መጠያየቅም ያለብን ይመስለኛል::

ለመሆኑ ከነአካቴው ቤተ ክርስቲያን መሄድስ አለብኝ ወይ? ከሚለው ጥያቄ ጀምሮ የደጀ ሰላም ምልልሴ በሕይወቴ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? እስከሚለው ድረስ በጥሞና መወያየት ይገባናል እላለሁ::

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልጅነቱ ጀምሮ ወደ አይሁድ ምኩራብ ይሄድ ነበረ:: ሄዶ በቤተ መቅደስ ካሉት መምህራን ጋር ይወያይ ነበር:: "አንደ ልማዱም በሰንበት ወደ ምኩራብ ገባ" የሚለው የሉቃስ አገላለጽ ጌታችን ቤተ ጸሎት አዘውታሪ እንደነበረ በቂ ፍንጭ ይሰጣል:: ቀዳሚዎቹ ክርስቲያኖች በሳምንቱ ፊተኛ ቀን (እሁድ) ይሰበሰቡ እንደ ነበር አዲስ ኪዳናዊ ዘገባዎች ያመለክታሉ:: ተገናኝተው ምን ያደርጉ ነበረ? ቃለ እግዚአብሔር ያደምጡ ነበር፤ ይጸልዩ ነበር፤ የጸጋ ስጦታዎችን ይካፈሉ ነበር፤ የተቸገሩትን ለመርዳት ለወንጌልም ሥራ ገንዘብ ይሰበስቡ ነበር፤ ፍቅራቸውን ችግራቸውንም ይካፈሉ ነበር፤ የጌታን ራት በመቁረስ ኅብረታቸውን ያጠነክሩ ነበር ወዘተ ... ::

የመንፈሱ ማደሪያ እንድንሆን ጸጋውን ሰጥቶናልና በግንብ ያነጽነው ቤት ወይም በላስቲክ ከለላ ያዋቀርነው ዳስ ላይሆን ቤተ ክርስቲያን እኛ

ነን። እኛ ራሳችን ነን። ክርስቶስ አካላዊ አንድነታችንን ለመግለጽና ለማጽናት እንሰበሰባለን። ይህን ማድረጋችን ተገቢ ነው።

- ስንሰበሰብ የሥላሴን ሀልዎት/መገኘት እየናፈቅን ከእርሱ ጋር ተመስጠም፣ ሐሴትም ለማድረግ እየጓጓን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ። ከ 14ኛው ፕላኔት የመጣ እንግዳ ዛሬ ይሰብካል ስለ ተባለ ሳይሆን ከሰማየ ሰማያት የወረደው ጌታ በመንፈሱ ይገኛል እያልን በእግዚአብሔር ፍቅር ተጐትጉተን እንምጣ።
- የምሄደው የሰማዩን አባት ለማነጋገርና ለመስማት ብቻ ሳይሆን ወንድሞቼንና እህቶቼን ለማየት ነው ብለን እንሂድ፣ በደረስኩም ጊዜ ፍቅሬንና ናፍቆቴን ደስታዬንና ሥጋቴን ላካፍላቸው፣ ቤትስ ልጆችስ፣ ላሞችስ ጥገቶችስ እንዴት ናቸው? እያልሁ ልጠይቅ። የጸሎት አርእስት ተቀብዬ ሰጥቼም ልምጣ።
- በሕያው አምላክ ፊት በትህትናና በጥሞና በደስታና በማስተዋል ልሁን እንጂ "የአብዬ ፈለቀን ልጅ የሚሠራትን እኮ አሳጣት እስኪ ያረገችውን ጆሮ ጌጥ ተመልከት፣ ሰማ አንተ የእነገሌ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር በምን ጎጢአት እንደ ወደቀ ሰምተሃል?" ማለቴን ልተወው።
- ቤተ ጸሎት የደስታ ቦታ ቢሆንም የጥሞናና የስክነት አደባባይም ስለ ሆነ ተጀምሮ እስኪጨረስ እየዘለልሁና መንፈሴን ባዶ፣ ጸሎቴን ድጋምና ፉከራ እያደረግሁ ግልብ ሩጫ እነዳልሮጥ ልጠንቀቅ፣ መንፈሱ እንዲቀሰቅሰኝ ለውዳሴም ለትካዜም፣ ለሽብሸባም ለሰጊድም፣ እርሱ እንደሚመራኝና በጋራም እነደሚቃኘን ለመሆን ልሰናዳ። ደንብ የማስፈጸም ግዴታ የለብኝም።

ቤተ ክርስቲያን ሂያጆችና ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁልጊዜ በልማድ ጠፍር የምንቀፈደድ ስለምንድን ነው? አንዳንድ ቀን "አባታችን ሆይ" የሚለውን ጸሎት በስብሰባው መጀመሪያ ብናደርገውስ? አንዳንድ ቀን የሚዘመረው መዝሙር ሁለት ብቻ ቢሆንስ? አንዳንድ አሁድ

- ስብኩቱን ሃያ ደቂቃ አድርጎ የቀረውን ሃያ ደቂቃ በጋራ ብንጸልይበትስ? አንዳንድ ጊዜ ከአጭር ትምህርት በኋላ የቡድን ውይይት ቢኖርስ? አንዳንድ ቀን በአንድ ሰው ስብከት ፈንታ የመድረክ ላይ የሕይወት ምስክርነት ቃለ መጠይቅ ቢኖርስ? አንዳንዴ (በአንድ ቤተ ክርስቲያን እንዳየሁት) ስለ ወንጌል ስርጭት ትምህርት ተሰጥቶ ከፊሉን ጊዜ ለ ወንጌል ምስክርነት ቢወጣስ? ሁልጊዜ በልማድ ጠፍር የምንቀፈደድ ስለምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስ የሚመራን አዲስ መንገድ ካለ ለምን ዐይናችንን እንጨፍናለን?
- አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳየሁት ከስብሰባው በኋላ ብቸኞችን፣ እንግዶችን፣ ይዞ ወደ ቤት መውሰድ ምሳ መጋበዝ ወይም በሻይ ዙሪያ ልባቸውን ማዳመጥ ወይም ይህንን የመሳሰሉ ምግባረ ሠናያት የትስ ቦታ ቢሆን ቢለመድ ምን ክፋት አለበት?
- አሁድ ቤተ ክርስቲያን ሄደን ልዐሉን አምላክ እንደምንወድስ ረቡዕ ሟች ገበያው ውስጥ አምላክን የማናከብረው ለምንድን ነው? ሐሙስ ማታ የትምህርት ክፍላችን ውስጥ በፈሪሃ እግዚአብሔር የማናመሽ ስለ ምንድን ነው?
- አሁን በቅርቡ ቤተ ክርስቲያን የምትሄዱት መቼ ነው? በደስታ ሂዱ፤ በጥንቃቄ ሂዱ፤ በንቁ ልቡና ሂዱ። እንደ ቴአትር ተመልካች ሳይሆን እንደ አባታችን ቤት ልጆች የባለ ቤትነትና የአስተዋይ ተሳትፎ ልብ ይዘን እንሂድ።

Hast thou no scar?

Hast thou no scar?
No hidden scar on foot, or side or hand?
I hear thee sung as mighty in the land,
I hear them hail thy bright ascendant star,
Hast thou no scar?

Hast thou no wound?
Yet I was wounded by the archers, spent,
Leaned me against a tree to die; and rent by ravening beasts that compassed me, I swooned;
Hast thou no wound?

No wound? No scar?
Yet, as the Master shall the servant be,
And pierced are the feet that follow Me;
But thine are whole: can he have followed far
who has nor wound nor scar?
Amy Carmichael

ጠባሳ የለህም?

አንድ ቦታ እንኳ የለህም ጠባሳ?
በእግርህ ላይ የተደበቀ ወይ በጐንህ፣ ወይ በእጅህ?
አገሩ ላይ ገናና ነህ፣ ይወራልና ዝናህ
እንዴት ዕፁብ ነው እያሉ ይቀኙልሃልሳ!
ምንም የለህም ጠባሳ?
አንድ እንኳ የለህም ቁስል?
እኔን ግን ቀስተኞቹ አቆሰሉኝ፣ በታተኑኝ፣
ዛፍ አስደግፈው ገደሉኝ፣ ምኔም ሳይተርፍ በጫጨቁኝ፣
ስግብግብ አራዊት ከበውኝ ሲያሳዩኝ ቁምስቅል፣
አንተ ምንም የለህም ቁስል?
አንዳች ቁስል? አንድም ጠባሳ?
ግን፣ ኮ ባሪያ እንደጌታው መሆኑ ግድ ነው፣
የተከተሉኝ ሁሉ ተወግተዋል እግሮቻቸው፣
ያንተን ግን ሳየው ሙሉ ነው፣
አብሮኝ ሩቅ ሄዷል ትላለህ ለነፍሱ የሚሳሳ?
ያልተቀበለ አንዳች ቁስል ያላረፈበት ጠባሳ?
(አሚ ካርሚኬል እንደጻፈው ንጉሤ ቡልቻ ወደ አማርኛ እንደመለሰው)

፪. ንዳዬን ስፈትሽ

10. የክህደት እምነት 50

11.የብርሃን ያለህ! 58

12.የብዙ ዐይነቶች አንድነት 62

13.አይቴ ፍኖታ ለጉባሬ 66

14.ዕርቅ-የጥበብ መንገድ 70

15.ዘጠኝ ወንጀሎች 73

16.መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብርሃን ፍለጋ 79

17.የጠማው ንጹሑን ይጠጣ 85

18.በምን አወቅኸው 87

19.የመልእክት ያለህ! 91

20.የተቀባዮች ቅን ድርሻ 98

21.ይፈለጋል የቁጣ ችሎታ 105

22.ጉዳይ አለህ? 110

የክህደት እምነት

ክርስቲያንነት ምዝባባ ሆነ እንዴ? እንዲት ማለት ያው ስመ እግዚአብሔርን ጠርቼ፣ የሚባለውን የኑዛዜ ዓይነት አድርሼ፣ ወይም ከእናት ከአባቴ የወረደልኝን «ስሜ ነው፣ መጠሪያዬ ነው፣ አለሁበት» ብዬ ወይም ቅዳሴውን፣ መዝሙሩን፣ ቋንቋውን ጓዳውን አጥንቼ የቤተክርስቲያን አባልነቴን አረጋግጬ ሂደቱ (ፕሮሰሱ) ሲያልቅ ካርድ የምቀበልበት የክለብ ዓይነት ሆነ ወይ ማለቴ ነው።

በነገር ለመጋረፍ ዳር ዳር ማለቴ አይደለም፤ ማን ማንን ይገርፋል? ይልቁን፣ ዙሪያ ገባችንን የልቡናችንንም ዓይነት ስንፈትሽ የሚፋጠጠንን እውነታ እንድንነጋገርበት ወዲያውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ እንድንፈልግ ሜዳ ለማበጀት ነው። ይህን ያህል አሳሳቢ አነጋጋሪ ሁኔታ አለወይ የተባለ እንደሆነስ? አሳሳቢና አነጋጋሪ ብቻ ሳይሆን አስጨናቂ አስተካዥ ሁኔታ ላይ መሆናችንን መመልከት ይቻላል እላለሁ።

ማዕድ ፊታችን ሲቀርብ ቡራኬ የምንሰጥ ቢሆንም፣ ሰላምታችን እልፍ ጊዜ «ጌታ ይባረክ» በሚል መፈክር ቢያስገመግምም በጓዳ ጸሎታችን ግን «የወንድም ቀበኛዬን ዶግ ዐመድ አድርገህ አሳየኛ» እያልን የምንራገም ነን። ጸሎታችን አንዱ ታዛቢ እንዳለው የሚርት ጸሎት ሆነ።

«እሷ ዓላማዊት ናት ክርስቲያን?» እያልን የማጎበራችንን ወንበር የምንነፍግና የምንመጻደቅ ብንሆንም «ዓለማውያን» ከሆኑት ይልቅ ዓለም በደንበኝነት የምታውቀን እኛኑ ሆነ። ምክንያቱም ዓለማዊነት በዓለም ውስጥ መኖር ሳይሆን በገዳምም ሆነን ዓለም በእኛ ውስጥ መኖሯ ነው። መዝሙሮቻችን ደጋግመው "አምላኪ ጌታዬ" እያሉ የታላቁን አምላክ ስም ቢጠሩም ቁርጡን ስንጠየቅ ዕቃ አምላኪዎችና የገንዘብ ሎሌዎች መሆናችን እስከዚህም ድብቅ አልሆነም።

ሚች ስንሸኝ ስለዘላለም ቤት፣ ስለ ሰማይ መንግሥት ብናወራም የየዕለት የሕይወት ዘይቤያችን ግን ያላዩት አገር አይናፍቅም፣ የሚያቀጣኝ የጣሬውንና የእዚሁን አጥብቄ መያዝ ነው፣ የሚመጣውን ሲመጣ እናያለን። የሚል ይመስላል። አበሳችንን እያበዛሁ ክስ እያጠራቀምሁ ለማሳቀል አልፈልግም፣ ፋይዳ የሌለው አዙሪት ውስጥ ስለሚከተን። ይልቁን እንዲህ ያደረገን ምንድነው? እንዴትስ እንድንሆን ተጠርተናል? መባባል የተሻለ መንገድ ነው።

እኛ አማኞች ነን። ያመንነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ በገለጠውም የእውነት ትምህርት ነው። እርሱ ያለአንዳች የሰው ጥረት፣ ያለምንም የኛ አስተዋጽኦ እንዲያው በጸጋው አዳነን። መጽሐፍ አረጋግጦ እንደሚነግረን፦

«ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም። ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።»

በከንቱ አልባሌ ኑሮ፣ በጨለማ ድንብርብር ሕይወት፣ በታላቅ መንፈሳዊ ድንቁርናና ልበ ድፍንነት የኖረ ማንም ዐመፀኛ የአዳም ልጅ የጌታችን የፍቅር ጥሪ ሲገባውና አለኝታውን በእርሱ ሲያደርግ አመንሁህ ብሎ እጅ ሲሰጥ በዚህ ብቻ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ። እንዴት ያለ ታላቅ ጸጋ ነው! አድርግ፣ አታድርግ በሚሉ ሺህ ደንቦች ክስ ሥር የወደቅን ጉስቋሎች በጸጋ ብርቱ ክንድ ተነሣን። ምንም ምን ክፋት እንዳላደረግን ተቈጠርን። ወንጀለኛነታችን በእንከን የለሹ ክርስቶስ ላይ ሲያርፍ እኛ ጻድቃን ሆንን።

ይህ ከመዓት ያተረፈን ጸጋ ሥራው እዚያ ላይ ተደምድሟልን? ከትቢያ ካነሣን በኋላ «እንግዲህ ዕወቁበት» ብሎ ትቶን ሄዷልን? መጽሐፍ እንደርሱ አይልም። ይልቁን አዳኙ ጸጋ አሠልጣኙም እርሱ ራሱ እንደሆነ አረጋግጦ ይነግረናል።

«ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፣ ይህም ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን

ክብር መገለጥ እየጠበቅን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል (ቲቶ 2፥ 11-13)

የጸጋን ድነት የተቀበልን ሁላችን የጸጋን ሥልጠና የምንሸሸው ስለምንድነው? ጸጋ ኮ ሲያድነን ጉልበት እንደሆነን ሁሉ ሲያሠለጥነንም ዐቅም የሚሰጠን ከነስሙ ባለጸጋ ነው። እርግጥ ትምህርቱ ቆፍጣና ነው። በወለም ዘለምታ የሚያዝ አይደለም። ምን ያስተምራል የተባለ እንደሆነ ጳውሎስ እንደሚነግረን አንዱ ዋና ኮርሱ ክህደት ነው። እኛ የምናውቀው የእምነት ትምህርት ቢሆንም እምነት የሚጸናው የማይታመነውን በመካድ ነው። የነፍሴን መድኃኒት መድኃኔአለምን ሙጥኝ አልኩት፣ ታመንሁበት የሚል አንድ ምስኪን የአዳም ልጅ ወዲያው አያይ! ነፍሴን አውዳሚ መርዝ የሆነውን ኃጢአተኛነትንና ዓላማዊ ምኞትን እክዳለሁ እንዲል ጸጋ ይጠይቀዋል። በደባልነት ሊኖሩ ለማይችሉት ለእነዚህ ለሁለቱ ቁርጥ መልስ መስጠት ይጠበቅበታል፤ ለአንዱ አመኔታ ለሌላው ክህደት። በአሁድ ሚት ስብከታችን «ጌታን ለማመን የወሰናችሁ ወደፊት ኑ» እንደምንል ሁሉ «ዓለማዊነትን ለመካድ የቆረጣችሁ ወደፊት ኑና ይጸለይላችሁ» ማለት የሚገባን ይመስለኛል።

በአሁኑ ዘመን እያንዳንዱን አማኝ እና ቤተክርስቲያንን በጥቅሉ እየናጡ ካሉ ከፍተኛ ጎይላት መካከል ምናልባት ዋነኛው ዓለማዊነት ሳይሆን አይቀርም። ይህች ዓለም አሮጌ ብትሆንም፣ ዘዴዎቿ ድሮ ገና የታወቁ ቢሆንም፣ «እኔን ያየህ ተቀጣ» የሚሉ እርሷ ወግታ የጣለቻቸው አያሌ ቢሆኑም÷ዛሬም እንኳ ወይንጠጇ ያንገዳግዳል፤ ዛሬም የደጃች ድጥ ሙልጭልጭ ነው። ዓለማዊነትን ብርቱ ያደረገው ምንድነው ቢባል አባባይነቱ ነው። የደስታና የርካታ ገበታ አቅርቦ ማስጐምጀቱ፣ የባልንጀራ የአጫፋሪ ብዛት አሳይቶ ማባበሉ፣ የዋስትና የአለኝታ ዜና እየለፈፈ ማሳሳቱ፣ የክብር የዝናና የታዋቂነት ሥዕል እየሳለ ማማለሉ፣ ይህን ይህን የሚመስል ደመነፍሳዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ፍላጐታችንን ተገን

ያደረጉ ብዙ ማባበሎች እንደ ሠራዊት በፊታችን ማሰለፉ ነው ያርበተበተን። ጉልበቱ የእኛ ልዩ ልዩ ዐይነት ራብ ነው።

እንግዲያው ዓለማዊነት የማይደፍረው ወይም ቢቃጣም የማያንበረክከው የጠረቃውን ሰው ነው። በልቶ የጠገበ፣ ጠጥቶ የረካ፣ እግሩ የፈረጠመ፣ ልቡ ሙሉ የሆነ፣ ዓይኑ ያተኮረ፣ ልቡናው የሰመረ ሰው ሲያገኝ ትግሉን አይችለውም።

የዓለማዊነት መርዝ ማርከሻው እግዚአብሔር መሰልነት (Godliness) ነው ይህም ማለት እውነተኛ መንፈሳዊነት ማለት ነው።

ከእርካታ ሁሉ ምንጭ ከሰማዩ አምላክ የሚገኘውን የመንፈስ ቅዱስ ፍስሓ ያገኘ ሰው ሌላው ሌላው ፈንጠዚያ ተራና አልባሌ ይሆንበታል። በሰው ቋንቋ ከመግለጽ በላይ ከፍ ያለውን የክርስቶስን ፍቅር የሚያጣጥም ሰው የዓለም ፍቅር መናኛ ይሆንበታል። ከማርና ከወለላውም የሚጣፍጠውን የቃለ እግዚአብሔርን ማዕድ የቀመሰ ሰው እንቶ ፈንቶ የሆነውን ያሁኑን ዓለም ትዕይንት ይንቃል። በሕይወት መጽሐፍ ስሙ መጻፉን የተገነዘበ ሰው ለአላፊ ጠፊ የዚህ ዓለም መዝገብ እጅግም አይጨንቅም።

«ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፣
እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም»
«አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም
ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።»

ተብሎ የተነገረውና ይኸው ተስፋ የዘለቀው ሰው ዓለም ዋስትናና መተማመኛ እያለች የምታቀርብለትን ሁሉ ዝቅ አድርጐ ለመመልከት ጉልበት ያገኛል።

ወዳጆቼ ዓለማዊነት «ዞር በል» በማለት ብቻ የምንረታው ጠላት አይደለም፤ እኩይ መሠሪ ስለሆነ በየራባችን ቀዳዳዎች ሁሉ እየገባ «አለሁ» ይለናል እንግዲያው ሥራችን ራብን ማጥፋት ሊሆን ይገባል።

ለቅልውጥ ችግር አብነቱ ይሽው ነው። እቤት በልቶ መሠማራት። የእግዚአብሔርን አርኪነት በዝርዝር እየገባን መረዳት፣ በዚሁ ርካታ ውስጥ ለመኖር ራሳችንን ማሠልጠን። የእግዚአብሔር ቤት የእርካታ ቤት እንጂ ጠኔ ያጠላበት የተራቈተ ቤት እንዳይሆን የፍቅርን ገበታ፣ የሰላምን ማዕድ፣ የደስታን ዘይት ቶሎ ቶሎ ከመንፈስ ቅዱስ እየተቀበልን ሲጐድል እያስሞላን ማዕዱ እንዳያጥጥ፣ ራብተኛም እንዳይደነግጥ መትጋት የጊዜው ዋና ጥሪ እንደሆነ አምናለሁ።

የጸጋ ሥልጠና የራስ መግዛትም ሥልጠና ነው። ለካ ራስ መገዛት ያለበት ነገር ነው። ያልተገዛ እንደሆነ አፈትልኩ ወጥቶ አምባውን ሁሉ ያሸብራል። የሚይዘውን የሚጨብጠውን እንደማያውቅ ድንጉላ ፈረስ ሜዳውን ሁሉ ይጐደፍራል፤ አጉራ ዘለል ይሆናል። ክልክል የሚባል እንደሌለ እያመነና እያሳመነ አገሩን በማን አለብኝነት ይሞላል። የድፍረቱን ዕዳ ጽዋ እያንገሸገሸው እስኪጠጣ ድረስ ማረፊያም የለውም።

አዳኙ ጸጋ ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ እንዳወጣን ሁሉ ከራሳችንም ሊያድነን ነው የመጣው። የራስን ገናን ጉልበት የሚያንቀሳቅሰውን የሥጋ ሞተር በመንፈስ ቅዱስ ብርቱ ኃይል ሊተካው ነው የተዛመደን። ወዳጆቼ ራስ በምን ይገዛል በጌታ ቃል እውነት ብርሃን ያገኘ ጎሊና በመንፈስ ቅዱስ ዐቅም ካላንበረከከው በቀር!

«መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ---የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።»

የተባለው እኮ የራስ ፈቃድ እየገነነ በሚያቅራራበት ክፉ ዘመን ዐውድ ውስጥ ነው። እንግዲያው ወገኖቼ በራስ እንዳንሞላ፣ ናላ በሚያዞር በነገርና በምናምንቴው ሁሉ እንዳንስክር የልባችንን ማድጋ ተሽቀዳድመን ቅዱሱን መንፈስ እናስሞላው። የዘመናዊው ሰው አንድ በሽታ የዐይኑ መቃበዝ ነው፣ የዙሪያ ገባው ውልብልብታ እረፍት አልሰጠውምና ውልብ ያለውን ሁሉ ለማየት ሲዟዟር የአንገቱ ዋልታ ላላ። የገበያ ጋኔን ከሁሉ ሳይከፋም

አይቀር። የዕቃ፣ የአስተሳሰብ፣ የቁንጥ፣ የአላፊ አግዳሚ ወረት ሁሉ ልቡናችንን አቅበዘበዙት። ትክ ብሎ የሚታይ እየጠፋ አይታ የአፍታ የአፍታ ብቻ እየሆነ ሕይወት አዙሪት ጨዋታ ውስጥ ወደቀች። የጸጋ ትምህርት የትክታ ትምህርት ነው። አትኩሮ የማየት፣ ጸንቶ የመጠበቅ።

«የተባረክ ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ እየጠበቅን እንድንኖር ያስተምረናል።» አትኩሮት ለመላ አካላችን ቅርጽ ይሰጣል፤ ወደ አተኩርንበት አግጣጫ እናዘምማለን። ከሰማይ የሚመጣውን ይህን ክቡር ጌታ ስንጠብቅ የተነጣጠረ ሕይወትና ደማቅ መስመር እናገኛለን። ዓይናችንም መንከራተቱን ይገታና ሁነኛ ነገር ላይ ይውላል። የየዕለት እርምጃችን ከየስላቹ በሚያንባርቅ ጥሩምባ ሳይሆን በሰማይ ቅኝት ይመራል። ባለ ክቡር ዓላማ ገስጋሽ ሠራዊት እንሆናለን።

ጸጋው አማኞች ብቻ ሳይሆን ጠባቂዎችም ያደርገናል። ክርስቲያንነት ጥበቃ ነው፤ የዘወትር ተጠንቀቅ ነው፤ ሁሉ ነገር ያው የሆነበት ምድር ዓለሙ ሳይቋረጥ የሚጓዝበት የሰው ልጅ ታሪክ ዞሮ እየገጠመ እንደገና ዝንተዓለሙን የሚዞርበት ሽክርክሪት ሳይሆን ታሪክ ሁሉ ወደ አንድ ሁነኛ መድረሻ የሚገሠግስበት በዚህም ሳቢያ አማኙ ሰው «*በታላቁ ያለውን እየረሳሁ፣ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ*» የሚልበት ንቁ (active) ሕይወት ነው።

እነዚህ ቆፍጣና የጸጋ ትምህርቶች መነሻቸው የክርስቶስ ሞት ዓላማ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ከጸጋ መገለጥ ከጸጋም ሥልጠና ጋር አያይዞ የሚያነሣው መሠረቱና ድምድማቱ መስቀለ ኢየሱስ ነው። «ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለምንድነው?» የሚለውን ዋና ጥያቄ ለወትሮ በምንመልስበት «የሰማይ ቤት ሊያወርሰኝ» በሚል ወደፊታዊ መልስ ብቻ አያቀርበውም። የጌታችን ሞት ፋይዳ የዛሬም ጉዳይ ነው። የዛሬ

ኑሮ ጉዳይ ነው።

«ከፀመፅ ሁሉ ሊቤዠን» ሞተ ይለናል።

የፀመፀኛነት፣ የመለኮትን ሃሳብ የመቃወም የራስን ሃሳብ የማግነን የጌታችንን ትእዛዝ የመግፋት፣ የእንቢታ፣ የሽፍትነት ባሕርያችንን ሊለውጥልን ከዚህ ዲያብሎሳዊ ክፉ ዐመል ሊያላቅቀን ሞተ ይለናል።

«መልካሙን ለማድረግ የሚቀና ሕዝብ» ፈልጌ ሞተ ይለናል።

በመስቀሉ የተዋጀው ሕዝብ ሥራው ባያድነውም ከዳነ በኋላ ግን ብርቱ የመልካም ሥራ ዐርበኛ እንዲሆን ተፈልጌአል። «በጎ ሥራ የት ይገኛል? ብሎ በዓይኑ የሚማትር ሲያገኘውም በትጋት የሚፈጽመው ቅን ኅብረተሰብ የመስቀሉ ምርት ነው።

«ገንዘቡ የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ» ሞተ ይለናል»

የክርስቶስ ሞት አንድም የግዢ ውል ነው። በደሙ ስለገዛን የባለቤትነት ሙሉ መብት አለው። ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ ሕዝብ፣ ለወደደው ዓላማና ተግባር የሚያሰማራው ሠራዊት ፈልጌ ነው የሞተ። ታላቁ ጠቢብ በዚህ ሙዐለ ሕይወት (ኢንቨስትመንት) ሊከስር አይሻም። የተባለው ሁሉ ተብሎ እንደ አንድ የክርስቶስ ተከታይ እንደ ቤተክርስቲያንም ልናስብባቸው የሚገቡ ሁለት ዋና ነገሮች ይታዩኛል። የተያያዙም ቢሆን በየስማቸው ቢጠሩ ይወዳሉ።

መጀመሪያ ነገር እስከዛሬ ስንማር ስናስተምር የቆየነው ስለማመን ስለመቀበል ጌታን እሺ ስለማለት ነበረና አሁን ደግሞ ጨምረን ክህደትን እንማር፣ እናስተምር። ያው እንደተባባልነው በወደር የለሹ ክርስቶስ ላይ ያለንን እምነት ለማጽናት ተፎካካሪ ገናኖችን ልክ ልካቸውን ነግረን ቦታቸውን እናሳያቸው፣ ለአንድ ጌታ ሎሌነት ማደራችንን እናስታውቃቸው ብዙ የሚካዱ ጎሳዊ መሲኃን (እንደዚህ ሲባል ሥጋ የለበሱ ሰዎችን ብቻ ለምን እናስባለን) ከጽድቅ የሚያፈናቅሉንን የራሳችንን አጓጉል ምኞቶችና ዐመፀኛነቶች እንዳሉ ለባልጀሮቻችን ሁሉ እንንገር።

ክፉውን ደግ ደጉን ክፉ የሚያደርገውን፣ ክቡሩን ቀሊል ገለባውን ፍሬ የሚያስመስለውን የዓለሙን የተዛባ ሥራተ እሴት አንቀበልም ብለን እንካድ።

ሁለተኛ ነገር ይህን ዓለም ማሸነፊያ ዮሐንስ እንደነገረን በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ያለ እምነታችን ነውና በእርሱ ያለንን እምነት ስንኖርበት የሚያዩ ሁሉ «ውይ እንዴት ያማረ እንዴት የሰመረ ሕይወት ነው» እንዲሉ በጌታ ዘንድ ያለውን ሀብት እንጠቀምበት። «ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ» እንደተሰኘው ተረት እንዳይሆንብን ከመለኮታዊ ጸጋው የሚመነጨውን ደስታ፣ ፍቅር፣ ሰላምና ርካታ የሚያጣጥም ምላስ እናዳብር። ጤነኛ አፒታይት (የምግብ ፍላጐት) እንዲፈጥርልን የነፍሳችንን ጌታ እንለምነው።

እናምናለን በመስቀሉ
እንቆማለን በወንጌሉ
ሕያው ሆኖ ይሠራል
አልተለወጠም ቃሉ።

የብርሃን ያለህ

በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ዘመነ መሳፍንት የሚባል ጨርቁን ጥሎ ያበደ ዘመን ነበር። ሰው ሁሉ የሚፈልገውን ዐይነት አምላክ እያበጀ ጣዖት ባራኪ ቄስ እየቀጠረ በየጓዳው የሚጐነበስበት። አንዲት ሴት በወስላቶች ተደፍራ ሲነጋ ደጃፍ ሥር የምትሞትበት፣ የሚች ቁባቱን አካል በሰለት ቆራርጦ አስራ ሁለት ትንንሽ አድርጐ እዩልኝ ስሙልኝ የሚባልበት፣ በእጁ ያበጀውን ጣዖት ዘራፊዎች ሲነጥቁት "የሠራሁትን አምላኬን ወስዳችሁ ምን የቀረኝ ነገር አለ?" እያለ የተሰረቀ አምላክ ለማስመለስ ግብግብ የሚገጠምበት፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያደረበት አንድ መስፍን ራሱን ለዝሙት አዳሪ ያስተነተነበት፣ በቃልኪዳኑ አገር ላይ የባዕድ አምላክ፣ የበዓል መሠዊያ አፈረስህ ተበሎ ይሙት በቃ የተባለበት።

የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ የዚያን መላ ቢስ ዘመን ገጽታ ሁለት ጊዜ በጠቀሰው በአንድ ጠቅላይ ንግግር ስብስብ አድርጎ ገልጾልናል "በዚያን ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።" መሳ 17:6 እና 21:25

ብርሃን ሰጪ፣ አመልካች መሪ፣ ብያኔ ሰጪ፣ ደንብ አውጪ፣ ክርክር ቆራጭ ስላልነበር የተገኘው ምርጫ ሰው ሁሉ የራሱ ዳኛ፣ የራሱ ንጉሥ፣ የራሱ አስተማሪ መሆን ነው። ስለዚህ ለባዱው የተተወው የሰው ልጅ ሰካራም ስሜቱ እንደነዳውና ስግብግብ ነፍሱ እንዳራወጠው በየልቡ አምባ ለገነነው ፈቃድ ይገብር ነበር። የጨለማ ምስፍና ጣራ ነካ።

ነገሩ የትጋ እንደተበላሸ ሲጠቁም ጸሐፊው በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ የአደጋው መነሾ ማይምነት ነው ይለናል፤ የፊደል ሳይሆን የእግዚአብሔር። "ኢያሱ በነበረበት ዘመን ሁሉ ለእስራኤልም ያደረገውን ታላቁን የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ባዩት ከኢያሱ በኋላ በነበሩ

ሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አመለኩ።" ነገሩ ግን እንደዚህ አልቀጠለም፦

"ከእነዚያም በኋላ እግዚአብሔርን ለእስራኤልም ያደረገውን ሥራ ያላወቀ ሌላ ትውልድ ተነሣ" ከዚያች ቃል በኋላ ያለው የታሪክ ዘገባ ባብዛኛው የውርደት ጥድፊያ የሞላበት የክፋትና የክፉት ቅጣት፣ የቅጣት ጩኸትና የአፍታ ትድግና፣ የመልሶ ክፋት፣ የመልሶ ሥቃይ ጉዳና ነው።

አለማወቅ ክፉ ነገር ነው፤ በተለይ እግዚአብሔርን አለማወቅ። በስሚ ስሚ፣ በተለምዶ፣ በባህል፣ በይመስላል መንቀሳቀስ ሕይወትን ያለ መሪ በባህር ላይ የምትዋልል ጀልባ ማድረግ ነው። ያገኘን ሁሉ ሸቀጡን የሚጭንብን የአርባ ጌቶች አጉብዳጅ መሆን ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ከእኛ ልቡና ምጡቅ መሆኑና ሊደረስበት የማይችል መሆኑ እውነት ነው። ሥራውንና አደራረጉ በቀመር ተሰልቶ የማይገኝ ረቂቅ መሆኑ እውነት ነው። ይህ ስለሆነ ግን ጌታ አምላክ ራሱን ለሾላ በድፍን ግምት አልዳረገም። ወይም አንዳንድ ተራቃቂዎች "በየትኛውም መንገድ ብትሄድ አታጣውም፣ አንተ ነው ያልኸውን መሆኑ አይቀርም" እንደሚሉት ለሰው ልጅ ነሲብ ውርወራ ዒላማ አድርጎ ራሱን አላቀረበም።

ከማይደረስበት ጥልቅ ጥበቡ ከፍሎ፣ ከማይመዘነው የሥራው ስፋት ጨልፎ፣ የማንነቱን ጭላንጭል (በእርሱ ዐይን ጭላንጭል ቢሆን ለኛ የብርሃን ጉርፍ ነው) በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በተመዘገበ ሰነድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰጥቶናል። ቃለ እግዚአብሔር ብዙ አስተዋዮች እንደተናገሩት የእግዚአብሔር የራስ በራስ መገለጥ የማንነቱ ምስክር ነው። ይህን ሰነድ ያዘጋጀው መንፈስ የሰከነ መምህራችን ነው።

እንግዲያው እኛ ዘንድ ያለው ዝብርቅርቅነት ከየት መጣ? ባንድ ታዛ ሥር እያደርን በቤቱ ውስጥ እያወካን መደማመጥ የጠፋብት ባቢሎናዊ

ድንግርግር ላይ ምን ጣለን? አንዱን የመድኃኒታችንን ስም እየጠራን እኩሌታው በዚያ ስም የሰው ሕይወት ሲገነባ ሌላው ያንኑ ስም ተጠቅሞ ሕይወትና ቤት እያነካከተ የሚጥለው ምን ሆነን ነው? በደመነፍስ እንኳ ክፉትነቱ የሚታወቅ ክፉ ነገር እያደረግን "ጌታ አዝዞኝ ነው" የሚል ድፍረት እንዴት ተገኘ?

ወንድሞቼና እህቶቼ መንፈሳዊ ማይምነት የልቡናችንን ዐይን የጋረደው ይመስለኛል። ስሙን በአስር ቁልምጫ ብንጠራውም ጌታን ኢየሱስን ማወቃችንን እንጃ! የመጽሐፍ ቅዱስ አርበኞች ብንመስልም ለመጽሐፉ የከንፈር ግልጋሎት እንቸረው እንደሆነ እንጂ በትኩረት የምናየው አይመስለኝም። የክርክራችን መቁረጫ አንቱ የተባሉ ሰው የተናገሩት ወይም "ታይቶኛል" ተሰምቶኛል" ብሎ የልቡን አሳብ የሚያወራልን አንድ ሰው ወይም "እንዴ! ሁሉም እንዲህ ነው የሚያደርገው አታይም?" የሚል የዙሪያ ገባው ችሎት እየሆነ መምጣቱ ያሳስባል።

በተቀረጸ ፊደልና በተጠረዘ መጽሐፍ አሳቡንና እቅዱን አደራረጉንም የገለጸልን አምላክ ሕያው አምላክ እንደሆነ አምናለሁ። ስለዚህ በየልባችን ማነደር መንፈሳችንን በማንቃት በወንድሞችና በእህቶች በኩል መልእክቱን በማቀበል ዛሬም እንደሚናገር አምናለሁ። ክርስቶሳዊው ማነበረሰብ የታሪክ ዝክር ባለዐደራነት ብቻ ሳይሆን ዋና ጥሪው የታሪክ ሰሪው ጌታ ምስክርነት ነው። የተባለው ሁሉ ተብሎ ግን በልቡና ጓዳ በራእይ በትንቢት በሕይወት ገጠመኞች ሁሉ የሚቀርበው መልእክት አሳብ ወይም ትምህርት የቀዳሚውንና የባለሥልጣኑን ሰነድ የእግዚአብሔርን ቃል ያከበረ፣ ለዚህ ዋና መገለጥ የሰገደ በዚህ ጥቅጥቅ የእውነት ማጥለያ ላይ ሰፈፉ የተጠነፈፈ ካልሆነ ታላቅ አደጋ እፊታችን አለ። ይህ ጉዳይ ጊዜ ማሳለፊያ ጨዋታ ወይም ነገር ማሳመሪያ አይደለም። ወዳጆቼ ጉዳዩ የሞት የሽረት ጥያቄ ነው። የሐሰት

ትምህርትን፣ የሐሰት ትንቢትን ሐሳቄ ምሁራንን፣ የስህተት አሠራርንና አደጋ በሽለላና በቀረርቶ ወይም በማባበልና በማረሳሳት ማስወገድ አንችልም። በሁለት ወገን ከተሳለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለውን ቃል እግዚአብሔርን ዳኛና ጠበቃ መምህርና መካር ማድረግ አማራጭ የሌለው ተግባራችን ነው። የታየንን የተሰማንን ሌሎች ሰዎች ያዩልንን ቅዱስ ቃሉ ሚዛን ላይ ለማስቀመጥ ለምን እንፈራለን? በጌታ ስም የሚናገሩትን ሰዎች መመርመር አጉል ድፍረት እየመሰለን ነው? የተናገሩት ነገር ተፈትኖ ቢወድቅ ስሜታቸው ይጐዳል ብለን ሰግተን ነው? ወዳጆቼ ሰማይንና ምድርን ከሠራ ፈጣሪ በላይ ማንን ልንፈራ ይገባል? በመስቀል ላይ ከሞተልን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ በላይ ለእኛ መልካም የሚያስብ፣ መልካምም የሚናገርልንስ ማን ይገኛል? ምርመራ ና ፍተሻ ለማድረግ አንታክት። ይህን ስናደርግ ግን በማስተዋል እናድርገው።

በቃሉ በትር አንደባደብ፣ በቅዱሱ ቃለ ሽሙጥ አንናገር፣ ቃሉን የእኛ ብቻ እንደሆነ ዐይነት ሌሎችን ለማባረር አንጠቀምበት ይልቁን - በቃሉ እንመካከር እንወቃቀስ የቃሉን ማዕድ ዘርግተን እንጐራረስ የዛለውን ጉልበት እናበርታበት የተጣመመውን እንቅናበት፣ ያናከሰውን እንፈውስበት።

"የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ አውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል— እንደ ተማሪዎችም ትሰማ ዘንድ ጆሮዩን ያነቃቃል" ኢሳ 50:4-5

ቃሉ የብርሃን ምንጭ ነው፤ እንይበት፤ እንዳኝበት።

የብዙ ዓይነቶች አንድነት

«የእድገት ድምድማቱ አንድ ዓይነትነት ሳይሆን ስምምነት ነው» ብለው ያሉት የመቶ ዓመቱ ሽማግሌ የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ጳጳስ ነበሩ። ብዙ ዓይነትነት የእግዚአብሔር በረከት ነው እንጂ ፍዳ አይደለም። ፍዳው የሚመጣው የዓይነታችንን ብዛት የጠባችን ምክንያት ያደረግነው ጊዜ ነው። ባለ ብዙ ቀለም የቅጠል ዓለም ባለ ብዙ ጣዕም የፍራፍሬ እንቅብ አድርጎ ይህቺን ዓለም የፈጠራት አዋቂ አምላክ ነው። ልዩ ልዩነት መርገም አይደለም። ሙሉ በረከት የሚገኘው ይህን ልዩ ልዩነት ሳናጠፋ፣ ለአንድ ዓላማ አስማምተን መምራት የቻልን ጊዜ ነው። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ አንድ ዋና ዓላማ፣ አንድ ብቸኛ ተልዕኮ እንዳላት ግልጥ ነው መተኪያ የሌለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች ልብ ውስጥ እንዲነግሥ በዚሁም ንግሥናው የጎብረተሰብ አካሄድ እንዲለወጥ። ይህንን እንድናስብ፣ ለዚህ እንድንፀልይ፣ በዚህ መስመር ተሰማርተን እንድንሠራ ታዘናል። እኛ ሁላችን የአንድ ቁርጠኛ ጥሪ ተሰላፊዎች ነን። የሁላችን ግሥግሣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ባንዲራ በየስፍራው ለመትከል ነው።

ይህ ታላቅ ጥሪ ከባድ ፍልሚያ የሚጠይቅ መሆኑን ማንም አይስተውም። በጦርነት ጊዜ የሚያስፈልጉ ብዙ የባህርይ፣ የቁሳቁስ፣ የችሎታም ዝግጅቶች ቢኖሩም በአለቃው እዝ ሥር ሆኖ በስምምነት እንደመንቀሳቀስ ወሳኝ ነገር ያለ አይመስለኝም። ጦር ሜዳ ላይ አንድነት የሞት የሽረት ጥያቄ ነው። ቤተክርስቲያን ታላላቅ ምርኮዎች እንድታስገባ፣ የጌታችን ስምገንኖ እንዲወጣ ከፈለግን ምንም ሌላ አማራጭ የለንም በአንድነት ቆመን፣ ጦር በሳሳበት እይተካን፣ ግንባሩ በበረታበት ደጀኑን እያጠናከርን አንዱ የሌላውን እይታ ሳይከለክል፣ ጋሬጣ ሳይሆን፣ በውጊያ የዛሉትን እያቀናን የቆሰሉትን ተሸክመን፣ የአንድ ጦር አባሎች መሆናችንን

ካላረጋገጥን ድል የሩቅ ተስፋ ብቻ እንዳይሆንብን ያሰጋል። የጦራችን ስለት ወደ እርስ በርሳችን ሳይሆን የሕዝባችንን ልቡና እያጨለመ እውነትና ተስፋ ወደሚተማው ሳይሳሳ ወደ ሚረፈረፈው ክፉ ጠላት መዞር አለበት። የአንድነት ውጊያ ነው የሚያዋጣን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታዋቂው ጸሎት እንዲህ አለ። «አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ..... እነሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆን ዘንድ እለምናለሁ።»

ይህ እጅግ አሳሳቢ ጸሎት ነው እንደ ጌታችን አመለካከት እኛ አንድ ካልሆንን ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛነት ለማመን ይከብዳታል ማለት ነው። ይህ ጉልህ እውነት ነው። አንዱን ስም እየጠራን በአስራ ሦስት ልብ ስንጠላለፍ ለዓለም የምናሳየው ሥዕል የአንድ መቅደስ ሥዕል ሳይሆን መቶ መሸለኪያ ያለው የሌቦች ዋሻ ነው። ሰዎች እኛን ባያምኑን አይገርምም ይሆናል። ጌታችን እንዳይታመን እንቅፋት ስንሆንበት ግን እጅግ አሳዛኝ ነው። የአንድነት እንቅፋቶች ምንድን ናቸው? ለጊዜው ሦስት ይታዩኛል።

አንደኛው ከልክ ያለፈ ግለኝነት ነው። «ከልክ ያለፈ» ማለቴ የራሳችን ማንነት ከናካቴው አይጠፋምና፣ መኖሩም ይጠቅማልና መተናፈሻ ለመስጠት ነው። ነገር ግን ሁልጊዜ ስለራስ የግል ስጦታ፣ ስለእኔ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለእኛ ቡድን፣ ስለ እኛ ብሔር፣ ስለእኛ ራእይ የምናስብ የምናወራ፣ የሆነ አየሩ ይታፈናል፤ ባልንጀሮቻችንን በሰባት በተገመደ ሽቦ አጥር ውስጥ እናስራቸዋለን። አንድነት የሚፋፋው የሌሎችን ስጦታ፣ የሌሎችን ቤተክርስቲያን፣ የሌሎች ሰዎችን ቡድን ወይም ብሔር፣ የሌሎችን ራእይ ለማወቅ ስንጓጓ፣ ለማክበር ስንሞክር፣ ለማበልፀግ ስንሰናዳ ነው። «እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትህትና ይቁጠር» ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ መክሮናል።

ሁለተኛው የአንድነት ደንቃራ አገልጋዮቻችን መሪዎቻችንን እንደ

ሰዎች ማየት ትተን የሰማይ ከዋክብት ማድረግ ነው። እነርሱ ደማቅ ከዋክብት ከሆኑ እኛ በእነርሱ ዙሪያ እያጨበጨብን የምንዞር ቢራቢሮዎች ነን። «ዘራፍ የጳውሎስ አሽከር» እንደማለት ነው። ይህን በታዋቂ አገልጋይ ዙሪያ መሽከርከርና ሌሎችን ማጣጣል በዚህም ምክንያት መከፋፈልን ሐዋርያው ጳውሎስ ብርቱ የተግሣጽ በትር አሳርፎበታል። «ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰቀለን?.... አጵሎስ ምንድነው? ጳውሎስ ምንድነው?.... አገልጋዮች ናቸው....ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎች ይቁጠረን» በማለት የሰው ሁሉ ዐይን ወደ ልዑል እግዚአብሔር ብቻ እንዲነሣ ተማጠነ። መሪዎቻችንን ከማክበርና ከመታዘዝ በላይ ወደ ልዕለሰብእ ደረጃ ካሸጋገርናቸው በጤና የማሰብ ሥራችን ተጓሳለ ማለት ነው። የእነርሱን ጉድለት አንሥቶ የሚናገር ሰው ቢያጋጥመን፣ ወይም ከእነርሱ አሠራር የተሻለ ቢገኝ ክሌሎች ጋር ልንጣላላቸው ነው። ይህ «በሽተኛ ሎሌነት» ትልቁን አንድነት ያፋልሰብናል።

ሦስተኛው የአንድነት ሰላቢ እንዝህላልነት ነው። ለምንናገራቸው፣ ለምናደርጋቸው ጥቃቅን ለሚመስሉ ነገሮች ጥንቃቄ አለማድረግ። ስለ ጎረቤታችን ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ሥራ ባልደረባችን፣ ስለ አገልግሎት አጋራችን፣ ስለ ሌላው ብሔር /ጎሣ/ አባል አፋችን አድጦት የሚወጣው ሁሉ ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ አውዳሚ መዓት ነው። «የእነንትና ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያደረጉትን ጉድ ሰምተሃል?» «ይሄ ብሔር እንዴት ዓይነት ጠማማ መሰለህ?» «የእገሌ ቤተ ክርስቲያን ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምሩት ነገር አይጥመኝም» «ለጊዜው በዚህ ሥራ ይተባበሩን እንጂ እነርሱ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ርግጠኛ አይደለሁም» ወዘተረፈ። መጽሐፈ መክበብ የሞቱ ዝንቦች የተቀመመውን ሽቱ እንደሚያገሙት ነግሮናል። ያለ ማስተዋል የተወረወረ አስተያየት አንድነታችንን ያክፋል። የአንድነት መንገድ የጥንቃቄ መንገድ ነው።

አብረን ለመኖር እና አብረን ለማገልገል ተጠርተናል። አንድነት እኛ

ስንፈልግ የምንይዘው ሳንፈልግ የምንተወው የኑሮ አማራጭ አይደለም። የእግዚአብሔር ቤተሰቦችና የኢየሱስ ክርስቶስ ሎሌዎች ከሆንን፣ ይኸው ሁኔታችን አንድነት ጠሪ ነው። «የአባቴ ልጅ ወንድሜ ነው፣ ግን ንግግር የለንም፣ የአንድ ጌታ ባሮች ነን ግን አንግባባም» ማለት የእርስ በርስ ውድመት ጉዳና ነው።

የአንድነት ጉዞ እንደ ንግግራችን ቀላል እንዳልሆነ ይገባኛል። ቅዱስ ጳውሎስም ይህ ስለገባው አንድነትን ለመጠበቅ ብርቱ ዘበኝነት ያስፈልገዋል ብሎናል «የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ» ብሎ ለኤፌሶን ምዕመናን የጻፈው ታላቅ ምክር ነው «የዚህ የአንድነት ጥበቃ የዘበኛ ትጥቆች ምንድናቸው?» የተባለ እንደሆነ እዚያው መጽሐፍ ላይ ተዘርዝረው ይገኛሉ የትሕትና ቀበቶ፣ የፍቅር ባርኔጣ፣ የሰላም ማሠሪያ፣ የትዕግሥት ብርድ ልብስ፣ የየዋህነት መነጽር.... እየተዋደድንና እየተስማማን እንድናገለግለው እግዚአብሔር ይርዳን።

አይቴ ፍኖታ ለጎባሬ
(የአንድነት ጉዳናዋ ወዴት ነው?)

ስለ አንድነት ከምንሠራው የምናወራው ይበልጣል፣ ቢሆንም የግብዝነትን ገፈት እየሸሸን የእውነት ቃልን ንጹህ ወይን አብረን ከመጠጣት ልናፈገፍግ አይገባም።

ጠብና መለያየት ጌጥ አይደለም፣ የርግማን ምልክት ነው። እግዚአብሔር የተቆጣው ሕዝብ ነው የሚለያየው፣ የሚጣላው፣ ልቡ የሚራራቀው።

"... ምድርን በእርግማን እንዳልመታ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ወደ አባቶች ይመልሳል" ብሎ በሚልክያስ ነግሮናል። አንድነት በረከት ነው፣ የእግዚአብሔር የማያቋርጥ፣ የማይነጥፍ ጸጋ የሚፈስበት ወንዝ ነው፣ ብዙዎቻችን ስለ በረከት፣ ስለ ቅባት፣ ስለ ኀይል፣ ስለ ትኩስነት (Freshness) እንጸልያለን፣ በቤተ ክርስቲያናችን በረከት እንዲወርድ እንመኛለን። መጽሐፍ አረጋግጦ የሚነግረን ይህ ጸጋ ባስተማማኝ ሁኔታ የሚሠራው በኅብረት በአንድነት በተቀመጡ ሰዎች መካከል እንደ ሆነ ነው። ምናልባትም በዚህ በአገራችን የበረከት ዝናብ በቁጥቁጥ የሚዘንበው፣ ኧ! ብሎ ያላጥለቀለቀን ልባዊ የሆነ በጽድቅ የተገነባ አንድነት በሰፈው ስላልተገኘ እንደሆነስ?

አንድነት ምንድን ነው? የቤተ ክርስቲያኖች አንድነት እንዴት ይገለጻል?

- አንድነት በልብ አሳብ ተስማምቶ አብሮ መጸለይ ነው፤
- የሌሎችን አገልግሎት በቅንነትና በትሕትና መቀበል ነው፤
- ያኛው ቤተ ክርስቲያን እያደገ ሲመጣ፣ በደስታ አምላክን ማመስገን ነው፤
- ያኛው ቤተ ክርስቲያን ችግር አጋጥሞት ሲበጠበጥ ማልቀስ መቻል ነው፤

- ስለ ሌሎች በሹክሹክታ መናገርን መተው ነው፣ "አንተ የእነ እንቶኔ ቤተ ክርስቲያን ጉድ ታውቃለህ? ..."
- እኔ በሌላው ቤት ሌላው በእኔ ቤት ያለ ጥርጣሬና ፍርሃት ገብተን መውጣት መቻል ነው፤
- ያኛው ቤተ ክርስቲያን ከኔ ቤተ ክርስቲያን የተሻለ ነው ብሎ ማሰብ መልመድ ነው።

ምን አንድ ያደርገናል?

ወዳጆች በአንድ ልብ ሆኖ መኖርና መሥራት ጥረት እንደሚጠይቅ ባውቅም ባንድ አቅጣጫ ሲታይ ምናልባት የአንድነት ጎዳና ይህን ያህል ውስብስብ አይደለም፣ እያንዳንዱ ሰውና ቤተ ክርስቲያን ማእከላዊና ትልቅ አድርጎ በፊቱ ያቆመው የሚሰግደውም ለእግዚአብሔር ልጅ ለጌታ ለክርስቶስ ከሆነ ስለ አንድነት ብዙ ሳናስብ አንድ እንሆናለን። ዐይኖች ሁሉ ወደዚህ ማእከል ያተኩራሉ፣ ጆሮዎች ሁሉ ከአንድ ምንጭ ይሰማሉ፣ የንጉሡ ገበታ ላይ እንገናኛለን፣ እጆች ሁሉ ይህን ጌታ ያገለግላሉ፣ የእግሮች ግሥግሣ ባንድ መሥመር ላይ ይሆናል።

አሁን የምናየው አበሳ ግን ማእከሉ ሌሎች መሆናቸው ነው። ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያናችን አስገራሚ ታሪክ፣ የምንመካባቸው "ድንቅ አገልጋዮችን" ያከማቸነው የጸበረ የሰው ኀይልና ንብረት፣ ሌሎች የሌሏቸው እኛ ብቻ ያሉን አንዳንድ ልምምዶች፣ የሚያስቀናው የአሠራር ስልታችን፣ አደረጃጀታችን፣ የትምህርታችን ጥራት፣ ታዋቂነታችን፣ ትልቅነታችንና አስፈሪነታችን ወይም ትንሽነታችንና ምርጥነታችን ወዘተ ...። በነዚህ ላይ የምናተኩር እነዚህኑ የምንለፍፍ ከሆነ በ5፣ በ10 ሳይሆን በመቶና በሺህ ብንበጣጠቅ የሚገርም አይሆንም፣ ምክንያቱም መገኛ የሌለው የራስ ወዳድነት ግልቢያ ጀምረናል!

"ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ እንጂ እራሳችንን አንሰብክምና" ተብሎ መጻፉ የአንድ ጌታ ሉላልት የመሆን ጥሪ እንዳለን ያሳያል።

ወዳጆቼ መለያየት ድህነት ነው፣ "ሁሉ የእኛ" ሆኖ ሳለ አንዳንድ ሙዳ ሥጋ በጭቀን አጥንቱን እንደማያጋራ ውሻ በየጥጋችን የምናጉረመርም አስቂኞች ሆነናል።

"ጳውሎስም ቢሆን፣ ኬፋም ቢሆን፣ አጵሎስም ቢሆን ሁሉ የእናንተ ነው እናንተም የክርስቶስ ናችሁ፣ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው" የተባለበትን የአንድነትና የብልጥግና መሠረት ለቅቀናል።

አንድነታችን የጽድቅ እንጂ ምድራዊ ጥቅም ለማግኘት የመስገብገብ አይሁን። ለመተባበርማ ሌቦችም የዝርፊያ ማኅበር ያበጃሉ። በጽድቅ ጎዳና ስንሄድ መስመሩ ላይ እንገናኝ ነው የምለው። መንገዲቱ ጠባብና አንዲት ናትና በምንም ዐይነት አንጠፋፋም። የየግል ጥቅም ስናነፈንፍ የነጠላ ክብረታችንን ስንፈልግ ነው በአሳቻ መንገድ ገብተን የምንጠፋ፣ ወዲያውም ባለ ሃያ ልብ ሆነን የምንቀር። ሃያ ፍላጎት ካለ ሃያ መስመር የማንቀድበት ምክንያት የለም። ርቱዕ የሆነችው ሰው የማትፈራው በራሷም ላይ ለመፍረድ የማታመነታው የትሑታን ጎዳና የጽድቅ ጎዳና ናት። እግራቸው የቀና ሁሉ በዚያ ማለፋቸው አይቀርምና መናኸሪያችን የንጽህና አደባባይ ይሆናል። አንድነት የፍጥረታችን የአካሄዳችንም ውጤት ይሆናል። እኛ ለእውነት ስንጨነቅ ከእውነተኞች ሁሉ ጋር አንድ መሆን ቀላል ይሆናል።

ሥላሴ ውስጥ ያለው የአንድነት ውበት ምንድን ነው የተባለ እንድሆን ትሕትና ነው መልሱ፣ እየራሳቸው ማንነት ቢኖራቸውም፣ ስም ቢኖራቸውም፣ አንዱ ለሌላው ቦታ መስጠቱ ዝቅ ብሎ ማገልገሉ ያልተጋፋ ያልተፎካከረ የአንድነት ግዙፍ ምሳሌ ሆኖናል። ጌታ ኢየሱስ የለመነልን አንድነት ሞዴል ይኸው ነው፣ ባልንጀራዬ ማለት፣ ያኛው ቤተ ክርስቲያን ከእኔ ይሻላል፣ ብሎ በትሕትና

ማሰብ የውርደት ሳይሆን የክብር መንገድ ነው፣ የእስራት ሳይሆን የትልቅ ነጻነት መንገድ ነው።

"በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ አደረገው" ይለናል። ወዳጆቼ ክብራችንንና መብታችንን ከወንድማችን ጉሮሮ አንቀን አናስተፋ፣ እግራቸውን በማጠባችን ደንግጠው እንዲወዱን መንገድ እንክፈትላቸው። ይሄንን ጥበብ በምን ትተኩታላችሁ!

አንድነት አይታመምም ወይ ቢባልስ? ብዙ ጊዜ እንጂ፣ ግን ታክሞ ይድናል። አስታማሚ ከተገኘ፣ በሰዓቱ እየተጠበቀ መድኀኒት ከተሰጠው ለምሳሌ አንዱ ኪኒን ይቅርታ ነው፣ አንዱ መርፌ እውነተኛ መወቃቀስ ነው፣ አንዱ መታሻ የጥሞና ውይይት ነው። ከታከመ ይድናል፣ እንኳን የሰው ጠብ የማዜሩም መድኀኒት አለው። "አዳም በበደለ መድኀኒአለም ክሶ ..."

ዋናው ነገር ተስፋ አለመቁረጥ ነው፣ 489 ጊዜ ይቅር ብየሃለሁ አንድ ዕደል ብቻ ቀረችህ አለማለት ነው፣ እንደ ሰማይ አምላክ የምሕረት አውድማ መሆን ነው።

ደግሞ ሌላ ነገር፣ ቀረብ ብለን መተዋወቅ ነው፣ ምናልባት ለካ እዚያም ቤት ቡና የሚጠጡት እንደ እኛ በነጭ ስኒ ነው፣ እኔስ በጠላ ጣሳ መስሎኝ! ለካ መጽሐፍ እያዩ ቢጸልዩም እግዜሩ ይሰማቸዋል! ለካ ሲጸለይ የሚያለቅሰው ሰው የጌታ ውለታ በዝቶበት ነው እኔማ አንጎሉ ጤነኛ አልመስለኝም ነበር ለካ ...

«ዕርቅ - የጥበብ መንገድ»

እኛ በክርስቶስ የምናምን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች አንድነትና ስምምነት አጥተን ስንጣላ የሚሆነው ነገር ምን ይመስላል ቢባል፡ በታላቅ ጥበብና ጥንቃቄ በተሳለው የሸራ ቅብ ላይ አሮጌ የቀለም ጣሳ ቀድደን ድፍድፉን ቀለም ማፍሰስ ነው፣ ለመብላት ያሰፈሰፉ ሰዎች ዐይኖች በሚቋምጡት በወግ የተሰናዳ የእንጀራ ገበታ ላይ አሸዋ መድፋት ነው፣ ለድል አንድ ምዕራፍ የቀረውን ሯጭ ቋንጃ በስለት መበጠስ ነው። ጠብ የዐለም ሁሉ ሰቀቀን ነው። በእግዚአብሔር ቤተሰብ መካከል ጠብ ጉልበት ካገኘ ለምድርዓለም የተሰጣት የተስፋ ብርሃን ተስለመለመ ማለት ነው።

ምን ያጣላናል? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ቢሆንም ለጊዜው ለምን እርቅ ያስቸግረናል? የሚለውን መመራመር ሳይሻል አይቀርም። የዕርቅና የአንድነት እንቅፋቶች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ፈጥጠው የሚታዩኝን አራት ጭራቆች ብቻ ላንሳ።

አንደኛው ጠብ የሚያመጣውን አደጋ አለመፍራት ነው። «የመጣው ይምጣ» የሚል ሥጋዊ ድፍረት ነው። «እሺ ይህ ነገር ውሎ ያደረ እንደሆነ ከፉ ጣጣ አለው» ሲባል። «ምን ይመጣል ቢበዛ መሰያየት ነው» የሚል መንፈሳዊ ድንዛዜ ከክርስቶስ የአንድነት ጸሎት እንዴት የራቀ እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን እንዲህ ብሎ ለመነው።«አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ....እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።» ይህ እጅግ አሳሳቢ ጸሎት ነው እንደጌታችን አመለካከት እኛ አንድ ካልሆንን ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛነት ለማመን ይከብዳታል ማለት ነው። የተራቀቀ የወንጌል ስርጭት ስልታችን፣ የፈረጠመው አደረጃጀታችን ወይም የካበተ ልምዳችን ሰውን ሊያሳምን አይችልም ማለት ነው።

ሁለተኛው፡ በራስ አመለካከትና አቋም መዋጥ፣ የሌላውን ለማየት አለመቻል፣አለመፈለግም፣ የሌላውን ወንድም ወይም ወገን የአስተሳሰብ መንገድ መናቅ፣ ማጣጣል፣ መጠራጠር፣ አዘቦቱ መተርጐም፣ ይህንንም የሚመስል የራስ አስተሳሰብ ደሴተኛነት ነው። በራስ እንደመታሰር ያለ ግዞት የትም የለ።

«ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር» ያለው ሐዋርያ ምሳሌ አድርጐ የሚያቀርብልን ራሱን ባዶ ያደረገውን ኢየሱስን ነው። የባልንጀራውን የአባቱን ፈቃድና አሳብ አስበልጦ ወደደ፣ የሚያስከፍለውን ከፍሎ የኋላ ሽልማቱን በክብር ተጐናጸፈ። የሌሎችን አሳብ መቀበል ኪሣራ ከመሰለን የኢየሱስ ወንድሞች ነን ለማለት እንዴት እንደፍራለን?

ሦስተኛው፡ «አንዴ ብያለሁ፣ አሳቤን አልለውጥም» የሚል ዕቡይነት፣ ለተሻለ ነገርም ቢሆን ማፈግፈግን አለመውደድ፣ ቢያዋጣም ባያዋጣም የያዝኩትን አቋም እገፋበታለሁ የሚል ቂልነት ነው። ሞኝ ካመረረ፣ በግ ከበረረ።

የጠፋው ልጅ የተሞኘው ስሜቱን ብቻ አዳምጦ ከቤት የወጣ ቀን ነው እንጂ ውድቀቱን አይቶ በልቡ የተጸጸተ ቀን አይደለም አቅጣጫ ቀይሮ ወደተገቢው ቦታ መመለስ ልባምነት ነው እንጂ ፈሪነት አይደለም። በጨለማ መንገድ መፈርጠጥ ነው ሥጋዊነት፣ መመለስ መንፈሳዊነት ነው።

አራተኛው ጭራቅ ምንድነው የተባለ እንደሆነ፡ «የታረቅሁ እንደሆነ የተስማማሁ እንደሆነ ይህ ይቀርብኛል፣ ይህ ይጐድልብኛል» የሚል የሞኝ ስስት ነው። ሽማግሌ/አስታራቂ ሰምቼ እሺ ብል ማንነቴ ይደበዝዛል፣ ክብሬ ይስለመለማል፣ ጥቅሜ ይቀናነሳል ተደማጭነቴ ዝቅ ይላል የሚል አጉል ፍርሃት በአስር በትር እንድንደባደብ ያደርገናል። የፈሪ ዱላ አሥር ነው። ዕርቅና አንድነት ያበለጽጋል እንጂ

አያደኽይም፡ ለመኖርና ለመክበር ዋስትናችን የከበበን ፍጥራ ብዛት ሳይሆን የሚወደንና የሚያስብልን የእውነት ዳኛ እግዚአብሔር ነው። እውነተኛ ዕርቅ ከድርድር ሰነዱ ይልቅ በጻድቅ አምላክ ላይ ባለን እምነት የምንወስነው የጀግንነት ውሳኔ ነው።

ዘጠኝ ወንጀሎች

(በቃለ እግዚአብሔር ላይ የሚፈጸሙ)

በጥቁር ወይም በቀይ ቡናማ ፕላስቲክ ሽፋን ተለብጦ፣ የአክሱም ወይም የላሊበላ መስቀል ተቀርጾበት፣ በየቋንቋው ቀርቦአል፣ በቴፕ እየተቀዳ፣ በዜማ ፈርጥ ተጊያጊጦ፣ በሥዕል መግለጫ ተከብቦ በየዐይነቱ ቀርቦአል፣ በቡድን እሰጥ እገባ፣ በየምስባኩ ሞገድ ስግምግምታ ወይም በጸሎተ ስብሰባ ለሆሳስ በልዩ ልዩ መድረክ ቀርቦአል ቃለ-እግዚአብሔር፣ መጽሐፍ ቅዱስ።

የቅጂው ብዛት፣ የአድናቂው መበራከት በተንጣለለ ሜዳ፣ ያለ ጥቃት፣ ያለ ሥጋት የሚሄድ ያስመስለዋል። ይሁን እንጂ ነገሩ በርጋታ ቢጤን በጣም ከባድ ወንጀሎች እየተፈጸሙበት ያለ መጽሐፍ እንደ ሆነ ማየት ይቻላል። የሚገረመው ነገር አብዛኛውን ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች የመጽሐፉ ቤተሰብ ነን የሚሉ ሰዎች መሆናቸው ነው። ለወንጀሉ ምስክር ሳንጠራ፣ ለብይን ችሎት ሳንሰይም እንደ ውስጥ አዋቂ ብቻ፣ «እኔስ ወንጀለኛ ሆኜ ብገኝ» በሚል ትሕትና ወንጀሎቹን እንዘርዝር፡

1. ቃሉን ከሌሎች እኩል ማስለፍ

ሃይማኖት ብዙ ነው፣ መመሪያውም እንደየሃይማኖቱ ታሪክና ባሕል እንደሃይማኖቱ መሪዎች ዐይነት የተዋቀረሃረ ነው፣ በዚሁ የአስተሳሰብ ስልት ክርስትና የራሱ የእምነት መጽሐፍ አለውና ከብዙዎቹ አንዱ እንደ ሆነ ቆጥሮ በአንድ ተርታ መመደብ ቀዳሚው ወንጀል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሰው እጅ የተጻፈ፣ በሰው ቋንቋ የተነገረ፣ በየማኅበረ ሰቡ ዐውድ ውስጥ ባሉ ሁኔታዎች ዙሪያ የተቃኘ ቢሆንም ምንጩ መለኮት ነው፣ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በአይሁድ ባሕል ቀለም ቢነከርም ሸማው የተሠራው የሰውን ዘር ሁሉ በፈጠረው ሸማኔ ነው። የግሪክ ፍልስፍና ቃላት ቢበተኑበትም መደቡ ክርስቶሳዊ ነው በአንድ ጊዜ ባህል ጠቀስ፣ ባህል ዘለልም የመሆን ብቃት አለው ከጥንት ሥነ

ጽሑፎች አንዱ ነው፣ ነገር ግን በአሁኖቹነትና በዘላለማዊነት ማንም አያክለውም። ስለ ሥነ ምግባር ብዙ ይናገራል፣ ነገር ግን ከብዙ አማራጭ የሞራል ድንጋጌዎች አንዱ አይደለም። አስተያይታችሁ ለኩኝ ሳይሆን የሚለን ሁሉንም በእኔ መለኪያነት ተመልከቱ ነው። ከሌሎቹ ሁሉ ጋር ተጠጋግተህ ተቀመጥ ስንለው ምርጫው ሁለት ብቻ ነው ይለናል፣ ቀዳሚ አድርጉኝ አለበለዚያ አላወቃችሁኝም።

2. ቃሉን አለማንበብ

ብዙዎቻችን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ወደር የለሽነት አሳምረን መናገር እንችላለን ነገር ግን በየዕለቱ ይህን መጽሐፍ ላለማንበብ የምናቀርበው ሰበብ ሰፊድ ሙሉ ነው። የሥራ ውጥረት፣ የአካል ድካም፣ ሌሎች አስቸኳይ ጉዳዮች፣ የስሜት አለመነሣሣት፣ ወዘተረፈ። የምናወድሰው በአፋችን እንጂ በዐይናችን አይደለም፣ የከንፈር ግልጋሎት (lip Service) እየቸርነው እንኖራለን፣ ሕይወታችን በቀን ሩብ ምዕራፍ እንኳ ለማንበብ በማይችል ሁኔታ የተጣበበ ነው። ነገሩን ዞር አድርገን ብናየው ይህ አካሄድ ምን ማለት መሰላችሁ? ልዑል እግዚአብሔር ስልክ ደውሎ «ዛሬ ካንተ ጋር ልነጋገር እፈልጋለሁ፣ የግማሽ ሰዓት ጊዜ ልትሰጠኝ ትችላለህ?» ብሎ ቢጠይቀን «ካንተ ጋር መነጋገር በጣም ደስ ይለኛል፣ ግን ይቅርታ አድርግልኝ ዛሬ ቢዚ (ባተሌ) ነኝ» እንደ ማለት ነው።

ባለ ራእዩ ቅዱስ ዮሐንስ «የዚህን መጽሐፍ ቃል የሚያነቡ ብፁዓን ናቸው» ብሎአል። (ራእ 1:3)። ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክር «ለማንበብ ተጠንቀቅ» ብሎታል። «የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን የሕግ መጽሐፍ የቀን ሩብ ያህል አነበቡ...ተናዘዙ...ሰገዱ» (ነህ 9:3)። ተብሎ ተጽፏል።

3. ቃሉን አለማጥናት - አለመመርመር

ሃይማኖታዊ ትኩሳት በየቦታው አለ፣ ሰዎች ስለ እምነታቸው፣ ስለ ልዩ ልዩ አስተምህሮዎቻቸው፣ ስለሚደግፉት ትልቅ ሰው፣ ስለሚለማመዱት

አዲስ ልምምድ በንቃትና በስሜት ይናገራሉ፣ ወላፈኑን ዘልቀን ወደ ውስጥ ስንገባ ግን የነፍስ ግልብነት በገፍ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ በጥራዝ ነጠቅ የሚጠቀስ መጽሐፍ ሳይሆን በውል የሚጠና መዝገብ ነው። በስክነ ልቦና ቅንጣቶቹን፣ ቃሎቹን፣ ሐረጎቹን፣ ዐረፍተ ነገሮቹን፣ አንቀጾቹን፣ ምዕራፎቹን፣ መጽሐፎቹን፣ ኪዳኖቹን፣ ሁሉ መልካቸው ሊጤን ፍቺያቸው ሊመረመር፣ የሕይወት ተዛምዶአቸው ሊገናዘብ መቻል አለበት። የመጽሐፉ ጠቅላላ መልእክት፣ የጸሐፊዎቹ ዋና ትኩረት፣ የታሪኩ አፈላሰስ፣ የቅንጣቶቹ አሰካክ እንዲገኝ በርጋታ፣ በውይይት፣ በትሕትና ሊመረመር ይገባል።

የተባለው ሁሉ የተባለበት ዐውድ አለው። እያስተዋሉ ማጥናት ማለት ዐውደ ንብነት ነው፣ ይህንን አለማድረግ ዐውደ ውጥነት ነው። (ጋጠወጥ በሚለው ቀመር)።

«ልበ ሰፊዎች ነበሩና ነገሩ እንደዚህ ይሆንን ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ። ሐሥ 17:11»

4. ቃሉን ለራስ ጉዳይ እንዲመች መጠምዘዝ

መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስ ጌጥ ሆኗል። የጎማ ማስታወቂያ ባወጣ እንኳ ልጠቅሰው ሳልችል አልቀርም። የተማረ፣ የተመራመረ ሁለገብ አዋቂ ስለሚያሰኝ ከዚህ ሰፊ ባሕር በየልኬቱ መጨለፍ የስልጡኖች ወግ ነው። በሜዳ ያለው ይህንን ቢያደርግ እየታዘቡ እየተገረሙ ይኬድ ይሆናል። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ቃሉን ለማስተማር ቆመን፣ እንቅብ ሙሉ የሰው አሳብ እየነዛን የእንቅቡን ክፈፍ በቃሉ ቆዳ ብንለጉም እግዚአብሔር የሚምረን ይመስላችኋል? ከየጎዳናው ሳገኘነው አሳብ መንደርደሪያ፣ ከየማድጋው ለጨለጥነው ውሃ ማጣፈጫ እንደ ጭ እናደርገዋለን? «ቃሉን ስበክ» ተባልን እንጂ ቃሉን አስታክክ አልተባልንም። ከዚህ የሚመሳሰለው፣ ነገር ግን ከዚህ የከፋው በደል ደግሞ ቃሉ የማይለውን እንዲልልን የምናባብልበት፣ የምንገፋፋብት፣

የምናስገድድበት የንግድ ታክቲካችን ነው። የቃሉን እጅ ጠምዝዘን ጠምዝዘን ከሰፈሩ አፈናቅለን አውጥተን በየስርቻው ከመጣል የበለጠ ምን ወንጀል አለ? እንደ ባለሙያ አበባ ጎንጓኝ የምንፈልገውን ቀለም ብቻ ነቃቅሰን ሌላውን አንገዋለን ከፍጥረቱ ውጭ የሆነ ነገር ብንሠራ አንጠየቅበትም?

«የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍር ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ» (2ጢሞ 2:15)

«የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡ እንደ ብዙዎቹ አይደለንምና በቅንነት ግን እንናገራለን» (2ቆሮ 2:17)

5. ቃሉን አለመናገር

«ነገር ሲበዛ በአህያ አይጫንም» ጎተራም አይገባም። የእግዚአብሔር ቃል ግን የነፍስ ምግብ ነው፤ «የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ ዐውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል» የተባለለት የእግዚአብሔር ባሪያ ነው ኢሳ (50:4)።

ቃሉ ሲነገር የተዝለፈለፈ ይደገፋል፤ የጎበጠ ይቀናል፤ የገነተረ ይለዝባል ምላሳችን ያገሩን ሁሉ ወሬ ሲያስተነትን እየቀለጠፈ ቃሉን በሚናገር ጊዜ ለምን ይተሳሰራል? አለማወቅ ነው? እፍረት ነው? ስስት ነው? አለመዘጋጀት ነው? ምንድነው?

«በእኔና በቃሌ የሚያፍር የሰው ልጅ ከመላክቱ ጋር በሚመጣበት ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል» ብሎአል ጌታችን። ያህዌ ለኢያሱ «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ» አለው። ስትነሣ ተጫወተው፤ ስትቀመጥ አውራው፤ ከልጅህ ጋር ተነጋገረው አለው። የንግግር ጉትህን ቃለ እግዚአብሔር ይሙላበት፤ ቢጋራ ስትሰበሰብ የጨዋታህ ርዕስ ይሁን፤ ለባልንጀራህ መናገር ስትለምድ ለሌላውም የመንገር ጸጋ ኢያገኝህ ትመጣለህ። መዝሙረኛው «የአፍህን ፍርድ ሁሉ በከንፈሬ ነገርሁ» መዝ 119 13 ይላል። ለዚህ ንግግር መሠረቱ ለነቢዩ እንደተባለው «ቃሉን

በልብህ በጆሮህም መስማት ነው» (ሕዝ 3:10) የጌታ ሥርዐትም «ቃሌ ያለበት በእውነት ቃሌን ይናገራል» የሚል ነው (ኤር 23:28)

6. ቃሉን አለማድመጥ

ሰዉ በየቤተክርስቲያኑ ደጃፍ የሚንጋጋው ለምንድነው? ተናጋሪና ሰሚ ይደማመጣሉን? የምንወደው ሰባኪ ባይሆንስ? ያልተማረ ማይም ቃለ እግዚአብሔር ተናጋሪ ቢሆንስ? አቋሙ የማይጋብዝ እንደ ጳውሎስ «ሲታይ ሰውነቱ ደካማ» ወይም እንደ ጌታችን «ደም ግባት የሌለው» የሆነ እንደሆነስ? እናደምጠዋለን? ወይስ እንደ አክአብ «እርሱ ሁልጊዜ መልካም ነገር አይናገርልኝም» ብለን እንሸሻለን? ወይም እንደ እስጢፋኖስ ወጋሪዎች ጆሮአችንን እንደፍናለን?

7. ቃሉ የሚዳስሰውን አድማስ መወሰን

«የነፍስ ጣጣ ከሆነ፣ የወዲያኛው ዓለም ከሆነ ቃለ እግዚአብሔርን አነባለሁ ስለ እንጀራ፣ ስለ ሥራ፣ ስለ ሳቅ፣ ስለ ለቅሶ፣ ስለ ስፖርት፣ ስለ ቴአትር፣ ስለ ወዲህኛው ዓለም ግን መጽሐፉ የሚያገባው ነገር የለም» የሚለው አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ቃል ሁለገብነት ውሱን ያደርገዋል።

በማይካድ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የሥነ ቅርስ ምርምር፣ የሥነ ምግብ ጥናት፣ የሥራ ተውኔት ጥበብ፣ የሥነ ተዋልዶ ሳይንስ፣ ወዘተ አይደለም፤ ሲፃፍም ዓላማው ይህ አልነበረም። ይሁን እንጂ በሕይወት ጉዳዮች ሁሉ ላይ ስለምንወስዳቸው ርምጃዎች፣ ስለምንወስናቸው ውሳኔዎች አጠቃላይ ቢጋር (ንድፍ) ይሰጠናል። የመጽሐፉ ሰው ነኝ የሚል ሁሉ ዓለሙን የሚቃኘው÷ ርእዮተ ዓለሙን የሚገነባው በገጸ ባሕ በተጻፉት ታሪኮች፣ ቅኔዎች፣ ትምህርቶች አማካይነት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የኑሮ ዘይቤያችን መቃኛ ነው። የሕይወት ዜማ ጉባሬ፣ የሰማይ ምድር ሥምረት የሚገኘው በዚህ ቅኝት ውስጥ ለማደር በትሕትና እና በርጋታ ስንገራ ነው።

8. ቃሉን አለማመን

የቃሉን ውበት እያደነቁ፣ በጥንታዊነቱ እየተገረሙ፣ ገጾቹን በትጋት እየመረመሩ የሚለውን ግን የማያምኑ፣ ደግሞ የሚሰጠውን ተስፋ የሚጠራጠሩ የሥራውን ጉልበት የማይገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች አሉ።

አሮጊቷ ሣራ «የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ እንደሆነ ስለቆጠረች» ዘር ለመፀነስ ኃይል በእምነት አገኘች። ቃሉ የሚደምቀው የሚጠቅመውም ሲታመንበት ነው። በቃሉ ላይ እምነት ብናጣ ሕይወት ስክርክር ይላል። እነዚያ ወደ ኤማሁስ የሚያዘግሙ ግራ የተጋቡ ደቀመዛሙርት ከጌታ የተቀበሉት ተግሣጽ «ነቢያት የተናገሩትን ከማመን ልባችሁ የዘገየ» የሚል ነበር። (ሉቃ 24:25)

9. ቃሉን አለማድረግ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባታቸው ሥራ ሰጥቷቸው ስለ ተሰማሩ ሁለት ልጆች ምሳሌ ሰጥቷል። አንደኛው ትእዛዙን አልፈጽምም ብሎ የወጣ በኋላ ተጸጽቶ የፈጸመ ሁለተኛው እሺ ብሎ ተሰናብቶ ሳያደርግ የቀረ። አንዳንዶቻችን ቃሉን ስንሰማ፣ ስናነብ፣ ስናጠና «እሺ» እያልን በሕይወት ሜዳ ላይ ግን አመጸኞች፣ ልግመኞች፣ አታላዮች ሆነናል። ከሁሉ የከፋው በደል ይህ አይደለምን? ያዕቆብ የበረከትን ምንጭ ሲያሳየን እንዲህ አለ: «...ነፃ የሚያወጣውን ፍፁሙን ሕግ ተመልክቶ የሚፀናበት ሥራን የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው በሥራው የተባረከ ይሆናል። (ያዕ 1÷25)።

ቃሉ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ ቋንቋ፣ ግቡ በሆነ መንገድ ቀርቦልናል። እያገናዘብን እንድናጠናው ከመግለጫና ከማብራሪያ ጋር በእጃችን ተሰጠን። ይህንን የተደረገልንን ታላቅ ቸርነትና ውለታ በምን እንመልሳለን?

ለእኔ እንደሚገባኝ ውለታው የሚመለሰው በቃሉ ውስጥ የተፃፈውን ተቀብለን ስንፈጽመው ብቻ ነው። ይህ ትሕትናና እሺ ባይነት ቸሩን ጌታ ያስደስተዋል የእርሱ ደስታ የእኛ የተትረፈረፈ በረከት ይሆናል። የማያቋርጥ የበረከት ውደት።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብርሃን ፍለጋ

(እርሱ እኔና እኛ)

እንደኔ ባለ የማይም ደፋር ስታስቲክስ አንድ አማካይ ሰው (እንደዚህ የሚባል ካለ) በደቂቃ 80 ቃላት እያወጣ 8 ሰዓቶች ያህል ቢናገር - አላባም ቢሆን ገለባ - የንግግር ዕድሜውም 50 ዓመት ቢሆን አንደበቱ በሞት ክር ወደ ውስጥ ሳትሳብ በፊት ከ700 ሚሊዮን ቃላት በላይ ያቸኮሳደጉዳል። ይህ እንግዲህ የአንዱ ሰው ብቻ ነው፤ በዚሁ የዕድሜ ክልል ከሌሎች የሚያደምጣቸውን ቃላት እንቁጠር የተባለ እንደሆነ ደግሞ ስሌቱ አታካች ነው የሚሆን።

ዙሪያ ዙሪያውን የምሄደው ለምንድነው ቢባል በቃላት ታጥረናል፤ ስንሰማ ስናሰማ የምንኖር ተናጋሪ - ሰሚ ፍጥረት ነን ለማለት ነው። ምን ያህሉ ጠቃሚ ምን ያህሉ ሕይወት - አድን ቃል እንደሆነ ማን ይለካዋል?

ባለ ድምጥና ድምጥ ተርጓሚ ፍጥረት ያደረገን እግዚአብሔር ራሱ ደግሞ ይናገራል፤ የተናገረውና የሚናገረው ዋና ነገር አንድ ላይ በተጠረዙ 66 መጻሕፍት (መጽሐፍ ቅዱስ) ውስጥ ይገኛል። የሰውን ንግግር ጥሩነት ማረጋገጥ ባልችልም፤ የእርሱን ግን በድፍረት ልናገር እችላለሁ። ቃሉ ደጋፊ ቃል ነው፤ የሰው ልጅ እንግድግድ ስለሆነ። ቃሉ ገላጭ ቃል ነው፤ ዓለማችን በመንፈስ ጨለማ ውስጥ ስላለች። የእርሱ ቃል በጥልቅ የሚነካን ነው፤ ለሌላ ለማንም የማንበገር ስለሆንን። «የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ አውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል»[1] ብሎ በኢሳይያስ በኩል የተነገረው ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማንም እንደሱ አልተናገረም። ቃሉ በርግጥ የተንቀጠቀጠች ነፍስ አጽንቶአል። እስካሁንም ድረስ ይህንን ይሠራል።

ይህን የምታነቡ ብዙዎቻችሁ ስለ አምላካችን ቃል ብርታትና ጥሩነት

በትምህርትም በተረጋገጠ ልምድም የምታውቁ ስለሆነ በዚህ መስመር ልቀጥል አልፈቅድም። አሁን የሚያሳስበን ዋና ጉዳይ ይህ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ምንነቱ እንደሚያሳስበን ሁሉ «እንዴቱ» ም ሊያሳስበን ይገባል። «ካነጋገር ይፈርዳል፣ ካያያዝ ይቀደዳል» ተግባራዊ ምሳሌ ነው።

የቃሉን መረዳት አስመልክቼ ሦስት ዋና ዋና ምሰሶዎች ላቁም። (እነዚህን ጆን ስቶት ከጻፉት መጽሐፍ የቀዳኋቸው ናቸው) የመንፈስ ቅዱስ አብሪነት፣ የክርስቲያኑ ትጉህ ጥናት እና የቤተ ክርስቲያን ስብስብ ትምህርት።

የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ሰጪነት

ችሎታ እንዳለው እንደደራሲው ሆኖ የራሱን መጽሐፍ ለማብራራት የሚበቃ ማንም አይኖኝም። መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት አሳቢ ሰጪነትና ተቆጣጣሪነት የተጻፉ ናቸው። [2] ቃለ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ራስ ገላጭና ራስ - ተርጓሚ መዝገብ ነው። እንግዲያው ማንም ባለአእምሮ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ሲፈልግ ይህንን የብርሃን ባለቤት ቸል ሊል አይችልም። አንድ ሰው የተራቀቀ የሥነ ፈለክ (Astronomy) ሊቅ ሊሆን ይችላል። ወይም በውስብስብ ቀዶ ጥገና የሚተካከለው ላይኖር ይችላል፣ ወይም በቲኦሎጂ (ትምህርተ መለኮት) ብዙ የወረቀት ማስረጃዎች ሊኖሩት ይችላሉ። ያው ሰው ግን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በጥልቅ በመረዳት አግጣጫ ዘላ ሞኝ ሊሆን ይችላል።

➢«መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ አልጠላም ግን ሳነበው አይገባኝም» የሚለው አባባል የሚጠቁመን ነገር ቢኖር ይህንን ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት አይቻልም። «ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉመው አልተፈቀደም» [3] ይለናል ቅዱስ ጴጥሮስ ምክንያቱንም አስረግጦ ሲነግረን «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ /አነሳሽነት/ አልመጣምና «ይላል። ይህ እውነታ የሚያስገነዝበን ዋና ነገር ትሕትና ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ /ለመስማት/ ለመናገር ስንቀርብ ትሑታን እንሁን። «አንተ ያልመከርከኝ ያሳስረዳኸኝ ከሆነ ልዑል ጌታዬ ሆይ ልቡናዬ የሚቀምመው ሁሉ ፍሬ ከርስኪ ነው፣ የኔ ቡቱ ለራት አይበቃም። እንዲያውም ከማዳን ይልቅ ይገድልም ይሆናል፣ የተጫጠረውን ለመፍታት ስታትር የበለጠ ይወሳሰብብኛል፣ ልዑል መንፈስ ሆይ ብርሃን ስጠኝ፣ የቃልህን እርድ ስትዘረጋልኝ አበላለቱን አሳየኝ።» እያልን እንጸልይ።

የክርስቲያኑ ትጉህ ጥናት

ሁሉን በጥበብ የፈጠረ እግዚአብሔር አእምሮ የሚባል የእውቀት መናኸሪያ ሠራልን። የርሱ ሥሪት ነውና በመሠረቱ እንከን የለሽ ነው። ኃጢአት መርዙን ነስንሶ ለክፋት እያሰናዳው ሲውል የሚያፈልቀውን ስንት አበሳ ብንፈራም ለክርስቶስ በተገዛው አዲስ ሰው ውስጥ በጎ ሥራ ፈጻሚ ዕቃ መሆኑን ልንዘነጋ አይገባም።

ክርስቲያኖች ወንድሞችና እህቶች በአእምሮአችን እንጠቀም። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «የምለውን ተመልከት ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጥህ» [4] ሲል ሁለቱን የመረዳት ዘንጎች ባንድ ጊዜ ያቀርባቸዋል። የእግዚአብሔርን ርዳታ እና የሰውን አጠኖ የመመልከት ድርሻ። ጌታ በወንጌሎች ውስጥ በመደጋገም ይናገር የነበራቸው ቃላት «ለምን ራሳችሁ በቅን አትፈርዱም ወይም አስተውላችሁ አትናገሩም?» [5] የሚሉ የአእምሮን ሚዛን የሚጠይቁ ነበር። ጳውሎስም «አእምሮ ላላቸው ሰዎች እናገራለሁ የምለውን እናንተ ፍረዱ.....» [6]«እኛ ግን የክርስቶስ ልብ/ አእምሮ አለን።» [7] ይለናል።

ጸሎትና የአእምሮ ማስተዋልን ማፋታት በእውነት ላይ ግፍ መፈጸም ነው፣ የሁለቱ ሚዛን ከተጠበቁባቸው ሰዎች አንዱ ዳንኤል ነበረ።

«ዳንኤል ሆይ አትፍራ፣ ልብህ ያስተውል ዘንድ ሰውነትህንም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ

ተሰምቶአል::» 8

ጸሎት ወዳጅ ዳንኤል የምርምር ሰው ነበር:: መጻሕፍትን እየመረመረ የሕዝቡን ዕጣ ፈንታ የትውልድ አገሩን ተስፋ ያሰላስል ነበር «...በመጽሐፍ አስተዋልሁ» [9] ብሎ ራሱ እንደተናገረው ነው:: ዘማሪው «ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ» [10] ብሎ የሚመክረን ለመማር አእምሮአችንን እንድንከፍት ሲያበረታታን ነው:: ተግተን መጽሐፍ ቅዱስን እናጥና ስንል ምን ማለታችን ነው?

መጽሐፉን እንደ ስልክ ማውጫ መጽሐፍ የምንፈልገውን ቅንጣት ለማግኘት ብቻ አናገላብጠው የእግዚአብሔርን ሁለ-ገብ ምክር እንድናገኝ ርሱ በርሱ እያያዝን እናስተንትነው::

ለመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ-ጥናት በቂ ጊዜ እንስጥ:: ነፍሳችን ለየዕለቱ የኑሮ ጥብጠባ በቋፍ ላይ ሆና ከምናነበው የችኮላ ንባብ ጥልቅ ነገር እናገኛለን ብለን ራሳችንን ማታለል አይገባንም:: ደግሞስ የሚያናግረን የሰማይና የምድር ጌታን መሆኑን ልብ ልንል አይገባምን? ዛሬ በቤተክርስቲያን በግል ሕይወታችንም ለሚታየው ግልብነት አንዱ ምክንያት ግልብ ንባባችን ነው:: ስንት አልባሌ ነገር እያመነዥክን የምንውል ሰዎች የተባረከውን ቃል በቀን አንድ ጊዜ እንኳ ትንፋሽ ሰብስበን ለመመገብ አልቻልንም::

66ቱን መጻሕፍት የጻፉልን ሰዎች እንደ እኛ ሥጋ የለበሱ ባለ ስሜት ባለ ተጨባጭ ታሪክ ሰዎች መሆናቸውን እናስታውስና ለዘመናቸውና ለነበሩበት ሁኔታ የተሰጣቸውን መልእክት እንዳስተላለፉ ልብ እንበል:: ይህ ልብታ የሚሰጠን ዋና ነገር «ያን ጊዜ ለነዚያ ሰዎች ቃሉ ምን ፍቺ ነበረው? የሚለውን የተደላደለ የትርጓሜ መረባርብ ነው:: ከዚያ እውቀት ተነስተን ዛሬ «ለእኔ ይህ ቃል ምን እያለኝ ነው?» ወደሚለው ማገናዘቢያ ለመሄድ መንገዱ የተመቸ ይሆናል:: በቀጥታ የተነገረውን በቀጥታ ትርጉም+ በዘይቤ የተነገረውን በዘይቤ ፍቺ በግጥም

የቀረበውን የግጥም ሕግ በሚፈቅደው ትንታኔ በራእይ ስዕል የተሳለውን ስዕሉን በመተርጎም አግባብ ያለው የትርጓሜ ጎዳና ልንይዝ ይገባል::

– ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አሳብ ሁሉ ባንድ ጊዜ ፍንትው ብሎ ላይበራልን ይችላል:: ልንመልሳቸው የማንችል አያሌ ጥያቄዎች በፊታችን ድቅን ይላሉ:: አንዱ መካሪ እንደ ነገረን መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ዓሣ እንደ መብላት ዐይነት ነው:: እሾህ ስላለ መብላቱን አንተውም፤ በብልሃት እየነቀስን በማውጣት ለመብላት የተመቸውን እንበላለን እንጂ:: የሚያደናግሩን የውስጥም የውጭም ድምጾች ስለበዙ «እኔ ምን አታገለኝ» በሚል የስንፍና ዘይቤ ራሳችንን እየሸነገልን እንዳንርቅ መጠንቀቅ ተገቢ ነው:: ያለመታከት የሚቆፍረው ነው ጥልቅ ውሃ የሚያገኘው::

የቤተክርስቲያን ስብስብ ትምህርት

በየጸሎት ጓዳችን የሚገለጥልንን የእውቀት ፍንካች ይዘን ወደ እግዚአብሔር ልጆች ማኅበር የእውነት ዐምድና መሠረት ወደ ሆነች ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ይገባናል:: ለሁለት ዋና ዋና ጥቅሞች:: አንደኛ - «ተረድተናል» ያልነውን እውነት እርግጠኝነት ለማስፈተሽ-ለማጎልበት-ለማጽናት:: ሁለተኛ-ለጌታ ልጆች በጸጋ ከተሰጠው የመንፈሳዊ እውቀት ባሕር እየቀዳን ከጠቅላላው የቤ/ክ ትምህርት ጋር አንድ ቀለም እንዲኖረው እያስማማን ለመሸመን::

ጳውሎስ ለብቻው ከእግዚአብሔር የተማረ ሰው ነበረ:: ይህን ትምህርቱንና አገልግሎቱን ግን ማረጋገጥ ስለፈለገ ወደ ቅዱሳን ወንድሞች እንደሄደ ይተርክልናል:..... «እንደተገለጠልኝም ወጣሁ፤ ምናልባትም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብክውን ወንጌል አስታውቅኋቸው»[11] ይለናል::»

ጌታ ለቤተክርስቲያን አስተማሪዎችን ሰጥቷል:: ከዚህ ስጦታ ለመጠቀም ትሑትም ትጉህም መሆን ያስፈልገናል:: ይህ የትምህርት መድበል

ምናልባት በአንድ ቦታ ተከማችቶ ባይኖን በመጻሕፍት አማካይ ከልዩ ልዩ የጌታ አገልጋዮች ስብከት ልንጠቀም መፈለግ የኛ ፈንታ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ባለንበት አጥቢያ ቤ/ክ የሚያመረቃ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያላገኘን ሲመስለን ነቃፊዎችና ተቺዎች ወደ መሆን እንገፋፋለን። ከዚያ ይልቅ እኛ ልናደርግ የምንችለውን አስተዋጽኦ ማሰብ ፍሬያማ ያደርገናል። በብልሃት የተሠራ የቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የምግብ ገበታውን በማስፋትም ሆነ የትርጓሜ ጥንቁቅነትን በማስለመድ በኩል ከፍ ያለ ጥቅም ይሰጣል።

«ከቅዱሳን ጋር.....ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ» [12] መባሉ የእውቀት ጎዳና የወል አካሄድ እንዳለው ሲጠቁመን ነው። አብረን እንወቅ አንዱ በሌላው ላይ ይጨመር። «እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥፁ - አንዱም ሌላውን ያንጸው። [13]

-ያልነው ሁሉ ሲሰበሰብ፡ በብርሃን ፍለጋ ጥረታችን ውስጥ ትሕትና ትጋት እና ልበሰፊነት ያስፈልገናል ነው። ትሕትናው - የሰማይን አይተኬ ርዳታ ለመቀበል ትጋቱ በነቃ አእምሮ ልቡና የተጻፈውን ለመመርመር፣ ልበ ሰፊነቱ በቤተክርስቲያን የተሰጠውንና የሚሰጠውን ትምህርት ለጥቅማችን ለማስተናገድ ነው።

የጥቅሶች ማውጫ

1. ኢሳ 50:4
2. 2ጢሞ 3:16-17
3. 2ጴጥ. 1:20-21
4. 2ጢሞ 2:7
5. ሉቃ 12:57
6. 1ቆሮ 10:15 11:13
7. 1ቆሮ 2:17
8. ዳን 10:12
9. ዳን 9:2
10. መዝ 32:9
11. ገላ 2:2
12. ኤፌ 3:18-19
13. ቆላ 3:16

የጠማው ንጹሑን ይጠጣ

በሰማይ ብልጎት የተሠራ፣ የጤና የፈውስ መጠጥ፣
ትኩስ ጎይሉን ጠብቆ፣ ለበሽተኛው ሁሉ እንዲሰጥ፣
አጋፋሪነት ተሹመሃል በሰማይና በምድር መሃል።
እንዲበራከትልህ ብትሻ፣ ለዐላፊ አግዳሚው ሽኝት፣
ውሃ ከልሰህ አቀጣጥነው የጠማው አይለይ ማር ከሬት
ውሃ ያጣህ እንደሁ ማቅጠኛ፣
ዘመድ ወዳጅ መሸኛ፣
ያደረ ጠላ አይጠፋም በየጠማቂዋ ጓዳ
እንዲመሳሰል አርገህ ቀላቅለህ በርዘህ ቅዳ።
የጌሾ የብቅል ቅልቅል፣
የገብስ የበቆሎ ግንፍልፍል፣
ቀድተህ አጠጣው አዳሜን
ነፍሱን ውሃ ጥም አክስሎት በየደጃፍህ የቆመውን።
ቢያብረጀርጀውም ቄይቶ፣
ለጊዜው ተንፈስ ይላል ከቅይጥ ቅመምህ ረክቶ
ጮቤ ያስረገጠውም እንደሁ ናላውን ነካ አድርጎት፣
በቁብጨባ ታግዘዋለህ
ዕዳህን ምን ታደርጋለህ?
ዐይንህ ቀለሙን እየወደደ ምላስህ ዐቅም ቢያጣም፣
የሕይወትን ቃል ጠጣውና የነፍስህን ሕመም ዐክም።
እስካሁን ውጠሽው ቢሆን፣ ድፍረት አግኝተህ ጨልጠሽው፣
የሆድህን አውሬ በገደለው።

አፍ ሆድህ ተስማምቶልህ፣ ቀልብ ሥራህ ሰምሮልህ፣
ትጠቅም ነበር ሕዝቡን ሁሉ፣ እንዲያው እንጂ ነው መፍራትህ::
ሲውጡት ነው የሚሠራ መድኀኒት፣ ጨክነው ሲያስገቡት፣
በአፍ ይዘው ቢያንጓልሉት፣
ለታይታ ይሆን ብለው ቡልቅ ቡልቅ ቢያደርጉት፣
ቅርሻት ነው በሽታም ነው
ጌጥ አይደለም ማፈሪያ ነው::
ስለዚህ ብርዝ ውሃውን ተወው
ቅይጥ ቃልህን ትፋው::
የጠማው ንጹሕ ይጠጣ
ሰማያዊ ርካታ ይምጣ::
አንተም ተጐንጨው ጤና አግኝ
እውነት አገሩን ይዳኝ:: (2ኛ ቆሮ 2:17)

በምን አወቅኸው?

ሥነ መለኮት፣ ነገረ መለኮት ... ትምህርተ መለኮት፣
ለመሆኑ መለኮትን ያማሩታል? አሳቡና አካሔዱ በወረቀት ንባብ፣
በክፍል ውስጥ ክርክር፣ በብራና ምርመራ፣ በልቡና ቁፋሮ ይገኛል?
ያልተገኘ እንደ ሆነ የሦስት ዓመት፣ የአራት ዓመት፣ የአርባ ዓመት
ድካም መና ሊሆን ነው:: የማለዳ ሩጫ፣ የቀትር ማፋሸክ፣ የማታ
ቦዘዝታ፣ መፍዘዝ፣ መደንገዙ ሁሉ ፍሬ አልቦ ሊሆን ነው:: የሆነም
እንደ ሆነ ይሁን! ያልሆነ እንደ ሆነ ግን ይመርመር፤ ምናልባት
እውነቱ ሁለቱንም ያጣመረ በሰበቃውም የነጠረ ሌላ ብሩኅ ሐቅ ከሆነ
ደግሞ አንየው::

እግዚአብሔር መለኮት ከሰማየ ሰማያት የመጠቀ፣ ከሰው ልቡና ደረጃ
የላቀ፣ ከምድር ዓለም አበሳና ጉድፍ የራቀ፣ አሳብ ሥራውም የረቀቀ
አምላክ ነው:: ይኸው የአይሁድ ክርስቲያን አምላክ እዚያ ነው ሲባል
እዚህ የተገኘ፣ በዓለሙ ሁሉ የናኘ፣ የሰው ወዳጅ፣ የፍጥረት አሳዳሪም
ነው:: እሱን ማወቅም የሚከብደውና የሚቀለው በዚሁ መንታ ባህርዩ
ነው::

ይህ መለኮት ሊታወቅ ይፈልጋል፣ ማወቂያ ልቡናም ለሰው ልጅ
ሰጥቶአል፣ የመታወቂያ ገበታም ዘርግቷል:: እንግዲያው ልናውቀው
ይቻላላ! አዎን ይቻላል፣ የተቻለውን ያህል፣ እርሱ ሊገለጥ የፈቀደውን
ያህል እኛ ለመስማት የወደድነውን ያህል::

ይህን አምላክ ለማወቅ መጻሕፍትና መጻሕፍት ተንታኞች፣ ውይይትና
ክርክር፣ የክፍል ሥራና የቤት ሥራ ይረዱናል ወይ? አዎን ይረዱናል::

"መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ
እነዚሁ መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው"[1]

"የምትስቱት አኩ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ነው፤"[2]

"እዝራ እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር"[3]

"(ሉቃስ) ከቅዱሳት መጻሕፍት እያመላከረ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ከአይሁድ ጋር በጽኑ በመከራከር በሕዝብ ፊት ይረታቸው ነበር።"[4]

"(ጳውሎስ) በየሰንበቱም ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ጋር በምኩራብ ውስጥ እየተነጋገረ ሊያሳምናቸው ይጥር ነበር።"[5]

"ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው"[6]

ሠማር፣ መመራመር ከእግዚአብሔር ቃል ስለ መለኮት መረዳት የሚቻል፣ ጠቃሚና ተገቢም ነው።

ግን አምላክን ማወቅና መጽሐፍን ማወቅ አንድ ነገር ነውን? አምላክ ከመጽሐፍ ይበልጥ የለምን? ሰውስ አንባቢና ሰሚ ፍጡር ብቻ ነውን? እንግዲያው እግዚአብሔር በሰው ሕይወትና ልምምድ ውስጥ፣ በደስታና ቡነዙኑ፣ በሣቅና በለቅሶው፣ በእሺታና በእምቢታው፣ በብቻውና በቡድኑ፣ በቤቱና በሚዳው፣ በጉርምስናውና በርጅናው፣ በውጣ ውረዱ በውሎ አምሽቶው ... በዚህ ሁሉ ውስጥ ራሱን ይገልጣል። የፍጡሩን ልቡና ከርስቡሮ፣ በለሆሳስ ድምጽም ይሁን በነጐድጓድ ማንነቱን ያሳየዋል።

የሠነፅ ትንቢት "እግዚአብሔርን አላውቅም፣ መንገዱንም አልፈልግም" ብላ ግልብልቢት የምትከንፈውን እስራኤልን ሊከስም በማይችል ጽኑ ፍቅር በሕይወት ጥምዝምዝ ሰርጥ ሁሉ አየተከታተለ ራሱን የሚገልጥላት አምላክ ትርኢት ነው። እሷ ትፈረጥጣለች፣ እሱ ይከተላታል፤ ሚዳውን ትጋልባለች፣ ዳገቱ ላይ ቋጥኝ ይሆንባታል። በምሬት በትካዜ ታለቅሳለች፣ ዱር አውጥቶ ያባብላታል፣ ዐይኗ ዐሥር ቦታ ይቃብዛል፤ ለልቧ ይናገራታል። በሰው የርኅራኄ ገመድ፣ በፍቅርም ሰንሰለት ይስባታል።

ይህ ሁሉ ግብግብ ለምንድነው? የተባለ እንደ ሆነ የእግዚአብሔር ሙልስ በተደጋጋሚ "አንቺም አግዚአብሔርን ታውቂያለሽ" የሚል ነው። የእስራኤል ኩብለላ፣ ቃል ኪዳን አፍራሽነቷ፣ ሽምጥ ጋላቢነቷ፣ ውሽማ አሳዳጅነቷ ሁሉ እግዚአበሔርን ያለ ማወቅ ነው። የስሙን ፊደል ሳይሆን፣ የታሪኩን ዝና ሳይሆን፣ የፍልስፍናውን ጥልፍልፍ ሳይሆን፣ ማንነቱን፣ እርሱነቱን ነው። አሁን የሚሠራ፣ አሁን የሚሰማ፣ የሚያይ፣ የሚፈርድ፣ የሚያድን የማታደግ፣ ኪዳኑን የማያፈርስ የፍቅርና የጽድቅ አምላክ መሆኑን ነው።

ይህ ዕውቀት ከእርሱ ጋር በመኖር ይመጣል፣ በማየት በመቅመስ ይገኛል "እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ" ተብሏል። እግዚአብሔር በፊደል ገበታ የሚነበብ ብቻ ሳይሆን በሕይወት ውጣ ውረድ የሚቀመስም ጌታ ነው።

እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ኑ፣
ወደ ውሆች ኑ፤
ኑና ግዙ ብሉም[7]

ይህስ ይሁን፣ ሕያው እግዚአብሔር በሕያውነቱ ከምድር ዐፈር ከተሠራው ሰው ጋር ጥልቅ ዝምድና ተጨባጭ ግንኙነት የሚያደርግ ከሆነ፣ በዚህም መንገድ የሚታወቅ ከሆነ እንግዲያው የመጽሐፍ ንባብ የአዋቆች ትንተና ምን ያስፈልጋል ቢባልስ? ይህን ሁለት ፊት ዕውቀትስ እንዴት እናጋጥመዋለን ቢባልስ?

የመጽሐፍ ዕውቀት እኩ የብዙ ሕይወት ልምምድ ዕውቀት ስብስብ ነው፣ ስብስብነቱም የጠለለ የጠራ፣ ሰባት ጊዜ ተፈትኖ እንደ ተጣራ ብር የሰከነ ነው። የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ፣ የዮሴፍ፣ የዳዊት የጴጥሮስ፣ የጳውሎስ ወዘተ ... የሕይወት ልምድ የእስራኤል፣ የአሦር፣ የባቢሎን፣ የግሪክ ሕዝብ አመጽና ልመና፣ ቅጣትና ምሕረት ታሪክ ሁሉ የተከማቸበት ዕውቀት ነው።

"የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጻፈ"[8]

ሴላ ጥምረት ደግሞ እነሆ፤

እግዚአብሔር ሕያው ነው፤ የእግዚአብሔር ቃልም ሕያው ነው። የሁለቱ ሕያውነት ምን ዐይነት ሕያውነት ነው? የአንዱ እግዚአብሔር ሕያውነት ነው። በእጦትና በበረከት፣ በደስታና በጎዘን ጥልቅ መንፈሴን ዘልቆ የሚናገረኝ የዛሬ አምላክ፣ በመጽሐፍ ቃል መንፈሴንና ነፍሴን መርምሮ በሕያውነት ዛሬ የሚናገረኝ ራሱ ነው። ልዩነቱ በሕይወት ገጠመኝ የማገኘው ዕውቀት ማጥለያው የመጽሐፍ ዕውቀት ሲሆን፣ የመጽሐፍ ዕውቀት መተግበሪያው የሕይወት ውጣውረድ መሆኑ ነው።

አንግዲያው እኔ የመጽሐፍም የሕይወትም ተማሪ ነኝ። መምህሬ ግን የሁለቱም ባለቤት የሆነው ያው አንድ አምላክ ቅዱስ መንፈስ ነው። ልመናዬም እንዲህ የሚል ነው፡-

አቤቱ ፈጣሪ፣ መጋቢ አሳዳሪ፣ ዐዋቂ አምላክ ሆይ፤
በሣር በቅጠሉ፣ በዐፈር በጠጠሩ ሁሉ አስተምረኝ፤
አምላኬ ሆይ የጠለለ የተሰናዳ ዕውቀትህን ከገዘታህ
እየገመስህ ስጠኝ።
አና ጌታዬ ሆይ የምለምንህ
በሁለቱም የምበረታበት ስል ልቡና፣
ስንዱ መንፈስም ለግሠኝ ብዬ ነው።
ሥጋ በሆነው ቃል በክርስቶስ ኢየሱስ ስም

የጥቅስ ማውጫ

1. ዮሐ 5፥39 (አመት)
2. ማር 12፥24 (አመት)
3. ነህ 8፥8 (ነባሩ)
4. ሐሥ 18፥4 (አመት)
5. ሐሥ 18፥28 (አመት)
6. 2ጢሞ 3፥16 (አመት)
7. ኢሳ 55፥1 (አመት)
8. ሮሜ 15፥4 (አመት)

የመልእክት ያለህ! የሚዛን ያለህ!

ዜማ ልቡናን ሠርስሮ የሰውን ውስጠኛ መንበር የመያዝ ዐቅሙ ብርቱ ነው። እውነት ያዘለ፣ መንፈስ ቅዱስ የረበበት ከሆነ ደግሞ አስረኞችን የሚፈታ፣ እንቅጥቅጦችን የሚያበረታ፣ የነፍስ ዕውራንን የሚያበራ፣ ታምር የሚሠራ ጸጋ ነው። በቀድሞውም በአሁኑም ዘመን የሚጻፉ፣ የሚዘመሩ፣ ውብ መዝሙሮች ስላሉ ደስ ይለኛል። እኔ መዝሙር እወዳለሁ። ዘማሪ ነበርኩና ነኝ። የነበርሁት በመደበኛው የቤተክርስቲያን መዘምራን ቡድን ውስጥ አብሮ ቋሚ ሆኜ ጥንት ነው። የሆንሁት ደግሞ አሁን ከዚያ ወጥቼ በነጠላ ለአምላኬ ብቻ በሚሰማ መንገድ በለሆሳስ ነው። ድምፄ ለሰብአውያን እጅግም የሚጥም ባለመሆኑ (እኔም እንኳን የምሰማው በትዕግሥትና በርኀራኄ ነው) የልብ ምት ለሚያዳምጥ ብቻ መቅረቡ ተገቢ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቤተክርስቲያን መዝሙሮችና ዘማርያን የንግግር፣ የውይይት የትችት፣ የብስጭት፣ የአድናቆት፣ የጥያቄ፣ የአስተያየት የወዘተረፈ ርዕስ መሆናቸው ግልጽ ነው። በዚሁ የአስተያየት ጎርፍ ውስጥ ትንሽ ገባር ወንዝ ልጨምር። ባንድ አቅጣጫ ብቻ፣ ይዞታውን በሚመለከት።

የመዝሙሮቻችን ይዞታ (በውስጣቸው የተሸከሙት መልእክት) ምን ይመስላል? ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው? ነገረ መለኮታዊ ፋይዳው ምን ያህል ነው? (በጨዋ አነጋገር «ትምህርቱ ምን ያህል ጠቃሚ ነው?» አስተምህሮው ምን ያህል ጤናማ ነው? መልእክቱ አስተያየቱ ምን ያህል ሚዛናዊ ነው? ምን ያህል ምን ያህል..... ለምን ምን ያህል ተባለ የተባለ እንደሆነ ሁል ጊዜም እቅጭነት ስለማይገኝ ለአቅጩ የተዳረሰበትን ቅርበት መጠን መገመት ብቻ ስለሚያስፈልግ ነው። በመጀመሪያ ልናስብ ይገባናል ብዬ የማምነው መዝሙር መናገሪያ

መሆኑን ነው። በመዝሙር መናገር አለብን ብዬ አምናለሁ። የንግግሩ አቅጣጫ ሁለት ነው። ወደ ላይና ወደ ጎን። ቅዱስ ጳውሎስ ይደግፈኛል፤ በኤፌ 5:19 ላይ «በመዝሙር ... ተነጋገሩ» ይላልና። «እርስበርሳችሁ ተነጋገሩ፣ ለጌታም... ተቀኙ» እንግዲያው፣ ንግግር፣ መልእክት፣ አሳብ፣ ይዘታ የሌለው መዝሙር የክርስቲያን መዝሙር አይደለም። ለምሳሌ

«ወደ ሰማይ ብሄድ በምድርም ላይ ብዞር
ደስ ይለኛል በጣም ገባኝ ይሄ ምስጢር
መሄድም መዞርም ሁለቱም አንድ ነው
ጌታዬ ይመስገን ምስጢሩም ይኸው ነው።»

ይህ <መዝሙር መሳይ> ባለ አራት ስንኝ የወል ግጥም ነው። ቃላቱ እንግዳ አይደሉም፣ ግጥሙ ቤት ይመታል፤ በምንታርቦ ኪ ቦርድ በጥሩ ዜማ ጎበዝ ተጫዋች፣ እየተጫወተው አንድ የታወቀ ዘማሪ በጣፋጭ ድምፁ ቢያዜመውስ? የክርስቲያን መዝሙር ላይባል ነው? በፍጹም ሊባል አይገባውም። ምንም መልእክት የለውም፤ ወይም መልእክቱ በጭራሽ ግልጽ አይደለም። «እንዴ ጌታዬ ይመስገን ይላል እኮ» ይበላ! «እንዴ በጉባዔ ስንዘምረው 'ኮ ላባችን ጠብ እስኪሚል ተባርከንበታል።»

የሆነው ሁሉ ይሁን ይሄ የክርስቲያን መዝሙር አይደለም። የክርስቲያን መዝሙር በውስጡ ፍሬ ያዘለ፣ የሚያስተላልፈው መልእክት ያለው፣ ተናጋሪ ነው። ወይ ለአምላክ፣ ወይ ለሰው፣ ወይ ለራስ መናገር አለበት። እንግዲያው አንድ ያየሁት <በሽታ> ለመዝሙሮቻችን መልእክት አዘልነት አለመጨነቅ ነው። ድምቀታቸው፣ ጣፋጭነታቸው ቅንብራቸው...ላይ እያተኮርን የሚሉት ነገር ላይ የምንሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ ቅር ያሰኛል። በቅርጽ ብቻ ልንኖር አንችልም። ቅርጽ እንዲያውም የሚያስፈልገው ይዘታን ማቅረቢያ ገበታ ለመሆን ነው። እንጀራ በሌለበት መሶብ ብንሸላልም የራብተኛ ጠኔ ማባባስ ነው።

በክርስቲያን መዝሙር ውስጥ ንግግሩ የሚመለከታቸው አራት ወገኖች ያሉ ይመስለኛል። በተውላጠ ስም ልግለጻቸው፦

እሱ
እኔ
እኛ
እነሱ

እርሱ ማለት ያው እርሱ ነው። ፈጣሪ አምላካችን ጌታና አዳኛችን፣ ወዳጅ አለኝታችን፣ ልዑል እግዚአብሔር፣ ሥሉስ አምላክ። መዝሙሮቻችን ስለ እርሱ ለእርሱ መናገር አለባቸው። ውዳሴውን፣ ቅዳሴውን፣ አምልኮውን ምስጋናውን ማቅረብ አለብን። ይህን ስናደርግ ምን እንደምንል እያወቅን ሊሆን ያስፈልጋል፤ በእውነትና በመንፈስ አምልኩ ተብለናል። ለእርሱ ልንለው የፈለግነው፣ የመጣብን ነገር ምንድን ነው? ምን ማለታችንስ ነው? ይህን ስናገር አንድ ጥያቄ ሊነሣ እንደሚችል አስባለሁ። ለእርሱ የምናገር ከሆንሁ የትርጉም ጉዳይ ምን ያህል ያስፈልጋል? እርሱ የማይገባው ነገር የለማ!» የሚል። አዎን እውነት ነው፣ እግዚአብሔር ማብራሪያ አይሻም። ግን ለእርሱ ስንነግር የሚሰሙ፣ ጆሮአቸውን ጥለው የሚያዳምጡ ስላሉ ንግግራችን ፍቺው የሚታወቅ ሊሆን ጥሩ ነው። በእኛ ምስጋና በእኛ ጸሎት በለቅሶአችንና በሳቃችን ሌሎች እንዲገቡበት አብረውንም ለልዑል እንዲናገሩ ከፈለግን የምንለው መታወቅ አለበት።

የምናገረው ግን ለእኔም ጭምር ነው። ከነፍሴ ጋር ከልቡናዬ ጋር በዝግታ፣ በጉርምርምታ በሐሜት በፍንደቃ፣ በትዝብት በጥሞና። ዘማሪው ዳዊት

«ነፍሴ ሆይ ለምን ትተክዥያለሽ
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በአምላክሽ ላይ አድርጊ»

እያለ የምስጢር ሹክሹክታውን ይፋ ያወጣልናል።

የክርስቲያን መዝሙር ስለ ራስ በጭራሽ አይነገርበት ሊባል አይቻልም። ሲነገር ግን እውነታን ይከስት። ተጨንቆ ቢሆን ተጨንቄያለሁ ይበል፣ ተጠራጥሮ እንደሆነ ግራ ገባኝ ይበል። ይህን ሁሉ ብሎ ግን የተስፋን የዓላማን የድልንና የዕረፍትን ጮራ ይፈንጥቅ። የክርስቲያን መልእክት ዓይኑን ሳይሽ እውነትን የሚጋፈጥ፣ የእምነት ዓይኑን ከፍቶ ደግሞ ተስፋን የሚማትር፣ የምስራቹንም የሚያስተጋባ ነውና።

መሬቱ ላይ ያለሁት ደግሞ <እኔ> ብቻ አይደለሁም። እንደ እውነቱ ከሆነ አዲስ ኪዳን የተሞላው «እኛ» በሚል ቋንቋ ነው። እግዚአብሔር ለዓለሙ የሰጠው ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ቢሆን ክርስቶስ ደግሞ በመንፈስ ጎይል የሚራመድ አዲስ ማኅበረሰብ መሥርቶ ሄደ። በመዝሙራችን ስለዚህ ማኅበረሰብ ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለ ወንድሞች ስለ እህቶች ፣ ስለ አባቶች ስለ ልጆች የማንናገር ስለምን ነው? የማኅበረሰቡ ዓላማ፣ ውጣ ውረዱ ብርታት ድካሙ ኑሮውና ተስፋው ለምን አይዘመርም? ቤተክርስቲያንን ወቃሽ፣ አጎልማሽ መልእክት እንዴት ጠፋ? ስናስብ፣ ስንፀልይ፣ ስንዘምር፣ ለዘላለሙ ላንፋታ የተጣመርነውን የሕዝብ አይነት ሳንነካ እንዴት እንንቀሳቀሳለን?

በጣም በሚያጠያይቅ መጠን መዝሙሮቻችን ግለኞች ናቸው። ተውላጠ ስማችን እኔ ብቻ ነው። ውጊያውም ድሉም፣ እጦቱም ባርኩቱም ጸሎቱም ምስጋናውም እኔ ብቻ አልሆነምን? ልመናዬ ወቀሳዬም «እባካችን አብረን እንደምንኖር፣ ለሞት ለሽረትም እንደተቆራኘን የሚያገናዝብ ንግግር ይኑረን» የሚል ነው።

እሱ እኔና እኛ ባንድ ላይ ለዓለሙ መልእክት አለን፤ ለእነሱ። በየታክሲው ውስጥ ተሳፍሬ ስሔድ፣ በየመዝሙር ቤቱ ደጃፍ ጆሮዬን ስጥል አላፊ አግዳሚውን አብሮ ተሳፋሪውን መዝሙሮቻችን ምን ይሉት ይሆን? እያልሁ እጠይቃለሁ። በዜማቸው ብርታት ያስጨፈሩት ካልሆነ በስተቀር

አንዳንድ ጊዜ ሁነኛ መልእክት አያገኝም ብዬ እፈራለሁ። ፍራቴ እውነት ካልሆነ አጽናኙ። እውነት ከሆነ እንወቃቀስ። በምድር ላይ የምንኖረው፣ በየእሁዱ ቤተክርስቲያን ለመሳም ብቻ አይደለም። «ክጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራንን የእርሱን በጎነት ለመናገር» እንጂ። ለምን መዝሙሮቻችን በግልጽና በብርታት አይናገሩም? ለምን ትኔዎቻችን የሰውን ውጣ ውረድ፣ የነፍሱን ሃቅ ፍለጋ ጥማት አያነሱም? ለምን አይሞግቱትም? ለምን አያመለክቱትም? ለምን አያውጁለትም? ክርስቶስን ለምን አያስተዋውቁትም? በወዳጅ ልቦና ተርበው የነጠረውን እውነት ለምን አይነግሩትም? ለምን?ለምን? ለምን። እስካሁን ከተባለው ሁሉ ጋር የሚያያዝ ሌላ ዋና ነገር የመዝሙሮቻችን አንድ አይነትነት ነው። ያለመጠን አንድ ዐይነት ሆኑ። የዜማ ስልትና የዘማሪው ማንነት ካልሆነ በስተቀር አንዱን የሰማ ሌላውንም የሰማ ያህል ሊሆን ነው።

ዘመኑ ራሱ የሚነትተው አንድ ዓይነት መልእክት ይኖር ይሆናል። ይህም እንኳ ቢባል በሕይወት ጎዳና ላይ የምናልፍባቸውን ስንትና ስንት ገጠመኞች ጨፍልቆ አንድ ብቻ ትዕይንት ማቅረብ ተአማኒነት ያሳጣል። የመጽሐፍ ቅዱስ ዘማሪዎች የነበራቸውን የመዝሙር ልዩ ልዩነት (Variety) ስመለከት የኛን አንድ ቀለም ቤት መቀበል ቸገረኝ። ለምሳሌ የመዝሙረ ዳዊትን የመጀመሪያ ሃያ መዝሙሮች እንኳ በወፍ - በረር ብንቃኝ

ትምህርት	መዝ 1 መዝ 15
ጦርነት	መዝ 3 መዝ 18
አድናቆት	መዝ 19
ምስጋናና ትምክህት	መዝ 9 መዝ 16
ትንቢት	መዝ 2

የሕይወት ምልከታ	መዝ 8
ልመና፣ አቤቱታ	መዝ 12 መዝ 13
ቡራኬ	መዝ 20

ተደባልቀውና ተለያይተው በየተራቸው ተደርድረው እናገኛለን። የሰው ልጅን ጉራማይሌ ኑሮ፣ የጻድቁን ሰው ውጣ ውረድ የሚወክሉ ትዝብቶች ናቸው። የኛን ሕይወት ባንድ ምት እንዲፈስስ ማን ፈረደበት ወይም ፈረደለት?

የመዝሙሮቻችንን የመልእክት ዝመት (አጋድሎ) የመረመርን እንደሆን የሚዛን ቀውስም ይታየናል።

- ከማነበሩ ይልቅ ግለሰቡ የገነነበት
- ከዘለቄታው ይልቅ የዛሬው የደመቀበት
- ከባሕርይ ግንባታ ይልቅ ስኬት የተተኮረበት
- አዳኙ ክርስቶስና ጌታ የሆነው ክርስቶስ በሚዛን ያልቀረበበት
- የኢዮብ 40 ምዕራፎች ገሸሽ ተደርገው 42ኛው ብቻ የተሰበከበት አካሄድ ይታያል።

ያልነውን ሁሉ ብለን ስንቋጭ መዝሙር መዘመራችንንና መስማታችንን እናቁም ወደሚል ድንቁርና መግባት ከቶ የለብንም። ይልቁን የመልእክት ባለጠጋውን ጌታ ፍሬ አሳብ እንዲሰጠን፣ የውዳሴን መንፈስ እንዲያፈስልን እየለመንን ወደ ክቡር ስግደት እንደግ። ድምጽ አውጥተን በጉልህ የምንዘምርም፣ በቀስታ በቤታችን የምንዘምርም መዘመራችንን መቀጠል አለብን። ከልባችን።

እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት
የሞቱት አይደሉም፣

ወደዘመታው ዓለም የሚወርዱም አይደሉም።
ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም
እግዚአብሔርን የምንባርክ እኛ ነን።
እግዚአብሔር ይመስገን።

(መዝ 115፥17-18)

የቅን ተቀባዮች ድርሻ

እንደ እሳት ÷ እንደ ነፋስ ነው መንፈስ ቅዱስ። የታይታ የግብዝነት ገለባችንን እያቃጠለ እግዚአብሔርን ብቻ የምንፈራ ጓዘ ቀላል ያደርገናል። በተለመደ ድግግሞሽ ሥራና አምልኮ ታክታ ያንቀላፋች ነፍሳችንን በንጹህ ቀዝቃዛ ነፋስ እያርገበገበ ያነቃታል። ለእውነተኛ ሥራ በብርቱ ትታጠቃለች። የእግዚአብሔር መንፈስ የንጽህና የኀይልም መንፈስ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ያለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ድሃ ናት ደካማም። መንፈሳዊ ነገር ያለ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ይሠራል? ምን ትጋት ቢኖራት÷ ምን ገንዘብ ቢኖራት÷ ቤተ ክርስቲያን ያለ ሰማያዊው መንፈስ የምትሮጠው ሁሉ የእብድ ሩጫ ነው፤ ፍሬ ከርስኪ።

በቅርብ ዓመታት በአገራችን ባለች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማስብ፣ መጸለይ፣ መነጋገር ዐይነተኛ መልክ ሆኗል። እግዚአብሔር ይመስገን። ይህ እንዳለ ሆኖ ስለ ስጦታዎችና የስጦታዎቹ አጠቃቀም ብዙ ንግግር የአስተሳሰብ ስልቶችና አንዳንድ ጊዜ ጠንካራ ውዝግቦች መነሣታቸው አልቀረም። ቤተ ክርስቲያን መንታ ወልዳ ቀኝና ግራ እየተጐተተች ያለች ይመስላል። ጉተታው ሲበረታባት አንዴ የቀኙን ሌላ ጊዜ የግራውን እየተቆጣች ታቃስታለች። አንዳንዶች "ከዚህ ሁሉ ስቃይ ለመገላገል አንዱን ልጅ ጥለሽ አንዱን በደንብ አሳድጊ" ይሉዋታል (ባልወለደ አንጀት)። ሌሎች ደግሞ "በሁለቱ ጠብ ውስጥ አትግቢ ያሸነፈ ይደግ በኋላ ለባለድሉ ታጨበጭቢያለሽ" ይሏታል፤ የመንታ እናት ምን ትሁነው።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ጉዳይ በሙቀት ማነጋገር ከጀመረ ቆየ። እንዳይሆን ብንፈልግም እንኳ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ምእመናንም በስጦታዎቹ ጉዳይ አንድ ወጥ አስተሳሰብ ገና አላገኘንም። ብዙ ልዩ ልዩ

አቋሞች፣ አመለካከቶች፣ አሠራሮች፣ ስሜቶች እየበቀሉ ነው። ቤተ ክርስቲያንም የመንታ ብቻ ሳይሆን የአርባ ሃምሳ አስተሳሰብ መናኸሪያ ነው የሆነችው። ለመሆኑ ምን እየተባለ ነው?

- ጊዜው የመንፈስ ቅዱስ ነው፤ ትኵረታችንም እርሱ ላይና ስጦታዎቹ ላይ መሆን አለበት።
- ባሁኑ ዘመን የፈውስ፣ የመገለጥ፣ የተአምራት ስጦታ በይፋ ካልታየ እንዴት ወንጌል ይሰበካል?
- በመንፈስ ስጦታ ስም በየቤተ ክርስቲያኑና በየቤቱ ስንት ውል የለሽ ድብልቅልቅ እየታየ ነው?
- "ስጦታ አለን" ባዮቹን እናውቃቸዋለን፤ ሕይወታቸው እንኳ ከእግዚአብሔር ጋር ከሰውም ጋር አያኖር
- ጩኸት፣ ሁካታ በዛ የምትሉን ያ እኮ የሕይወት መኖር ምልክት ነው፤ መቸም ከሞት ይሻላል።
- መንፈስ ቅዱስ አእምሮን አስተሉ እንደ እብድ ያስጮኻል ካላችሁኝ እኔና እናንተ የምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ ይለያያል ማለት ነው።
- ጌታ የቀባቸውን ተስፋ ከማስቆረጥ፣ የሚያድጉበትን መንገድ መፈለግ አይሻልም?
- ጌታ በአገራችን በድንቅ መሥራት ሲጀምር፣ ከማያምኑ ሰዎች ጋር ተሰልፎ ቤተ ክርስቲያንን መውገር ምን ይባላል?

ንግግሩ፣ ክርክሩ፣ ፍርሃቱ፣ ጥርጥሩ፣ ውግዘቱ፣ ባርኮቱ፣ እንደዚህ እያለ ይቀጥላል። ወንድሞቼ እና እህቶቼ መነጋገራችንን አትጥሉት። እንኳን በየፊናችን አድገን እየቀል አንብበንና ተለማምደን ቀርቶ እያንዳንዱ ሰው በየራሱ ውስጥ ስንት እሰጥ እገባ ያካሂድ የለ? ውይይቶቻችን "ከሙቀት ይልቅ ብርሃን" እንዲጨምሩልን እንማጠን እንጂ ተራርቀንና ተኰራርፈን ዝም አንባባል።

በዚህ መንፈስ እኔ አንዳንድ መንደርደሪያ ጠቦች ሳነጣጥፍ፡-

3. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቹን አጥብቀን እንሻ

አሳፋሪ በሆነ ሥጋዊነት፣ የማያምኑትን በሚያሰደንግጥ ሥርዐት አልበኝነት እና በትዕቢት በተዋቀረ ወገናዊነት ለተተራመሰችው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል።

"መንፈሳዊ ስጦታን ... በብርቱ ፈልጉ" 1ቆሮ 14፥1

ሰዎች በመንፈሳዊ ስጦታ ስም ስንት ገለባ ይበትናሉ ብለን ከስጦታዎች አንሸሽ፣ ጭቅጭቁና ድብልቅልቁ ስለሚሰለቸን "ነመን በጤና" በሚል ዐይነት ከሕያው እግዚአብሔር በረከት ልንርቅ አይገባንም። ቤተ ክርስቲያን የኛ ክለብ አይደለችም የክርስቶስ ማኅበር ናት። እርሱ ደግሞ የሚሠራው በስጦታዎቹ አማካይነት ነው። ራስ ሆኖ ሌሎቹን ብልቶች በየቦታው በትክክል እንዲሠሩ ያዛል። አንድም ብልት ያለ ጥቅም አይቀርም። "ከጥቅሙ ጣጣው በዛ" ብለን ለመቁረጥ፣ ለመርሳት፣ ለማቃለል መሞከር አካሉን ክፉኛ ይጎዳዋልና የተበላሸውን በትእግስት እያቀናን ስጦታዎቹን እናበረታታ።

4. ባለ ስጦታዎቹንና የሚቀርበውን አገልግሎት ለመፈተን አንፍራ።

ከፍተሻ፣ ከምርመራ፣ ከግምገማ በላይ የሆነ ማንም የለም። ንጽሕት ሆና ለክርስቶስ የምትቀርበው ሙሽራ ከራስ ጸጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ድረስ እየተመረመረች መጽዳት አለባት። መገለጥ መጣልኝ፣ ራእይ ተሰጠኝ፣ ጌታ ተናገረኝ የሚለውን ሁሉ ሰምተን በጥቅጥቅ ማጥለያ የእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ገፈቱን ከጥሩው ልንለይ ይገባል፤ አድካሚ ሥራ መሆኑን ሳንረሳ።

ለመለካትና ለመፍረድ መመዘኛ ያስፈልገናልና በዚህ ሥራ የሚረዱንን ለጊዜው ሦስት ነገሮች ብቻ ልጥቀስ፡-

❖ ኢየሱስ ብቻ ጌታ እንደሆነ የሚያሳላ ነውን?

ባለስጦታውን ወይም ሌላ ታዋቂ አገልጋይ ወይም አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይ ቡድንን የሚያደምቅ ውዳሴ ከንቱ የበዛበት ከሆነ በወፍራም መጥረጊያ ገለል ማድረግ ነው። ልንሰብክ ልናነግሥ የተጠራነው ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ነው። 2ቆሮ 4፣ 5 1ኛ ቆሮ 12፥1

❖ **የክርስቶስ መስቀል የደኅንነታችን መሠረትና የኑሮ መመሪያችን መሆኑን ይገልጣልን?**

ምንም ዐይነት ልዩ መንፈሳዊነትና በጎ ምግባር ለደኅንነታችን አስተዋጽኦ አያደርግም። ያው መስቀል ብቻ ነው ያዳነን። ይህም ብቻ አይደለም ፍለጋውን እንድንከተል ምሳሌ ትቶልን የሄደው ጌታ ኢየሱስ ጎዳናችን የመስቀል መሆኑን አበክሮ ተናግሯል። ችግር፣ ሥቃይ፣ እንግልት፣ እጦት የሌለበት በምድራዊ በረከት የተንበሸበሸ ቀላል ሕይወት ተስፋ አልገባልንም። ሞቱን ተሸክመን ነው የምንዞረው።

"መስቀሉን ተሸክመን፣ መከራን ታግሰን፣
አክሊሉን እንድንጭን እንጓዝ ወደ ሰማይ"

መዝሙራችን ነው።

❖ **የእግዚአብሔርን ፍቅርና ጽድቅ ያመጣጥናልን?**

"በጽድቅና በፍርድ በምጎረትና በርኅራኄ አጭሻለሁ አንቺም እግዚአብሔርን ታውቂያለሽ" ብሎ በነቢዩ በሆሴዕ በኩል ለእስራኤል የተናገረው እግዚአብሔር ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይህን ጻድቅና ርኅሩኅ አምላክ እንድናውቅ ያግዙናል። አምላካችን እንደ ጨፍጋጋ ማስፈራሪያ ለማስደንገጫነት ወይም "ባለስጦታዎቹ" ከሚያዙን እንዳንወጣ ለመግረፊያነት የተቀመጠ ጨንገር ካደረግነው ትልቅ መነባበት ሆኗል ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን የቅዠቶቻችን ሁሉ አስተናጋጅ የምኞቶቻችን ሁሉ አቅራቢ ተላላኪ አድርጎ የሚያሳይ አገልግሎት ስለ እግዚአብሔር የሚሰልልን የተጭበረበረ

ሥእል ነው። በስጦታዎቹ አመካይነት የሚሰጠው አገልግሎት በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን እግዚአብሔርን እንድናውቀው የሚረዳ ሊሆን ይገባል።

5. ስጦታዎቹንና በስጦታዎቹ የሚያገለግሉትን እንለይ።

አንዳንድ ጊዜ በቆሻሻ ኮት ኪስ ውስጥ ሺህ ብር ይገኛል። እግዚአብሔር ከቸርነቱ የተነሣ መንፈሱን፣ ስጦታውን ለደካሞች ላልበሰሉ ሰዎች ለማያስተውሉ ሕጻናት ይሰጣል። እነርሱ ከአያያዛቸው የተነሣ ቢያስነቅፉትም እኛ የጌታን ክቡር ዕቃ ልናጣጥለው አይገባም። ባለ ስጦታ መሆን ማለት ፍጹምነት አይደለምና አገልጋዮቹን እየገሰጽንና እየመከርን አገልግሎቱን ልንጠቀም ያስፈልጋል። ደግሞስ ማን አድነ ጨርሷል? በልዩ ልዩ ጸጋ የምናገለግል ሁላችን በእኛ ምክንያት ቅዱሱ ስጦታ እንዳይረክስ እንጠንቀቅ።

6. ድፍረት ይቅር፣ ቡድናዊነት ይወገድ

መንፈስ ቅዱስ ትሁት መንፈስ ነው፤ ወልድን ሊያከብር ይሠራል። አብና ወልድ ያሉትን ያጸናል። እርሱ የተጠጋቸውን ሰዎች በምንም ዐይነት ትዕቢትን ሊያስተናግዱ አይፈቅድላቸውም። አንደበታቸውን በርኅራኄ ያለዝባል። ለማፍረስ ሳይሆን ለማነጽ ይተጋል። ይህ እንዲህ ከሆነ ታዲያ አንዳንድ ባለ ስጦታዎች ለምንድን ነው ሰው የሚላቸውን የማይሰሙት? ለምንድን ነው ሲናገሩ ለነገ የማይሉት? ሥጋዊነት እያሸነፋቸው ነው። ስመ እግዚአብሔርን የሚጠራ ሰው በንግግሩ ጠንቃቃ ካልሆነ ወየው! ወየው! ስንት ጥፋት በጎዳናው ላይ አለ። ሌሎቻችንስ እነዚህን ወንድሞችና እህቶች የምንናገርበት መንፈስ ምን ዐይነት ነው? አገልግሎታቸውን ለማደባየት፣ ሥራቸውን ሁሉ ለማኪያኪያስ በንቀትና በጥላቻ ከሆነ ወየው ወየው!!! ንጉሥ ዳዊት ያንን በእብሪትና በቅናት የተበላሸ ሳኦልን "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን አላነሳም" ማለቱ የሳኦልን ሥራ ማጽደቁ አልነበረም፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንጂ።

ከዚህ ጋር በጣም እያስፈራኝ የመጣው ጭራቅ ቡድናዊነት ነው። አካሄዳችንን ልብ ያለው ሰው ሁላችንም ጥግ እየፈለግን የአንድ ጎራ ጭፍራ የመሆን አዝማሚያ እያሳየን እንደሆነ ያውቃል። ይህ ምንድን ነው የተባለ እንደሆነ ትንሽነት ነው። የጳውሎስ ነኝ፣ የኬፋ ነኝ፣ የአጵሎስ ነኝ ወዘተ... ። የዛሬዎቹን ትልልቅ መሪዎች ስም ቀይሩበትና በሉት። ያው ያልጸዳ ሥጋዊነት ነው። ወንድሞቼና እህቶቼ የትኛውም ጎራ ለመጠለል አልተሰጠንም። ቶሎም ይሁን ዘግይቶ የሚያፈስ ቀዳዳ አታጡበትም። ይልቅ "ሁሉ የእናንተ ነው እናንተም የክርስቶስ ናችሁ" በተባለበት መንፈስ ቀኙንም ግራውንም በክርስቶስ ዐይን ብንመለከት በፍቅር ብናቅፍ እንድናለን።

2. ስጦታዎች ብዙ ዐይነት እንደሆኑ ልብ እንበል

እየደጋገምን የምናነላቸው፣ የምንሟገትባቸውና የምናነላቸው ስጦታዎች ሦስት ወይም አራት ይሆኑ ይሆናል፣ ፈውስ፣ ትንቢት፣ ልሳናትና ዕውቀት መግለጥ። እነዚህ ተገቢ ሥፍራና ንጹህ አቀባበል ሊሰጣቸው ያስፈልጋል። ሆኖም በሌሎቹ ኪሳራ እነርሱን የምናደምቅ ከሆነ ከሚዛን ወጥተናል።

እቤት ድረስ መጥቶ ከባለቤቱ ጋር ያደረገውን የነገረኝን የአንድ ወንድም ታሪክ ልንገራችሁ "ባለቤቴ ልጅ ትወዳለች፣ ጎዳና ላይ ራቁታቸውን የሚሄዱ አባት እናት የሌላቸውን ልጆች ወደ ቤታችን ወስደቻቸው፣ ሳታማክረኝ በማድረጓ ግር ቢለኝም ተስማምተን ማሳደግ ቀጠልን በኋላ ቆይቶ ሌሎች ተመሳሳይ ልጆች እናደና ልባችን ይነካል ጨምረን ወስደን ማሳደግ ቀጠልን፤ በየጊዜው አሳስችል እያለን ስንቀበል ስናስገባ አሁን ስንት ልጆች እንደምናሳድግ ታውቃለህ 14 አሉን አለኝ። ደነገጥኩ፣ ደስ አለኝ፣ አፈርኩ።

እነዚህ ባልና ሚስት የራሳቸው አራት ልጆች አሉዋቸው፤ ኑሮአቸው ትልቅ የሚባል አይደለም። ቤት ቢጠባቸው ተከራይተውላቸው ልጆቹን

ያሳድጋሉ። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ እንዳደረገላቸው ነግሮኛል። በስንቶቻችን ቤተ ክርስቲያን ፑልፒት ላይ ስለነዚህ ሰዎች ይነገራል? የመስጠት/ የልግስና ስጠታቸውን ምን ያህል ጊዜ እንነጋገርበታለን? ይህ ስጦታ እንዲኖረን ምን ያህል እንመኛለን?

7. አግባብና ሥርዐት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን አንርሳ

የውሃውን ምንጭ በተጠረበ ድንጋይ ለመድፈን አንነሳ እንጂ ቦይ ቀድደንለት ቢንዶለዶል ጥቅሙ ለሁሉም ነው። ያለበለዚያ አላፊ አግዳሚ በጭቃ እግሩ እየረገጠው ከብቱም አውሬውም እየፈነጩበት ያደፈርሱታል። የጠራ ውሃ ያለህ! (1ቆሮ 14)።

ይህን ካልኩ በኋላ የነፍሴ ምኞትና ሲቃ አንድ ብቻ ነው እርጅናችንን የሚያድስ፣ ፍዝነታችንን የሚያነቃ፣ አድርባይነታችንን የሚገስጽ፣ አታላይነታቸንን የሚፈውስ፣ ተታላይነታችንንም የሚያስወግድ፣ የመኖር የመሞት ዐላማ የሚሰጠን ባንድ ጊዜ ከስታራም ርኅሩኅም የሚያደርገን ቅዱስ መንፈስ ይውረድብን። አሜን! አሜን!

ይፈለጋል! የቁጣ ችሎታ ያለው

የእግዚአብሔር ሰው ማለት ድምፁን አለዝቦ፣ ዐይኑን አቅለስልሶ፣ ፊቱን አለስልሶ፣ በቀኝም በግራም ሰላምታ እየሰጠ፣ ለአላፊ ለአግዳሚው ፈገግታ እየረጨ፣ የሰዎች ክፋት ሰማይ ሲደርስ "የባሰ አታምጣ" እያለ፣ ቤተ ክርስቲያን ቆሽሻ፣ መቀመጫ ሲጠፋ መሐረቡን በአቧራው ላይ ጥሎ "ተቀመጡ" እያለ "ወተት ነጭ ነው? ጥቁር?" ተባብለው ሲጣሉ "ሁለታችሁም ልክ ናችሁ" እያለ፣ በመቅደሱ ውስጥ ውሾች ቢተኙበት "ሳስል ከእንቅልፋቸው እንዳላባንናቸው" ብሎ አፉን በመሃረብ እየለጐመ፣ ሸካራ ቃላትን ለምሳሌ፦ "ዘለፋ፣ ነጠላት፣ ቅጣት" የተባሉትን በተለሳለሱ ቃላት ለምሳሌ "ምክክር፣ የምርጫ ነጻነት፣ ተጽእኖ" በሚሉ እየለዋወጠ የሚኖር እሳት አልባ ፍጡር ነው። እውነት ወይስ ሐሰት? ሐሰት።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው ነበረ ሙሴ የሚባል። ልዑል አምላክ የሰጠውን ጽላቶች ከእጁ ጥሎ ሰበራቸው። ሕዝቡ በስንት መዋጮ የሠራውን የወርቅ ጥጃ አቃጥሎ ፈጨው፤ ትቢያውን በውሃ ላይ በተነው። ሕዝበ እስራኤልን የጣዖቱን ዐመድ ውሃ አጠጣቸው። ወደ ወንድሙ ወደ አሮን ዞር ብሎ "ይህ ሕዝብ ምን አደረገህ እንዲህ ዐይነት ፍዳ ውስጥ የምትከተው? አለው። ወደ ሕዝቡ ዞሮ "ተነሥታችሁ ወንድሞቻችሁን ግደሉ" አለ፣ ሦስት ሺህ ሰው ያን ቀን ሞተ። ከሁሉ የሚገርመው "በረከትን እንዲያወርድላችሁ በልጃችሁና በወንድማችሁ ላይ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሱ" ያለው ነው። "ግደሉና እጃችሁን ንጹህ አድርጉ" ማለቱ ነው፤ እንዴት ያለ ታላቅ ቁጣ ነው! እንዴት ያለ ታላቅ መንፈሳዊ ቁጣ ነው!

ሙሴ አንድ ምሳሌ ብቻ ነው፤ ሳሙኤልስ ቢሆን፣ አሞጽስ ቢሆን፣ ኤርምያስስ ቢሆን፣ ጳውሎስስ ቢሆን:: ከሁሉ ይልቅ ደግሞ ያ የደግነት ምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእውነተኛ ቁጣም ምሳሌ ነው::

የቁጣ ቴዎሎጂ ሳያስፈልገን አይቀርም::

ለመሆኑ እኛ ዘንድ የቁጣ መጠን አንሷል እንዴ? ቁጣማ እንዳለ በየመስኩታችን የሚትጎለጎለው ጢስ ይነግረናል:: ለምንድን ነው የምንቆጣው ነው ጥያቄው::

"ስንት ዓመት በጌታ የቆየሁት እኔ እያለሁ ትናንት የመጡትን ነው ቦታ የሚሰጧቸው"

"ጌታ የባረከኝ እንደሆን ለሁሉ ሰው ገንዘብ መበተን አለብኝ እንዴ? አላበዙትም!"

"የማን ብሔረሰብ ከማን ያንሳል? አስበው አይናገሩም?"

"እነሱ ሙስና ውስጥ ተዘፍቀው እኔ ትንሽ እንከን ቢገኝብኝ ይህን ያህል ማውገዝ ምን ይባላል?

ቁጣማ ሞልቷል፤ የቁጣችን ምክንያት ግን ምንድን ነው? "የእኔ ምኞት፣ የእኔ ክብር፣ የእኔ ስም፣ የእኔ ጥቅም" ማእከላዊ የሆነበት ቁጣ ከሆነ አሁን ከምንነጋገረው ጋር አይመጣጠንም::

የእግዚአብሔር ሰው የሚቆጣው ቡጉሊት ላይ ነው:: የሚቆጣውም እውነትን ለማጽናትና ስሕተትን ለመገሠጽ ነው:: እንዲያውም ይህ ሰው የሚቆጣው እግዚአብሔር ስለሚቆጣ ነው:: የአምላኩን ቁጣ ነው የሚያስተጋባ:: ወደ እግዚአብሔር በኩል ያለው ነፍሱ ከመሳሳቱ የተነሣ የአምላኩ ድምጽ ጮክ ብሎ እየተላለፈበት ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ታላላቅ የቁጣ ምክንያቶች በግርድፍ እናስተንትን ብንል ምናልባት ሦስቱ ጎልተው ይታያሉ::

1. በእግዚአብሔር ላይ ያለንን ታማኝነት ማጉደል (በእግዚአብሔር ላይ ማመንዘር) ሙሴ በምድረ በዳው ጉዞ (ዘፀ 32)
   - ነቢዩ ሆሴዕ ለኩብላይዋ ለእስራኤል የተናገረው (ሆሴዕ 1-2)
   - ጌታችን ኢየሱስ ለመቅደስ ውስጥ ነጋዴዎች የተናገረው (ማቴ 21)
2. በሰዎች ላይ የሚሠራ ግፍና በመጽ:- የፍትሕ ማዛባት በኢኮኖሚያዊ፣ በሥነ ልቦናዊ፣ በማኅበራዊ ግንኙነት የሚፈጸም በደል
   - አሞጽ ለጽዮን ዓለመኞች (አሞጽ 4)
   - ነህምያ ከምርኮ ለተመለሱ አይሁድ ባለጠጎች (ነህ 5)
   - ኢሳይያስ ለሕዝቡ (ኢሳ 58)
3. በሃይማኖት ስም የሚታይ አስመሳይነት፣ ግብዝነትና ማታለል
   - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሃይማኖት መሪዎች ላይ (ማቴ23)
   - ነቢዩ ሕዝቅኤል በእስራኤል እረኞች ላይ (ሕዝ 34)
   - ሐዋርያው ይሁዳ በሐሰተኞች አስተማሪዎች ላይ (ይሁዳ)
   - ነቢዩ ኤርምያስ በሐሰተኞች ነቢያት ላይ (ኤር 23)

እነዚህ የቁጣ ምክንያቶች ዛሬ እኛ ዘንድ የሉምን? ያሉ ከሆነስ የቁጣውን ድምጽ ጥርት ባለ ሁኔታ እየሰማን እያሰማንስ ነውን? ወይስ ተፈራርተን፣ ተከባብረን ተቀምጠናል:: ጎጢአት ባለበት ክብር የለም ሰውን መፍራትም የሞት መንገድ ነው::

በቤታችን፣ በቤተ ክርስቲያናችን፣ በጎብረተ ሰባችን ጽድቅ ሲጓደል፣ ፍትሕ ሲዛባ፣ ግፈኞች ከፍ ሲሉ ለመናገር በምንችልበት ሁኔታ መጠላትን ከመፍራት "እንዳልጠመድ" ከመስጋት የተነሣ ስንት ጊዜ እንተሻሻለን?

በቤተ ክርስቲያን የተከበረ ሰው ንጹህ ያልሆነ ሥራ ሲሠራ እያየን በጽድቅ ሚዛን በመለካት ፈንታ ሚዛኑን ለርሱ ስንል እናስተካክልለታለን:: "እውነቱን ተናግረን በመሸበት በማደር" ፋንታ በእውነት ሽያጭ ገንዘብ

በቁጭት ተነሥተን የምንሆነው ነገር አይመስለኝም። ልስላሴንና እንደ ድመት መፍረግረግን፣ አድርባይነትን እድሜ ልካችንን ስንለምድ ኖረናልና የእውነት ጭፍራ ለመሆንም መሠልጠን ያስፈልገናል። "የመንፈስ ቆዳችን" የእውነትንና የሌብነትን አካል ዳስሶ ለመለየት የሚሰማው መሆን አለበት።

ይህ "የጽድቅ ሰውነት" እንዴት ይገኝባል? እግዚአብሔርን በማወቅ ነው፣ ባሕርዩን በመረዳት ነው። በፍጹም ብርሃን ውስጥ የሚኖረውን የሰውን ፊት አይቶ የማያዳላውን የማይለወጠውን አምላክ ማወቅ ስንጀምር ስሜቱን እንጋራለን። የኀጢአትን አጥፊነት ስናውቅ ልባችን ይጨክናል። ኀጢአት ላይ ፈርደን ኀጢአተኛውን ለማዳን። በሁሉ ላይ የመጨረሻው ባለሥልጣን ልዑል እግዚአብሔር እንደ ሆነ ስንረዳ ትናንሽ መሳፍንትን አንፈራም።

"ሰዎችን አትፍሩ" አለ ጌታ ኢየሱስ "ቢበዛ ምን ያደርጓችኋል? ይገድሏችኋል እንጂ፤ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ" እንደዚህ ያለው ፈሪሃ እግዚአብሔር ሲለምድብን ነው "የጽድቅ ሰውነት" የሚገነባው።

"ተቈጡ፤ ኀጢአትንም አታድርጉ።" (ኤፌ 4÷26)

ተሳፍረን ሳይመሽ ቤት መግባት ለምደናል። ይህ ከፍርሃት የተነሣ ያደረብን ልማድ በሰውነታችን ተሠራጭቶ እየቆየ ሲሄድ የእውነትና የሐሰት ልዩነትም እየጠፋብን እንዳይሄድ ያሰጋል። ምላሳችንን ዘመርዋራ መንገድ አስተምረነዋልና አቅንቶ መናገር አይችልም። ዐይናችን ሽሙራራ ነው።

የሐቅ ሚዛን፣ የእውነት ፍርድ፣ የጽድቅ ቁጣ በሌሎች ላይ ከመሰንዘሩ በፊትና በላይ ራስን ሊያስተናግዱበት ግድ ነው። "ጣያትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህ? ብሏል ቅዱስ ጳውሎስ። "ራሳችንን ብንመረምር ባልተፈረደብንም ነበር" ማለት እኮ አስቀድመን እኛው በእኛው ላይ ከፈረድንና ከተስተካከልን ሌላ ፍርድ አይጠብቀንም ማለት ነው። ሌሎችስ ሲወቅሱንና ሲዘልፉን በጥሞናና በአክብሮት እንሰማለን ወይስ ቱግታችን ከራሳችን ሌላ የማንንም ድምጽ እንዳንሰማ ያግደናል?

ቁጣ ብንል ግን ሰውን ለማጥፋት አይደለም። የቁጣን ትንታግ እያየን የወላፈኑ ቀለም የሚያስደስተን ከሆነ ተሳስተናል። ለጽድቅም ብለን፣ ለእግዚአብሔር መንግሥትም እንኳ ብለን "እሳት ከሰማይ ወርዶ ይብላቸው" ብንል የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራም" ይለናል መጽሐፍ። ቁጣን የምንፈልገው ለቁጣነቱ አይደለም፤ ምንም ጌጥ የለውም፤ መቆጣትም በራሱ በቂ ግብ አይደለም። ኀጢአትን እየተጸየፍን በመርዙ የተያዙትን ለማውጣት በፍርሃት እንድንምር ታዘናል። "የሙሴ ቁጣ ተቃጠለ ሕዝቡን አመድ አጠጣቸው" ቢለንም መጽሐፉ ብዙ ሳይርቅ፣ በዚያው ምዕራፍ "አሁን ይህን ኀጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ከጻፍከው መጽሐፍህ አባክህ ደምስሰኝ" ብሏል ይለናል። ወንድሞቼ የምንቆጣ ከሆነ ቁጣችንን የሚበልጥ ፍቅር በጉያችን መኖሩን እናረጋግጥ። ያለበለዚያ የሞት መልእክተኞች ሆነን መቅረታችን ነው።

የእግዚአብሔርን ቁጣ ለመቆጣት፣ የሚፈርድ፣ የሚያድንም እሳት ለመሆን አንዱ እንዳለው "የጽድቅ ሰውነት" ያስፈልገናል። በአንድ አዳር

ጉዳይ አለህ?

የመሪነት ጉዳይ መሪነት አይደለም፤ በጭራሽ። መሪዎች ዋና አጀንዳቸው መምራት የሆነ ቀን አገር ጠፋ፤ ሕዝብ ጠፋ። ማን ኖረ? መሪነት ኖረ። እውነተኞች መሪዎች በቀዳሚ ደረጃ የሚያስቡት ስለመሪነት አይደለም። ስለ ሕዝብ ስለ ሕይወት ስለ ዛሬ፣ ስለ ነገ፣ ስለ ብዙ ነገዎች ነው። መሪነትን ስለራሱ ሲሉ አስበውትም አሰላስለውትም አያውቁም፤ ወደ ግባቸው ሲገሠግሱ እግረ መንገዳቸውን ያገኙት እንደሆነ እንደአስተዋይ ጎረቤት በብልሃት ይይዙታል፣ይጠቀሙበታል፣ ያዳብሩታል፣ይሠሩበታል አንዳንዴ አብሮአቸው እንዳለም ልብ ሳይሉት ወደ ዓላማቸው ሲሮጡ ያው መሪዎች ሆነዋልና ይፋጠጡታል እንጂ ደጅ አይጠኑትም፣ አያሞካሹትም፣አይሰግዱለትም። ያለ መሪነት ጉዳያቸው ግብ ይደርስ ከሆነ እንዲያውም ይህን መሪነት የሚባል «ደፋር ጌታ» እንዴት ዋልክ ሳይሉት ሊሔዱ ይችላሉ።

የመሪነት ጉዳይ ሰው ነው፤ የሰው ተባብሮ ዕድገት፣የሰው ልማት፣ የሰው ሁነኛ መድረሻ። እግዚአብሔር አምላክ መሪዎች ይፈልግ እንደሆን ለሰው ሲል ነው፤ ሰዎች እርሱን እንዲያውቁ ዐውቀውት ሕይወታቸው እንድትለመልም፣ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታቸው እንዲያምር፣ከዘላለም በፊት ያለው ያሁኑ ኑሮአቸው እንዲሰምር።

«ራሳቸውን ብቻ ለሚንከባከቡ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው - እረኞች መንጋውን ማሰማራት አልነበረባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ፤ (ከጠጉሩ የተሠራውን ሱፍ ትለብሳላችሁ) የሰባውን ዐረዳችሁ፤ነገር ግን መንጋውን አትንከባከቡትም።

ደካማውን አላበረታችሁትም
የተጎዳውን አልጠገናችሁትም
የባዘኑትን አልመለሳችሁም
የጠፋውን አልፈለጋችሁትም

ስለዚህ እረኛ የለምና ተበተኑ፤ በመበታተናቸውም ለአራዊት ሁሉ መብል ሆኑ »

(በነቢዩ በሕዝቅኤል በኩል 34:2-5)

እንግዲያው በማያወላዳ ቋንቋ የእረኞች ጉዳይ በጎች መሆኑ ታወቀ፣ተገለጠ። በጎች ምን እንዲሆኑ የተባለ እንደሆነ ዝርዝሩ ይፋ ነው። በመስኩ እንዲሰማሩ÷ እንዲመገቡ፣እንዲበረታቱ፣ሲጎዱ እንዲጠገኑ፣ ሲባዝኑ እንዲመለሱ፣ ሲጠፉ እንዲፈለጉ።

በዚሁ የእረኝነት ዘይቤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እረኛ/መሪ የመሆኑ ዓላማ መሪ መሆን እንዳልሆነ ገለጸ፤ ያልቁን ዋና ጉዳዩ የሰዎች ሕይወት ልማት መሆኑን አበሰረ።

«እኔ ሕይወት እንዲኖራችሁ እንዲትረፈረፍላችሁ መጥቻለሁ መልካም እረኛ እኔ ነኝ » (ዩሐንስ ወንጌላዊው እንደጻፈው 10:10-11)

መሪ መሆን የምትሹ ወይም መሪዎች የምትባሉ ወይም ስለ መሪነት የምታስቡ ሁሉ ጉዳያችሁ ምንድነው?